ምዕራፍ 6

የተቃራኒ ጾታ ግንኙነትን በሚዛን ማድረግ

አገልጋይ በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚያገለግልበት ወቅት ከብዙ ዓይነት ሰዎች ጋር ይገናኛል። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ከተቃራኒ ጾታ መገናኘት ነው። አገልጋይ በአደባባይ በመሰበክና በማስተማር እንደሚያገለግል ሁሉ በግል ምዕመናንን በመጎብኘት፣ በማማከር፣ ከእነርሱ ጋር በግል ጊዜ መስዶ በመጸለይ ያገለግላል። አገልጋይ በተለይ በግል ከምዕመናን ጋር በሚያሳልፍበት ወቅት በተቃራኒ ጾታ ፈተና ሊጠመድ የሚችልባቸው እያሌ ሁኔታዎች ይኖራሉ።

በአብዛኛው መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡ አገልጋዮች በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚታዩትን የተለያዩ የግልና የጋራ ችግሮች ሲያወሩ ይደመጣሉ። ሆኖም አልፎ አልፎ ካሳጋጠመ በስተቀር ብዙ አገልጋዮች በተቃራኒ ጾታ ፈተና ያጋጠማቸውን ፈተና ሲናገሩ አይደመጡም። የአገልጋዮችን በተቃራኒ ጾታ መፈተን አስማውራት ችግሩ እንደሌለ አያመለክትም። ይልቁንም ችግሩ እንዳለና አገልጋዮች ግን ማውራት የማይፈልጉት ጉዳይ እንደሆነ መመልከት ይቻላል። አገልጋዮች በተቃራኒ ጾታ መፈተናቸውን ለመናገር የሚፈሩባቸው ምክንያቶች ምንድናቸው? መንፈሳዊ አገልጋዮች ይህን አደንዳ ማንሳት ከማይፈልጉባቸው ምክንያቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም፦

- ✓ መንፈሳዊ ለው በተሰይም የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነ ለው የወሲብ ለሜትም እንደሌለው መታሰብ
- ✓ አገልጋዩ ሥጋዊ ምኞቱን ገና ያልገደለ ሥጋዊ ለው እንደሆነ ለለሚያለገምተው መንፈሳዊ ስመባል ብቻ ችግሩን መደበቅ
- ✓ መንፈሳዊ አገልጋይ ስሜቱን በመግዛት ከእግዚአብሔር ጋር መጨረስ አለበት እንጂ ይህን ጉድ ወደ ውጭ ማውጣት እንደሌለበት መገመት
- ✓ አገልጋዮች እንዲሁም የቤተክርስቲያን መሪዎች ይህን እንደ ነውር ለለሚያዩ ችግሩን ሲናገር አገልግሎቱ በአደጋ ላይ ሲወድቅ እንዲሁም በእነርሱ ዘንድ ያለው ተቀባይነት ሲቀንስ እንደሚችል ማሰብ
- ✓ የለሙት ለዎች ምሥጢሩን ለሌሎች ለዎች በተሰይም ለትዳር ጓደኛ ቸው መናገር እንደሚችሉ መስጋት
- ✓ በዚህ ጉዳይ አገልጋይን ሊረዱ የሚችሉ የበለሉ ሰዎች በአካባቢው አለመኖራቸውና የመላለሱት ናቸው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱና ሌሎችም ተመሳሳይ ምክንያቶች አገልጋዮች ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያላቸውን የግንኙነት ችግር አስመነጋገራቸውን እንዲሁም ቤተክርስቲያንም በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ ትምህርት አለመሰጠቷን ያመለክታሉ። ከዚህም የተነሳ ጥቂት የማይባሉ አገልጋዮች በተለያዩ ሥፍራዎች በዚህ ፈተና ወድቀው ሕይወታቸውንና አገልግሎታቸውን እንዲሁም በቤተክርስቲያን ለምና በምዕመናን ላይ ትልቅ መንፈሳዊና ሥነልቦናዊ ጉዳት አድርሰዋል።

አገልጋይ ከለዎች ሁሉ ጋር መልካም ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስጢሞቴዎስ «ሽማግሌ የሆነውን አትግሥጸው፤ እርሱን ግን እንደ አባት፣ ጎበዞችን እንደ ወንድሞች፣ የሸመገሉትን ሴቶች

እንደ እናቶች፣ ቆነጃጅቱን እንደ አኅቶች በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው» (1ጢሞ.5፡1-2) በማለት ከወንዶችና ሴቶች እንዲሁም ከዕድሜያ አኳያ ደግሞ ከታላላቆችና ከታናናሾች ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረው እንደሚገባው ይመክረዋል። ለለዚህ ዝምታውን ሰብሮ ለችግሩ አማራጭ መንገድ መፈለግ መልካም ይሆናል።

አገልጋይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነትና እንዴት ራሱን ተገቢ ካልሆነ የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት መጠበቅ እንደሚችል ከማየታችን በፊት አንዳንድ ቅድመ አላቦችን መጥቀስ ለግንዛቤ ይረዳል።

- ✓ አገልጋይ ከወሲብ ፈተና ራሱን የመከላከል የተፈጥሮ ወይም መንፈሳዊ ክትባት አልወሰደም። ለለዚህ ማንኛውም አገልጋይ በወሲብ ሊፈተን ይችላል። ማንም ጥሩ መንፈሳዊ አገልጋይ ነው የሚባለው አገልጋይ ሁሉ ለወሲብ ፈተና የተጋለጠ ነው።
- ✓ የወሲብ ፈተና ሁልጊዜ ከሴት በኩል ይጀምራል ማለት ስህተት ነው። ሴት ዘወትር ለይጣን ተጠቅሞ ወንድን ወይም አገልጋይን የሚፈትንበት መሣሪያ ነው ብሎ ማሰብ ስህተት ነው። የወሲብ ፈተና በአገልጋይም በሴትዋም ሊጀምር ይችላል።
- ✓ መንፈሳዊ አገልግሎት መከታ በማድረግ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ውጭ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት የሚፈልጉ አገልጋዮች ይኖራሉ። ብዙ ሴቶችን በዝሙት ኃጢአት የጣሉ አገልጋዮች እንዳሉ ግልጽ ነው።
- ✓ መንፈሳዊ አገልግሎት አንፈልጋለን በማለትም ሌላ ለውር ዓላማ ያላቸው ሴቶችም እንዳሉ ግልጥ ነው። አገልጋዮችን ለማጥመድ የተለሰፉ እና የጣሉ ሴቶችም እንደሚኖሩ ማወቅ አስፈላጊ ነው።
- ✓ በማንኛውም ምክንያትና መንገድ አገልጋይ ከምዕመናን ጋር የሚፈጸመው የወሲብ ግንኙነት ኃጢአት ነው።
- ✓ አገልጋይ ለለወሲብ ፈተና በማወቅ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለመቻልና ቸልተኛ መሆን ኃላፊነትን በትክክል ያለመወጣት ምልክት ነው።
- ✓ በአገልግሎት ግንኙነት ውስጥ ተገቢውን የግንኙነት ርቀት ወይም ወሰን መጠብቅ ያለበት አገልጋዩ ነው። አገልጋዩ በምንም መንገድ ለሚፈጸመው የሥነምግባር ጉድለት በቅድሚያ ተጠያቂ ነው። አገልጋዩ አስቀድሞ ተገቢውን የማምለጫ እርምጃ መውለድ ይኖርበታል።
- ✓ አገልጋይ ከሚያገለግላቸው ምዕመናን ጋር በወሲብ ኃጢአት ቢወድቅ የሚወለድበት የእርምት እርምጃ ከፍተኛ ይሆናል። ምክንያቱም አገልጋይ እንደመሆኑ መጠን ምዕመናንን የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነትና ሥልጣን ተሰጥቶት ሥልጣኑን አለአግባብ በመጠቀምና ኃላፊነቱን በመዘንጋት ምዕመናንን የሚጎዳ ተግባር በመፈጸሙ ነው (ማቴ18፡6)።

እነዚህ መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን መረዳት ቀጥለው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱትን አላቦች ለመገንዘብ እገዛ ከማድረጉም በላይ አንዳንድ በሕዝቡ ዘንድ ያሉትን ትክክለኛ ያልሆኑ አስተሳሰቦችን ስማስተካከል ይረዳል።

አገልጋይ በተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ከገደብ አንዲያልፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎች ይኖራሉ። አገልጋይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር በአገልግሎት በሚገናኝበት ወቅት መጠበቅ የሚገባውን የግንኙነት ርቀት አንዲጥስ ሊጋፋፋው ከሚችሰው አገልግሎቶች መካከል አንዱ በማማከር አገልግሎት ወቅት ነው። በማማከር አገልግሎት አገልጋይ ከሴት ጋር የሚኖረው ግንኙነት በጥንቃቄና በሚዛን ካልተጠበቀ ወደ መጥፎ ሁኔታ ሊያመራው ይችላል። ከእነዚህም አንዳንድ ሁኔታዎች እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል። አንዳንዱ ፈተና ከራሱ ከአገልጋዩ የሚነሳ ይሆናል። አገልጋይ በወሲብ ፈተና ውስጥ መግባቱን ሊያሳዩ የሚችሉ ውስጣዊ ምልክቶች አሉ። ከእነዚህም ሰምሳሌ ያህል፦

- በአገልግሎት ያገኛትን ሴት ማሰብና በአዕምሮው ስለእርስዋ መልካም ነገሮች ማሰላሰልና «እንዴት መልካም ሴት ናት» ብሎ ከራስ ጋር ማውራት መጀመር
- ያችን ሴት ከትዳር ጓደኛው ጋር በማነጻጸር ከትዳር ጓደኛ የተሻለች እንደሆነች ማሰብ
- አገልጋዩ መልካም አገልጋይ በመሆኑ በእርሱ እንደተማከረች ዓይነት አድርጎ ማሰብና አንድ ነገር ቢጠይቃት ፈቃደኛ ልትሆን እንደምትችል መገመት
- ከዚያች ሴት ጋር ስመገናኘት ማንኛውንም አማራጭ መንገድ ሰመጠቀም መሞከር
- ከሴትዬዋ ጋር በአሳብ ወሲብ መፈጸም (በዓይን አይቶአት ተመኛት፣ በልቡም ከእርስዋ ጋር ማመንዘር ይጀምራል)
- አገልጋይ የራሱን ሁኔታና ችግር ስዚያች ሴት ማካፈልና የእርስዋን አንከብካቤ መሻት እና የመሳሰሉት ናቸው።

አገልጋይ ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ሲያደርግ ራሱን ሊያገኝ በፈተና እንዲወድቅ የሚያዘጋጁ ቅድመ ሁኔታዎች መሆናቸውን በመረዳት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይገባዋል። እነዚህን ምልክቶች በውስጡ እያዳመጠና እያየ በጭፍን ምንም እንዳልሆነ የሚሄድ ከሆነ በወሲብ ፈተና መውደቁ አይቀርሰትም።

አንዳንድ ፈተና ደግሞ ከውጭ የሚመጣ ይሆናል። ከአገልጋዩ ሳይሆን የእርሱን አገልግሎት ከሚፈልጉ ሴቶች ይሆናል። ይህም ምን ሊመስል እንደሚችል እንደሚከተለው ይገለጸል። ሴት ወደ አገልጋይ ለማማከር አገልግሎት በመምጣት በዝሙት ኃጢአት እንደ ወደቀች ሰአገልጋዩ በዝርዝር ያደረገችውን ሁሉ በምታወራበት ጊዜ የአገልጋዩ የወሲብ ፍላጎት ሊቀሰቀስ ይችላል። ከዚያም አገልጋዩ ራሱን በሰማው ሁኔታ ውስጥ በማስቀመጥ የሆነውን ነገር በአዕምሮው ማሰብና መሰል ይጀምራል። ከማማከር በኋላ በአዕምሮው ስሰማው ሁኔታና ስለሴትየዋ ሁኔታ ማሰላሰል ካበዛና የሠራችው ከፋ ሥራ እንደሆነ ከማሰብ ይልቅ በወሲብ አፈጻጸሙ ላይ ትኩረት በማድረግ ጥሩ የወሲብ ሕይወት ያላት እንደሆነች መገመት ሊጀምር ከአገልጋይ ሥነምግባር መሳቱ ይሆናል።

ሴትዋ ኃጢአትዋን በምትናዘዝበት ጊዜ ራስዋን መቆጣጠር እንደማትችልና ሰጠየቃት ወንድ ሁሉ አሺ የማለት ባሕርይ እንዳላት ከገለጸችለት በአገልጋይ ሕይወት ላይ የሚያስከትለው ፈተና ከባድ ይሆናል።

ሰወንድ ሁሉ ፈቃደኛ መሆኑዋን መናገርዋ ብቻ ሳይሆን ወንድ ሁሉ አገልጋዩንም ጨምሮ ከእርስዋ ጋር ወሲብ እንዲፈጽም ለማድረግ የምታደርጋቸው ተጽዕኖዎች አሉ። እርስዋ ከምትጠቀምባቸው መንገዶች አንዳንዶቹ ቀጥተኛ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ በስውር መልዕክት የሚያስተላልፉ ናቸው። ስምሳሌ ያህል፦

- ✓ የአገልጋዩን ልብ የሚስርቅ ማስትም ወንድ ከሴት የሚፈልገውን አነጋገር መናገር እንዲሁም ቀድሞ የነበራትን ወንድን ሊማርክ የሚችል የወሲብ ታሪክዋን መተረክ
- ✓ ወንድን መማረክ የሚችል አካልዋን የሚያሳይና ወሲብን ሊቀሰቅስ የሚችል አለባበስ ለብሳ ወደ አገልጋይ መምጣት
- ✓ መንፈሳዊ ልብስ አያስበሰችው አገልጋዩን ማቆላመጥና አልፎ አልፎም «አወድሃለሁ» ማለት
- ✓ አገልጋዩ ቢፈልጋት ሰወሲብ ፈቃደኛ መሆንዋን መናገር እና ሌሎችም የሚጠቀሱ ናቸው።

ሴት በማማከር አገልግሎት የምትፈልገውን አገልግሎት አግኝታ ደስ ሲሳት አገልጋዩ ያደረገላት ነገር መልካም እንደሆነ በማሰብ ከእርሱ ጋር መልካም ግንኙነት መመሥረትን ታሰባለች። ይህ በመጀመሪያ የወሲብ ግንኙነት ስማድረግ የታሰበ ነገር ባይሆንም ቀሰ በቀስ ግን ወደዚያ ሊያመራ ይችላል። ከመንፈሳዊ አገልግሎት ውጭ መገናኘት ይጀምራሉ። አገልጋዩ እንደ መንፈሳዊ ሰው መልካም ግንኙነትን ከሚፈልግ ሰው መራቅ ጥሩ እንዳልሆነ ያስባል። የማያገኛቸው ነገር በማይኖርበት ወቅት እንኳ እርስ በርስ ሰመገናኘት መንገድ ይፈልጋሉ። ስልክ ያሰበት አካባቢ ከሆኑ ይደዋወላሉ፣ አንዳንድ ጊዜ ሰሰዓታት ያወራሉ። ከዚያም አንዳቸው ግንኙነታቸውን ይበልጥ ስማጠናከር አንዱ ሰሌላው ክልክል የሆነውን ነገር ሰመከፋፈል ያስባሉ። አብረው ከመቆየታቸው የተነሳ የወሲብ ግንኙነት ቢፈጽሙ በደል እንደሆነም አስከማያስቡበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ።

አገልጋይ በወሲብ ፈተና አንዲወድቁ ሊያደርገው የሚችሉ ሁኔታዎች አሉ። ብዙ አገልጋዮች በወሲብ ቢፈተኑም በፈተናው አይወድቁም። አንዳንዶች ግን በወሲብ ፈተና ሲወድቁ ይታያሉ። በወሲብ ፈተና ሰመውደቅ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

- አገልጋዩ የተፈተነባት ወይም አገልጋዩን የፈተነችው ሴት ቆንጆ መሆን
- አገልጋዩ በትዳር ሕይወቱ ደስታና እርካታ ያላገኘ መሆን
- አገልጋይ ከትዳር ጓደኛው ሰለሚር ወይም ሰረጅም ጊዜ ተሰይቶ የሚኖር ሲሆን
- የሴትዋ ሰወሲብ ዝግጁ መሆንን መግለጥና ይፋዊ ጥያቄ ማቅረብ
- ሁለቱም ሰሰወሲብ ሕይወታቸውና ገጠመኞቻቸውን ቀድሞ የተነጋገሩ መሆን
- አገልጋዩ በሕይወቱ ወይም በአገልግሎቱ የተቸገረበትና ግራ የተጋባበት ወይም የተጨነቀበት ሁኔታ መኖር
- የአገልጋይ በመንፈስ መሰላቸት ውስጥ መሆን፣ ራሱን በመጣል የሕይወትና የአገልግሎት ትርጉም የጠፋበት ሁኔታ ውስጥ መገኘት፣ ስለወደፊቱ በተስፋ መቁረጥ ስሜት ውስጥ መግባት
- የአገልጋይ በአገልግሎት ብዛት በሕይወቱ መዳሸቅ

በወሊብ ፈተና መውደቅ በአንድ ጊዜ አንደ መብረቅ በለው ሳይ የሚወርድ ሳይሆን ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድ ክስተት ነው። አገልጋይ በአንድ ጊዜ ተፈትኖ ሊወድቅ አይችልም ማለት ሳይሆን በአብዛኛው የሚታየው አገልጋይ በወሊብ ፈተና የሚወድቀው በሂደት ውስጥ በሚፈጠረው የግንኙነት ጥልቀት ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችል የአንድን መጋቢ ታሪክ እንመልከት።

መጋቢው ተካ (አውነተኛ ስሙ አይደለም) ይባላል። ባለቤቱ በአንድ መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት ውስጥ ትሠራለች። ከሥራዋ ጸባይ የተነሳ ብዙ ጊዜ ለመስክ ሥራ ጉዳይ ከቤት ውጭ ሳምንታትን ታሳልፋለች። መጋቢ ተካ ተከራይቶ የሚኖርበት ባለቤት ሚስት ደግሞ የቤት አመቤት ስለሆነች በአብዛኛው አቤት አካባቢ ትውሳለች። ተካ በሳምንት ውበጥ ለአንድ ቀን እቤቱ ሆኖ በግሉ ይጸልያል። የቤቱ ባለቤትም ክርስቲያን ስለሆነ ከአርሱ ጋር መጸለይ እንደሚቻል ጠየቀችው። መጋቢውም እምቢ ማለትን ፈራና እሺ አለ። ከዚያም ሁለቱ አብረው መጸለይ ጀመሩ።

ለተወሰነ ጊዜ አብረው ከጸለዩ በኋላ ሌትዬዋ ከባልዋ ጋር ችግር እንዳሳት በመናገር በዚህ ጉዳይ መጋቢ ተካ በጸሎት እንዲያግዛት ጠየቀችው። ስዚያም ከጥቂት ላምንታት በኋላ «ባለፈው ጊዜ ስለትዳራችን ሁኔታ እንድትጸልይልኝ የጸሎት ርዕስ አቅርቤ ነበር። ምን እንደሆነ አልገባኝም። ችግሩ ይቃለሳል ብዬ ተበፋ አድርጌ ነበር። ሆኖም ችግሩ እየባሰበት መጣ» በማለት አጫወተችው። መጋቢ ተካ አንዲህ በመሆኑ አዘኑን በመግለጽ «ተስፋ ላንቆርጥ አጥብቀን መጸሰይ አለብን» በማለት ወደ ጸሎታቸው ሄዱ። አሁንም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከባልዋ ጋር ያላትን ችግር አነሳች። «ዛሬስ ችግሩን በዝርዝር ልነገርህ አፈልጋለሁ» አለችና ከባልዋ ጋር ያላት ችግር በወሊብ ጉዳይ አስመጣጣም እንደሆነ ገለጸችለት። ካገባችው ስድስት ዓመት ቢሆንም አንድም ቀን የወሊብ አርካታ አግኝታ እንደማታውቅ በማልቀስ ነገረችው። ከዚያም ጸለየሳትና ሌላ ጊዜ በስፋት አንነጋገራለን በማለት ተለያዩ።

መጋቢ ተካ ስለአርሰዋ ሁኔታ ማሰብ ጀመረ። «እንዲህ ቆንጆ ሴት ሆና የሚያረካት ባል ማጣትዋ ያሳዝናል። ምነው አግዚአብሔር ጥሩ ባል ለጥቶአት ቢሆን...» አያስ ማሰቡን ቀጠለ። አልፎ አልፎም «እኔስ ቢሆን አረካት ይሆን?» አያስ ያሰላስል ነበር። ከዚያም በጸሎት ቀናቸው ተገናኙ። ጸሎታቸውን ሊጨርሱ «እንዴት ነው ያ ችግር ተፈታ ወይ?» ብሎ ጠየቃት። አርሰዋም በዚያ ሳምንት ስለሆነው ነገር በዝርዝር ነገረችው። ከዚያም አንደተስመደው ማልቀስ ጀመረች። በዚህ ጊዜ መጋቢ ተካ ከተቀመጠበት ቦታ ተነስቶ አርሰዋ የተቀመጠችበት ትልቁ ሶፋ ላይ በአጠገብዋ ቁጭ ብሎ አምባዋን ማበለ ጀመረ። አርሰዋም በአግሮቹ ላይ ጋደም አለች። ሁለቱም ላያውቁ በለሜት ተወረሩና መተሻሸት ጀመሩ። ተካ ምን እንዳደረገ ያወቀው ስሜቱን ከጨረሰ በኋላ ነበር።

መጋቢ ተካ በዚህ ኃጢአት እንዲወድቅ ያደረገው ነገር ምንድነው? በፈተናው አንዳይወድቅ ምን ማድረግ ነበረበት?

✓ ሁለቱም በአንድ ቤት ውስጥ ስብቻቸው ሆነው መጸለያቸው ለፈተና ሊያጋልጣቸው አንደሚችል በመገመት ከአንዲህ ያለ ሁኔታ መሸሽ

ነበረበት። በፈተና ባይወድቁ አንኳ ሌሎች ለምች ወይም ምዕመናን ለብቻቸው አብረው መጸለያቸውን ቢያዩ ወይም ቢሰሙ ሊስናከሉባቸው አንደሚችሉ በማሰብ ለብቻው ከሴት ጋር መሆን አልነበረበትም።

✓ ጸሎቱ የግል ጊዜው በመሆኑ አርሰዋ ከአርሱ ጋር አንድትጸልይ መፍቀዱ ትክክል አልነበረም። አንዲህ ማድረግ አንደሌለበት ቢያውቅም መጋቢው ይሉኝታ በመፍራት ከአርሱ ጋር አንድትጸልይ ፈቃደኛ መሆኑ ስህተት ነው።

✓ መጋቢ አንደ መሆኑ መጠን አቤቱ ቁሚጸልይ በቤተክርስቲያን ውስጥ ጸጥታ ያሰው አንድ ክፍል ውስጥ ሳምንታዊ የግል የጸሎት ጊዜውን ቢያሳልፍ የተሻለ ነበር። ተጠያቂነት በሌለበት በገለልተኛ ቦታ መሆን ለክፉ ነገር ሊያጋልጥ አንደሚችል ማስብ አስፈላጊ ነው።

✓ የሴትየዋን ችግር ካዳመጠ በኋላ በውስጡ የተስማው ተገቢ ያልሆነ ስሜት ነበር። ለአርሰዋ የቀድሞ ዓይነት አመለካከት ማለትም አንደ አህት ብቻ የማየቱ ነገር መቅረቱን አንደተረዳ ከአርሰዋ ጋር ዳግመኛ መጸለይ አልነበረበትም። በውስጡ የተሰማው ስሜት «አሁን ያለህበት ሁኔታ ለኃጢአት የሚጋብዝህ ስሰሆነ ከዚህ ነገር ቶሎ ሽሽና አምልጥ» የሚል መልዕክት ነበረው። አርሱ ግን ይህን የማሰጠንቀቂያ ደውል ቢስማም የሚገባውን አርምጃ አልወሰደም።

✓ በወሊብ የተመኖት ሴት አጠገብ ቁጭ ብሎ አምባዋን ማበለ መሞከር ምን አደጋ ሊያመጣበት አንደሚችል መገንዘብ አቅቶት ወይም ለአርሰዋ ያለውን ፍቅርና የተንከባካቢነት መንፈስ ለማሳየት ከአርሰዋ ጋር የነበረውን የቦታ ርቀት መጠበቅ ነበረበት። ሆኖም ከአርሰዋ ጋር በአካል ከመነካካት አልተቆጠበም። ይህ ደግሞ በኃጢአት ውስጥ አንዲወድቅ የመጨረሻ አርምጃው ሆነ።

አገልጋይ በዝሙት ኃጢአት ቢወድቅ ምን ማድረግ አለበት? አገልጋይ በዝሙት ኃጢአት በሚወድቅበት ጊዜ ከማወቅም ሆነ ግራ ከመጋባት የተለያዩ አርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል። አገልጋይ ቢወበድ ለሕይወቱ ደህንነት ሊጠቅሙ የሚችሉ መልካም የሆኑ አርምጃዎች አሉ። እነዚህ አርምጃዎች ሕግጋት አይደሉም፣ ነገር ግን ከአግዚአብሔር ቃል አኳያ ሊታዩ አገልጋይ ሕይወቱን እንደገና ማስተካከል ወደሚችልበት አቅጣጫ ሊመሩ የሚችሉ ጠቃሚ አሳቦች ናቸው። አነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

1. አገልጋዩ የፈጸመው ነገር ኃጢአት መሆኑን መቀበል። አገልጋይ ከትዳር ውጭ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ወሲብ ከፈጸመ ኃጢአት እንደሠራ ሊቀበል ይገባል። ይህን ሁኔታ ለማስተባበል መሞከር ወይም ደግሞ በተለያዩ መንገዶች እንዳይታወቅ ለማድረግ ማሰብና እርምጃ መውሰድ ኃጢአቱን ያባዛዋል። አንድ የነበረው ኃጢአት ሌሎች ተጨማሪ ኃጢአቶች እንዲፈጸመ ያደርጋል። የመጀመሪያውን ለመሸፈን ተብሎ ሌላ ኃጢአት ይፈጸማል። ለለዚህ አገልጋይ በዝሙት ኃጢአት ውስጥ ሲወድቅ የፈጸምኩት ነገር ትክክል አይደለምና መቀበል አለብኝ ወደሚል አሳብ መምጣት ይጠይቅበታል።

2. ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር መናዘዝ። አገልጋይ ኃጢአት በመፈጸሙ በቅድሚያ የተበደለው አርሱን ለአገልግሎት የጠራው አግዚአብሔር እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጓል። ከዚያም በኋላ ለእግዚአብሔር ያደረገውን ነገር በመናገር ከልብ የሆነ ንሰሐ መግባት ይገቧል። ምናልባት እግዚአብሔርን

እንዳለዘዘነው የማይሰማው ወይም የንስሐ ልብ እንደሌለው የሚሰማው ከሆነ ይህ የጥፋት መንገድ በመሆኑ ምሕረቱ ብዙ የሆነ እግዚአብሔር የንስሐን መንፈስ እንዲሰጠው መጠየቁ መልካም ነው። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የንስሐ መንፈስ በመከልከልም ሰዎችን ሊቀጣ ስለሚችል የንስሐ ልብም ለማግኘት እግዚአብሔርን መለመን ጥሩ ነው።

አገልጋይ እርሱን ታማኝ አድርጎ መንጋውን እንዲጠብቅና እንዲመግብ የሾመውን ጌታ እግዚአብሔርን በማለዘኑ የሆነውን ነገር በተሰበረ መንፈስና በተዋረደ ልብ መናዘዝ አስፈላጊ ነው። አንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከበግ እረኝነት ላይ አንስቶ፣ እርሱን ሊያጠፉ የሚፈልጉትን ጠላቶቹን አስወግዶ፣ የሚያስፈልገውን ነገር ሰጥቶ የእስራኤል ሕዝብ ንጉሥ እንዲሆን ያደረገው ንጉሥ ዳዊት ከእንድ ምስኪን ሰው ሚስት ጋር በማመንዝር እንዲሁም የሠራው ኃጢአት እንዳይታወቅበት ለመሸፈን ሰውየውን በማስገደሉ እግዚአብሔር በጣም አዝኖበት ነበር። ንጉሥ ዳዊት በነቢይ በኩል በእግዚአብሔር ፊት የሠራውን ኃጢአት ሲያስተውል እጅግ እዘነ። እርሱን በሾመውና አሁን በኃጢአቱ ላሳዘነው ለሕያው የሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር በተሰበረ መንፈስና በተዋረደ ልብ ሆኖ ንስሐ ገባ (መዝ 51)።

3. ስግዚአብሔር ደቅርታ እንዳደረገለት መቀበል፦ አገልጋይ የዝሙት ኃጢአት በመሥራቱ ተጸጽቶ ንስሐ ከገባም በኋላ ከሚቸገርባቸው ነገሮች አንዱ እግዚአብሔር ይቅር እንዳለው እርግጠኛ መሆን እለመቻል ነው። «እኔ አገልጋይ ሆኜ ይህን ከፋ ነገር በእርሱ ፊት ሠርቼ እግዚአብሔር ይቅር ይለኛል ወይ?» እያለ ራሱን ይጠይቅና ይጠራጠራል። አገልጋዩ ስለኃጢአት ይቅርታ ሌሎችን ያስተምር የነበረው ትምህርት ለእርሱ እንደሚሠራ ማመንና መቀበል ይቸግረዋል። ለይጣንም ይህን ፅድል በመጠቀም አገልጋዩ ከፍተኛ የበደለኛነት ስሜት ተሰምቶት ከእግዚአብሔርና ከምዕመናን እንዲርቅ ያደርጓል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ቀስ በቀስ አገልጋዩ ከእግዚአብሔር እንዲርቅና «መቼም እግዚአብሔር ይቅር ስለማይለኝ» ብሎ በኃጢአት ውስጥ መመላለሱን እንዲቀጥል ይገፋፏል። ሆኖም ግን እውነቱ እግዚአብሔር ንስሐ የገባውን ማንኛውንም ኃጢአተኛ ይቅር ይላል። ስለዚህ የእግዚአብሔርን የኃጢአት ይቅርታ መቀበል የተቸገረ በዝሙት የወደቀ አገልጋይ ቃሉ ስለኃጢአት ይቅርታ የሚለውን ማለላለል ይጠቅሟል (ምሳ 28:13፣ 1ዮሐ.1:7-9፣ መዝ.32:1.5)።

4. ከሠራው ኃጢአት የተነሳ ሊከፍል የሚችለውን ዋጋ መገመትና ለመቀበል መዘጋጀት፦ ኃጢአት ከተሠራ ምንም ቢሆን ዋጋ ሳያስከፍል አይቀርም። አገልጋይ ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር በሚናዘዝበት ወቅት የኃጢአት ይቅርታ ያገኛል። ነገር ግን በመዝራትና በማጨድ መንፈሳዊ ሕግ (ገላ.6:7) አገልጋዩ የዘራውን የኃጢአት ፍሬ ያጭዳል። ኃጢአት የሚያስከትለው ቁስል ሕመሙ ቢድንም ጠባሳው ግን ይኖራል። ለአገልጋይ የዝሙት ኃጢአት መሥራት የሚያስከትለው ጉዳት ብዙ ነው። አገልጋይ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ክብርን ያጣል። ምዕመናን ለእርሱ ያላቸውን ክብርና ተቀባይነት መስጠት ያቆማሉ ወይም ይቀንሳሉ። ስዎች በቅድስና እንዲኖሩ ለማስተማር ድፍረት ያጣል። በድርጊቱ ቤተክርስቲያን ጌታን ባላመኑት ለዎች ዘንድ ትስደባለች። «የዚያ ቤተክርስቲያን አገልጋይ አመንዝራ» እየተባለ ሊወራ ይችላል። በዚህም የአገልጋይ ቤተሰብ በሆነው ነገር ያገናል፣ ምናልባትም የትዳር መናጋትም ሊያስከትል ይችላል። የዝሙት

ኃጢአቱ የተፈጸመው ካላገባች ሴት ልጅ ጋር ከሆነ ምናልባት ልጅ ቢጠሰድ የሚመጣው ችግር የበለጠ ውስብስብ ይሆናል። ባለትዳር ከሆነች ደግሞ ከሌላው ወገን ጋር ግጭት ሊፈጠር ይችላል።

አገልጋይ በዝሙት ኃጢአት ውስጥ እንደ ወደቀ ንስሐ ገብቶ ሕይወቱን አስኪያስተካክል ድረስ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ማቆም ይኖርበታል። ይህ ደግሞ የኑሮውን ሁኔታ አሳሳቢ ያደርገዋል። መንፈሳዊ አገልግሎቱን ካቆመ ከቤተክርስቲያን የሚለጠው ደመወዝ ሊቋረጥበት ይሆናል። ከዚህ የተነሳ ደግሞ ቤተሰቡ በኢኮኖሚ ችግር ላይ ይወድቃሉ። ለምግብ፣ ለቤት ኪራይ፣ ለልጆች የትምህርት ቤት ክፊያ እና ለመሳሰሉት ወጪዎች ገንዘብ ከየት ይመጣል? አገልጋይ መንፈሳዊ አገልግሎትን ስለመተው ወይም ከአገልግሎት ስለመለናበት ሲያስብ እነዚህን ሁኔታዎች ሁሉ ያስባል።

አነዚህን ሊመጡ የሚችሉትን ነገሮች በማሰብ አገልጋይ ምን ማድረግ ይጠበቅበታል? አገልጋይ አነዚህ ነገሮች ሊመጡ እንደሚችሉ በማሰብ በእግዚአብሔር ጸጋ ለመቀበል ራሱን ማዘጋጀት ይኖርበታል። እግዚአብሔር በዚህ አስቸጋሪ የሕይወት ጉዞ ውስጥ ከእርሱ ጋር እንዲሆን በመለመንና በእርሱ በመታመን አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። አገልጋዩ በታማኝነት ራሱን ለመግለጽ ዝግጁ ከሆነና ቀጥሎ የተጠቀሱትን እርምጃዎች ከወሰደ ሊመጣ ያሰውን ጉዳት ሊቀንስ ይችላል።

5. ሁኔታውን ለመንፈሳዊ ሞግዚት ወይም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የቤተክርስቲያን መሪዎች በመናገር ቤተክርስቲያን የምትወስደውን ስርምጃ መቀበል፦ አገልጋይ በደሉን ሳይደብቅ ለመንፈሳዊ ሞግዚት ከተናገረ አብረው እንዴት ለቤተክርስቲያን መሪዎች በመንገር ተገቢው እርምጃ እንደሚወሰድና እንዴት በደሉ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት መቀነስ እንደሚችል ማሰብ ይቻላል። ጽድቅ ሳይጎድል ጉዳዩን በጥበብ በመያዝ አገልጋዩንም ሆነ ቤተሰቡን እንዲሁም በበደሉ የተጎዱትን ወገኖች ማትረፍ እንደሚቻል መቀየስ የተሻለ ይሆናል። አገልጋይ የሠራውን በደል ለሚመለከተው ክፍል ማሳወቅን ችላ ካለ ወይም ፈርቶ ከተወው የሚመጣው ጉዳት የባሰ ይሆናል። በመንፈሳዊ አይታ ሊታይ አገልጋይ ኃጢአት በመሥራቱ የቤተክርስቲያን ሥራ ይታሠራል። እግዚአብሔር እርም ባለበት ሁኔታ ከሰዎች ጋር አብሮ አይሠራም። እግዚአብሔር በማይሠራበት አካል ውስጥ ያሉ ምዕመናን መንፈሳዊ ድርቀትና ረሃብ ይይዛቸዋል። በሕይወታቸው አያድጉም፣ እርስ በርስ ያላቸውም ግንኙነት የተበላሸ ይሆናል። ይህም ብቻ ሳይሆን አገልጋይ ራሱ ኃጢአቱን ሳይናዘዝ በሌላ መንገድ ከተደረሰበት በእርሱ ላይ የሚወሰደው እርምጃ ከባድ ይሆናል። ሰዎችም ለእርሱ የሚራራ ልብ አይኖራቸውም። «አገልጋይ ሆኖ እንዴት እርም ይዞ እግዚአብሔርን ያገለግላል?» በማለት በእርሱ ላይ ይጨከናሉ። ይህ ሰዎች በጸሎታቸው አገልጋዩን እንዳይደግፉት እንቅፋት ይሆናል።

6. ሁለንተናዊ ፈውስ ስለሚያገኝ ድደል ተገቢውን ስገዛዝት መፈጸግ፦ አገልጋይ በወሲብ ኃጢአት ሊወድቅ ከዚህ ሁኔታ ተፈውሶ እንደገና እንደ ቀድሞ ለመሆን ተገቢውን የማማከርና የድጋፍ አገልግሎት ማግኘትን አንዲሁም ጊዜ ወስዶ በእግዚአብሔር ፊት መሆንን ይጠይቃል። በዚህ ችግር ውስጥ የወደቀ አገልጋይ የሕይወት ተሐድሶ ለማግኘት እንድ ሊረዳው የሚችለው ታማኝ መንፈሳዊ ሞግዚት ያስፈልጓል። በእርሱ ተስፋ

ሳይቆርጥ እርሱን ለመመሰል ጸጋ፣ ጥበብና እውቀቱ ያለው ሰው አገልጋዩን አየሞረደ የተሻለ አገልጋይ ሆኖ እንዲወጣ ከዚህ ውድቀት ሊያወጣው ይችላል።

አገልጋይ በዝሙት ላለመውደቅ እንዴት መከላከል ይችላል?

አገልጋይ ምዕመናን በኃጢአት እንዳይወድቁ ራሳቸውን የሚጠብቁበትን መንገዶች እንደሚያሳያቸው ሁሉ ራሱም በኃጢአት በተለይም ከተቀራኒ ጾታ ጋር ባለው ግንኙነት ችግር እንዳይመጣበት ራሱን መጠበቅ የሚችልባቸውን መንገዶች መቀየስ ይኖርበታል። ከእነዚህም የመከላከያ መንገዶች አንዳንዶች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል። እነርሱም፦

ራስን ማመቅ፦ አገልጋይ ራሱን ማወቅ ከዝሙት ኃጢአት እንዲከላከል ይረዳዋል። አገልጋይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ባለው ግንኙነት ምን ጠንካራና ደካማ ጎን እንዳለው ካወቀ ራሱን ለደካማ ጎኑ በማያጋልጥ ሁኔታ መመላለስ ይችላል። አገልጋይ ሰው እንደሆነና በዚህ ፈተና እንደማንኛውም ሰው መፈተን እንደሚችል ሲቀበል ይገባል። «እኔ በዚህ ፈተና አልወድቅም» በማለት በራስ መተማመን ማብዛት የማያዛልቅ ወቅታዊ መፎክር ብቻ ሆኖ የሚቀርበት ሁኔታ ሊመጣ ይችላል። ስለዚህ «ከዝሙት ሽሽ» በሚለው መርሕ አሳብ መሠረት አየኖረ በጥበብና በማስተዋል በእግዚአብሔር ላይ ታምኖ ማገልግል መልካም ነው።

ስገሷጋዩ የተዳቢ ሕጸመቱን ከሚገባ ማጠናከር፦ ይህ ከፈተና ባያድንም በፈተና ከመውደቅ ሊጠብቅ ይችላል። አገልጋይ የሚፈልገው ፍላጎት በተለይም በተቃራኒ ጾታ በኩል ሊሟላለት የሚገባው ፍላጎት ከተሟላለት ቢፈተንም የመቋቋም ኃይል ያገኛል። «ይህ እኔ ያጣሁት ነገር ስለሆነ በዚህ በኩል ማግኘት አለብኝ» ብሎ በፈተናው ውስጥ ጭልጥ ብሎ አይገባም።

ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያለውን ግንኙነት በገደብ ማድረግ። የሴት ወዳጅ አለመሆን አስፈላጊ ነው። ተቃራኒ ዋልታዎች እንደሚሳሳቡ ሁሉ ተቃራኒ ጾታዎችም የመሳሳብ ኃይል በመካከላቸው ስለሚኖር ተገቢ ያልሆነ መቀራረብ አለማድረግ ይረዳል። ከወንዶች ይልቅ ከሴቶች ጋር ለመሆን የሚፈልግ አገልጋይ ለምን እንዲህ እንደሚያደርግ ራሱን ሊጠይቅ ይገባል። የሴት ወዳጅ የሆነ አገልጋይ ወሰኑን ጠብቆ ከሚሄድ አገልጋይ ይልቅ በወሲብ ፈተና የመውደቁ ዕድል ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም ከተቃራኒ ጾታ ጋር ወሲብ ነክ የሆኑ ቀልዶችንና ጫወታዎችን ማስወገድም ያስፈልጋል። ከአገልጋይ እንደበት የማያንጹ ወሲባዊ የሆኑ ቀልዶች፣ አስተያየቶችና ንግግሮች መሰማት የለባቸውም። አገልጋይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ትክክለኛ የአገልግሎት ወሰን ሊያከብር ይገባል።

ስንዶ ስገሷጋዩ ከስግዚአብሔርና ከቤተክርስቲያን የተሰጠው የስገሷግሎት ኃላፊነት ምን ያህል ታላቅና ክብር እንደሆነ ዘወትር ማሰብ፦ አግዚአብሔር የሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎትና ለዚህም አገልግሎት መጠራት ትልቅ ክብር ነው። አግዚአብሔር ብቃት የሌለውን ሰው ጠርቶ በምሕረቱ ብቻ የታላቁ ጌታ አገልጋይ እንዲሆን እንዳደረገው ዘወትር በማሰብ ይህን ታላቅ ክብር ያለውን ነገር ሊያዋርድ ከሚችል ከማንኛውም ከፉ ነገር ለመሸሽ ያስችላል። የጥሪው ታላቅነት በውስጡ የሞላው ከሆነ አሳቡ የተያዘው በዚያ ስለሆነ ለዚህ ርካሽ ለሆነው ኃጢአት ራሱን አይሰጥም።

ስጊዜያዊ የስሜት እርካታ ብሎ የሱስን ስምነትና ስገሷግሎት ማቃሰል የሕሊና ጠባሳ ጥሎ እንደሚያልፍ ማሰብ። የወሲብ ኃጢአት መፈጸም በሕይወት፣ በቤተሰብና በአገልግሎት ላይ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት እጅግ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ አንደ መንፈሳዊ አንዲሁም አንደ ባለአዕምሮ በስክነ ሁኔታ በማሰብ ውጤቱን ማነጻጸር ወደዚህ ዓይነት ድርጊት ሲያመራ ከሚችል ሁኔታ እንዲርቅ ያግዚል።

እግዚአብሔር ራስን የመግዛት ጸጋን እንዲጨምር መጸለይ፦ አገልጋይን ከፈተና ወጥመድ ሊያስመልጥ የሚችል አግዚአብሔር እንዳለና ከተጠየቀ ጸጋውን ሊሰጥ ዝግጁ መሆኑን ምንጊዜም ሊረሳ አይገባም። ቁምነገሩ የወሲብ ፈተና ሲጀምር በግልጽ ለእግዚአብሔር ሁኔታውን በመግለጽ ራስን የመግዛት ጸጋ እንዲሰጥ መለመን አስፈላጊ ነው። ሆኖም ግን በዚህ ላይ መረሳት የሌለበት አንድ ነጥብ አለ። ይኼውም እግዚአብሔር ራሱ አገልጋዩን ጎትቶ ካለበት ሁኔታ አንዲያወጣው ብቻ መጠበቅ የራስን ድርሻ መዘንጋት ነው። በእርግጥ አግዚአብሔር ራስን የመግዛት መንፈስ ይሰጣል። ሆኖም አገልጋይ በወሲብ ሲፈተን ከዚያ ሁኔታ በመሸሽ ራሱን መርዳት ይችላል። ስለዚህ አገልጋይ አያወቀ በወሲብ ፈተና ውስጥ ሊያስገባው በሚችል ሁኔታ ውስጥ ቁጭ ብሎ «እግዚአብሔር ሆይ አድነኝ» ማለት አባቶች «መንገድ ዳር አድሮ ጌታ ሆይ በስላም አሳድረኝ» እንደሚሉት ከንቱ ጸሎት ነው። ስለሆነም አገልጋይ እግዚአብሔርን እየለመነ እንዲሁም ራሱንም የሚያድንበትን መንገድ መፈለግ እንደሚገባው መርሳት የለበትም።

ሰይጣን የስገሷጋዩን ሕጸመትና ስገሷግሎት ስማጥፋት የሚጠቀምበት መንገድ መሆኑን በማወቅ ደህ ሁኔታ ሲመጣ ስጥብቅ መዋጋት፦ አገልጋይ በዝሙት ኃጢአት ከወደቀ ተመልሶ አግዚአብሔርን አንደገና ለማገልገል ያለው ድፍረት እንስተኛ ነው። በጎብረተሰቡ ዘንድ በዝሙት ኃጢአት መውደቅ እጅግ አስከፊ በደል ተደርጎ ስለሚቆጠር አገልጋይ በጎብረተሰቡ ውስጥ ያለው ምስክርነት ስለሚበላሽ ያለው ተቀባይነት በአንድ ጊዜ ይወርዳል። ሰይጣን ይህን ስለሚያውቅ እግዚአብሔር በሕይወታቸው የሚጠቀምባቸውን አገልጋዮች በዚህ ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ሰይጣን ኃጢአቱ የሚያስከትለውን ጉዳት ሸፍኖ አሁን አገልጋዩ ሊያገኝ የሚችለውን ጊዜያዊ ደስታ ያለየዋል። አገልጋዩ በዚህ የሰይጣን ሽንገላ ከወደቀ በኋላ ደግሞ እጅግ ከፋ የተባለ ኃጢአት አንደፈጸመ በማሳየት ራሱን እንዲጠላ፣ አግዚአብሔር አንደማይቀበለውና ቤተክርስቲያንም እንደምትጸየፈው በማሳየት በበደለኛነት ስሜት ተይዞ ያለይቅርታ እንዲኖር ለማድረግ ጥረት ያደርጋል። ስለዚህ አገልጋይ ሆይ! ሰይጣን የሚያቀርብልህ ይህ ጊዜያዊ ደስታ የሚገድል መርዝ መሆኑን በመገንዘብ ላለመጠጣት የሚመጣበትን መንገድ አጥብቀህ ጠብቅና ተዋጋው!

የቀርብ ጓደኛ መያዝ፦ መንፈሳዊ ሞግዚት ካሶ ስእርሱ በማካፈል ምክር ማግኘት። አገልጋይ ጓደኛ ከሚያስፈልግበት ምክንያቶች አንዱ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ባለው ግንኙነት የወሲብ ፈተና ሲያጋጥም ሁኔታውን በማካፈል ምክር ለማግኘት ነው። አገልጋይ ለእርሱ ቅርብ ለሆነው ታማኝ ጓደኛው ወይም ለመንፈሳዊ ሞግዚቱ ምሥጢሩን ቢያካፍል የተጸነሰው ኃጢአት እንዳይወለድ ለመከላከል ይረዳል። ይህ ጓደኛ ወይም መንፈሳዊ ሞግዚት ከአገልጋዩ ጋር አብሮ ይጸልያል አንዲሁም መውለድ የሚገባውን አማራጭ መንገዶች ያሳየዋል። አገልጋዩም አሰቀድሞ በመናገሩ ራሱን ለጓደኛው

ወይም ለመንፈሳዊ ሞግዚቱ ተጠያቂ ስለሚያደርገው ከፊት ይልቅ ከሁኔታው ለማምለጥ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል።

በሥነመለኮት ትምህርት ቤት ወይም አገልጋዮች ለአገልግሎት ከመውጣታቸው በፊት በሚሰጣቸው ሥልጠና ወቅት ከተቃራኒ ጾታ ጋር ሊኖረው ስለሚችለው ግንኙነትና ፈተና ሲገጥማቸው እንዴት ማስተናገድ አንደሚገባቸው ማሰተማር። ይህም አገልጋዮች የአዕምሮ ቅድመ ዝግጅት እንዲኖራቸውና ፈተናው ሲገጥማቸው የመፍትሔ አቅጣጫ እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል።

የምሰጠናንን ጉብኝት ሰብቻ ሰጠማድረግ፦ አገልጋይ ምዕመናንን በተለይም ተቃራኒ ጾታን በቤታቸው ወይም በሆነ ቦታ በሚጎበኝበት ጊዜ ለብቻው ባያደርገው መልካም ነው። ሁኔታዎች ከአቅም በላይ ካልሆኑ በስተቀር አገልጋይ ከሌላው አገልጋይ ወይም ከአንድ ምዕመን ጋር በመሆኑ አህቶችን ቢጎበኝ ከፈተና ለመዳን ይረዳል። ከፈተና ለመዳን ብቻ ሳይሆን አገልጋይ ለብቻው አህቶችን ሲጎበኝ የሚያዩ ሰዎችም አሪምሮአቸው እንዳይቆሸሸባቸው ለእነርሱም መሰናከያ ላለመሆን ይረዳል። ስለዚህ አገልጋይ ብቻውን ጎብኝት ባያደርግ ይመረጣል። ሁለት ሆኖ ጉብኝት ማድረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሕ አሳብ ነው (ሉቃ.10:1፤ የሐዋ.3:1፤8:12፤13:2፤14:40)። ይህን አሳብ ማብራራት የሚችል አንድ ምሳሌን እንመለከት።

★★★

በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የሚያገለግል በጣም የሚወደድ ገና ትዳር ያልመሠረት አገልጋይ ነበር። አንዲት አህት በቤተ እምነቱ ውስጥ ካሉት ከሌላ አጥቢያ ቤተክርስቲያን በሥራ ምክንያት ወደዚያ ትሄዳለች። ከነበረችበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ደብዳቤ ይዛ መጥታ ቤተክርስቲያን አሰገብታለች። የመጀመሪያውን ቀን አምልኮ ስትመጣ ከአገልጋዩ ጋር ተገናኝታ ደብዳቤውን ሰጥቸው። ከዚያም ሌላ ጊዜ አንደምትመጣ ነገረቸውና ተለያዩ። በቀጠሮው መሠረት ቢሮ መጣች። አሁንም በምትኖርበት አካባቢ አንግዳ አንደሆነችና የወንድሞች ጉብኝት አንደሚያስፈልጋት ነግራው ተለያዩ። አገልጋዩ እርስዋ ባለችበት አካባቢ ያሉት ወንደሞች አንዲጎበኙአት ነገራቸውና ወንድሞች ተራ በተራ ሄደው ይጎበኙአት ጀመር። ሆኖም አሁንም ቢሮ መጥታ አገልጋዩ አንዲጎበኛት ጠየቀችውና አንድ የምትነግረው ጉዳይ እንዳለም ጭምር ነግራው ሄደች። አገልጋዩ አርስዋ በለጠችው ቀጠሮ መሠረት ወደ ቤትዋ ብቻውን ሄደ። አርስዋም ተቀበለችውና የዶሮ ወጥ አቀረበችለት። የሚጠጣውን ደግሞ ብርዝ ስጠችው። አገልጋዩ በልቶ ጠጥቶ አመስግኖ ለመሄድ ሲዘጋጅ ከጎኑ ቁጭ አለችና ጥምጥም አድርጋ ይዛው መሳም ጀመረችው። አገልጋዩ ከተሰማው ስሜት የተነሳ ራሱን መቆጣጠር አልቻለም። ከዚያም በዝሙት ከአርስዋ ጋር ወደቀ። አንግዲህ ከዚህ ዓይነት አደጋ ለማምለጥ አገልጋይ ብቻውን ተቃራኒ ጾታን መጎብኘት አይገባውም።

በማማከር ወቀት ተገቢ አርምጃዎችን መውሰድ፦ አገልጋይ የማማከር አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት ከተቃራኒ ጾታ ጋር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት ላለማድረግ ጥንቃቄ ማድረግ ይችላል። አገልጋይ የማማከር አገልግሎት የሚሰጠው ቢሮው ውስጥ ከሆነ አርስን ሰዎች ከውጭ በመስኮት በኩል ሲያዩት በሚችሉበት ሁኔታ መቀመጥ ይችላል። ሆኖም ምክር ፈላጊው መታየት የለበትም። የክፍሱን በር መዝጋት ግን አለመቆለፍ፤ ለሰዎች ውጭ

ወይም በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ እንዲኖሩ ማድረግ፤ ተገቢውን ርቀት ጠብቆ መቀመጥ፤ ተገቢ ያልሆነ ለሳምታ አለመስጠት (ለምሳሌ ደረትና ደረትን የሚያነካካ) እና የመሳለሉትን መንገዶች መጠቀም ይቻላል። እነዚህ ውጫዊ የሆኑ ሁኔታዎች ከፈተናው ለመሸሽ ሊረዱ ቢችሉም ዋናው ግን ውስጣዊ ከሰላ ማድረግ መቻል ነው። ከውስጥ የተነሳውን ፍላጎት ውጫዊ ነገሮች ሊያግዱት አይችሉም። ሆኖም ማቆየት ይችላሉ። በቆይታ ውስጥ ደግሞ ራስን ለማየት ዕድል ሊገኝ ስለሚችል የማይናት ድርሻ ይኖራቸዋል።

በሙሞሪት ወቀት ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያለውን ግንኙነት መገደብ፦ አገልጋይ በራሱ ችግር ተወጥሮና ግራ ተጋብቶ ወይም ተስፋ ቆርጦ ባሰበት ሁኔታ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያለውን ግንኙነት በገደብ ቢያደርግ ይመረጣል። ከችግሩ ለትንሽ ጊዜ እፎይ ለማለት ብቻ ብሎ ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት እንዳያደርግ መሸሽ አማራጭ የለውም። በዚህ ጊዜ አገልጋይ ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት በመቀነስ በእግዚአብሔር ፊት በመሆን መጸለይ፤ ቃሉን መሞላትና የራስን ሕይወትና አገልግሎት መገምገም የበለጠ ይጠቅሟል። ከዚያም በአዲስ ኃይልና ራእይ መውጣት ይችላል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የመከላከያ እርምጃዎችን በመከተል አንድ አገልጋይ በወሲብ ኃጢአት ላለመውደቅ መከላከል ይችላል። ሆኖም በወሲብ ኃጢአት መውደቅ ቢያጋጥም ተስፋ ሳይቆርጡ እንደገና በእግዚአብሔር ፊት መቆም እጅግ አስፈላጊ ነው። አገልጋይ እንደ ማንኛውም አማኝ ይቅርታ ያገኘ ኃጢአተኛ እንዲሁም ያልተሻረ አዳማዊ ባሕርይ ያለው እንጂ የተሰየ መንፈሳዊ ፍጡር አይደለም። ስለዚህ ሊወድቅ ይችላል። ነገር ግን ከወደቀበት ቦታ ቶሎ በመነሳት ወደፊት ለመሄድ በእግዚአብሔር ላይ መታመን አማራጭ የሌለው መንገድ ነው። ቤተክርስቲያንም አንድ ጊዜ በተፈጸመ ኃጢአት በአገልጋይ ተስፋ ቆርጣ እንደማይጠቅም ዕቃ ልትቆጥረው አይገባትም። ነገር ግን እንደ አንድ ወንድም /እህት/ ተገቢውን እንከብካቤ መስጠት ይጠበቅባታል። መቼም ምንም ቢሆን ለሆች ለእርሱ የሚኖራቸው አመለካከት እንደ ቀድሞ ባይሆንም ከውድቀቱ መልካም ትምህርት ቢማር ለቤተክርስቲያን እጅግ ጠቃሚ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ይህ ግን በተዓምር ብቻ ሳይሆን አገልጋዩ የሚመለስና የሚታረም ልብ ሲኖረው እንዲሁም ቤተክርስቲያንም የሚቀበል መንፈስ ሲኖራት ነው።

እንግዲህ አገልጋይ ሕይወቱን፤ ቤተሰቡንና አገልግሎቱን በትልቅ አደጋ ላይ ሊጥል ከሚችለው ከወሲብ ፈተና ለመሸሽ ዘወትር ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያለውን ግንኙነት በገደብ ማድረግ አለበት። ከተቃራኒ ጾታ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ሚዛኑን ያልጠበቀ መሆኑን በውበጡ ከሚሰማው ስሜትና ከሌላው ወገን የሚታዩትን የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ማንበብ መቻል ይኖርበታል። በዚህ ፈተና ላለመውደቅ የራስን ኃላፊነት ከመወጣትም በተጨማሪ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ መደገፍ፤ መንፈሳዊ ሞግዚት ወይም ጓደኛ መያዝና ችግሩን ለአነርሱ ማካፈል ትልቅ እገዛ አለው። ባልታሰበ ሁኔታ በወሲብ ኃጢአት ውስጥ መውደቅ ቢያጋጥም የእግዚአብሔር ምሕረቱ ብዙ ስለሆነ ይቅርታ እንደሚኖር መረሳት የለበትም። ጠባሳውን ማበወገድ ባይቻልም ሕይወትን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ መኖር የሚቻልበት ዕድል ይኖራል። ከዚህ ውድቀት ለመፈወስ ግን ሂደቱ ረጅም ስለሆነ ከሆነ በኋላ ለማከም ጥረት ከማድረግ ይልቅ ከመሆኑ በፊት በመከላከሉ ላይ ትኩረት ማድረጉ የተሻለ ነው።

ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ።

1. *አገልጋይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ባለው ግንኙነት የሚገጥመውን ፈተና እንዴት ማስተናገድ አለበት? ቤተክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ዓይነት መመሪያ ሊኖራት ይገባታል?*
2. *አገልጋይ በዝሙት ኃጢአት ቢወድቅ ምን ማድረግ አለበት ብለህ ታስባለህ? ቤተክርስቲያንስ ምን ማድረግ ይጠበቅባታል?*
3. *አገልጋዮች ከተቃራኒ ጾታ ጋር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት እንዳያደርጉ ራሳቸውን እንዴት መርዳት ይችላሉ? ቤተክርስቲያንስ ምን ማድረግ ይገባታል?*

አንግዲህ በሕይወትና በአገልግሎት ፍሬያማ ለመሆን ከለዎች ሁሉ ጋር ወለኑን የጠበቀ መልካም ግንኙነት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ሁሉ አገልጋይ ያለውንም ጊዜ በአግባቡ በመጠቀም እግዚአብሔር እንዲሠራ ያቀደለትን ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል። አገልጋይ ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም የሚኖረው ጥቅም ምን እንደሆነ፣ ጊዜን በተገቢ መንገድ ለመጠቀም ተግዳሮት የሚሆኑ ነገሮችን፣ የጊዜ አጠቃቀም መርሆዎችንና ሌሎች የጊዜ አጠቃቀምን በተመለከተ ሊነሱ የሚችሉትን አሳቦች በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ በስፋት ይዳሰሳሉ።

ምዕራፍ 7

አገልግሎትና የጊዜ አጠቃቀም

በአብዛኛው በዚህ ዘመን ከአገልጋዮች አንደበት የሚሰማው «ጊዜ የለኝም» «አገልግሎት በዛብኝ» የሚል አባባል ነው። በእውነት በእሁኑ ዘመን ያሉ አገልጋዮች ከአገልግሎት ብዛት የተነሳ ጊዜ የላቸውምን? ይህ አባባላቸው ትክክል ነውን?

አንዳንድ አገልጋዮች ጊዜ የለንም የሚሉት እውነታቸውን አይደለም። ጊዜ የለኝም ማለት የተሰጣቸውን ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም አለመቻላቸውን ወይም ቢሠሩም ፍሬያማ መሆን አንዳቃታቸው የሚያሳይ መልዕክት አለው። ጊዜያቸውን በመበጀት የማይሠሩ አገልጋዮች ጊዜ ያጥራቸዋል። ምክንያቱም በየዕለቱ የሚሠሩት ነገር ሁሉ አገልግሎታቸው ይሆናል። የሚሠሩትንና መሥራት የሌለባቸውን ነገሮች ለይተው አያውቁም። ስለዚህ ጊዜ የማያገኙ ለዎች «ሥራ» የሌላቸው ወይም ሥራቸውን በዕቅድ የማይሠሩ ለዎች ናቸው። በዚህ ዘመን አገልጋዮች ከሌላው ዘመን የተለየ አገልግሎት እየሰጡ አይገኙም። የዓውድ ልዩነት ቢኖርም በቀድሞ ዘመናት የነበሩ አገልጋዮች ያገለገሉት ዓይነት አገልግሎት እየሰጡ ናቸው። ጊዜ የለኝም ወይም በአገልግሎት ተወጥራለሁ የሚሉት ጊዜአቸውን በሥርዓት መጠቀም ስላቃታቸው እንጂ በእርግጥ አገልግሎት ወጥሮአቸው ላይሆን ይችላል።

አገልጋዮች ጊዜ የሚያጡበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ለአገልግሎታቸው ወሰን ስለማያበጁ ነው። አገልጋዮች ለአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ተጠርተውና ተሰማርተው አያገለገሉ ግን እግዚአብሔር የጠራኝ ሁሉንም ቤተክርስቲያናት እንዳገለግል ነው በሚል አሳብ በመመራት አጥቢያ ወይም ቤተእምነት ዘለል አገልግሎት ይሰጣሉ። በተጠሩበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን የተሰጣቸውን ኃላፊነት በተገቢው መንገድ ሳይወጡ ክቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ያገለግላሉ። አንዳንዶች ይህን የሚያደርጉት እውቅናና ዝና ለማግኘት ወይም ከአጥቢያ ቤተክርስቲያን ኃላፊነት ለመሸሽ ወይም አልፎ አልፎ የትራንስፖርት ገንዘብ ለማግኘት ነው። አገልጋዮች የመጀመሪያ ተጠያቂነታቸው ለተጠሩበትና ለተሰማሩበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን መሆኑን ቢረዱና በዚያች አጥቢያ ያላቸውን አገልግሎት በተሳካ ሁኔታ ካከናወኑ በኋላ ባላቸው ትርፍ ጊዜ ለሌሎች በረከት እንዲሆን ያላቸውን ጸጋ ቢያካፍሉ ችግር የለውም። አለበለዚያ ግን «የሌላውን ለታማበል የራስዋ አረረ» እንደሚባለው ይሆናል።

ከልምድ እንደሚታየው ደግሞ አገልጋዮች በገጠርም ሆነ በከተማ የአስተዳደርን ሥራ ከሚሠሩ አገልጋዮች በስተቀር ሌሎች አገልጋዮች ቀን ባብዛኛው የሚሠሩት ሥራ የላቸውም። ቀን ተገልጋዮች ማለትም ምዕመናን በሥራ ላይ ስለሚውሉ አገልጋዮች ሚት ሰጋራ ጸሎት ቤተክርስቲያን ይሄዳሉ። ከዚያ በኋላ የቀረው ጊዜ የራሳቸው ነው። ጊዜያቸውን ለጸሎት፣ ቃሉን ለማጥናት፣ ለገሣጽና ለመሳሰሉት ነገሮች መጠቀም ይችላሉ። ይህን ደግሞ እቤታቸው ሆነው ወይም ቤተክርስቲያን ሆነው ማድረግ ይችላሉ። ሆኖም ግን ብዙ አገልጋዮች ቀን ጊዜያቸውን ፍሬያማ በሆነ መልኩ አየተጠቀሙበት እንደሆነ አይታይም። አገልጋዮች በአብዛኛው በአገልግሎት ላይ የሚሰማሩት ማታ ማታና ቅዳሜና አሁድ ነው።

እገልጋዮች ተገቢ የሆነ ሥራ በመሥራት እንጂ በእገልግሎት ሰም ብቻ ሥራ እየፈቱ ከቦታ ቦታ ወይም ከቤት ወደ ቤት እየዘሩ፣ በለምኝ ጉዳይ እየገቡ ወይም ለሰለምኞች እያወሩ፣ የፈጠራ ወሬ እያወሩ እንዲሁ ደመወዝ ከቤተክርስቲያን ወይም ከምዕመናን ማግኘት ጊዜን ከማባከንም በተጨማሪ ድርጊቱ በራሱ ከሥነምግባር የጎደለ ተግባር ነው (2ተሰ.3:11)።

የእግዚአብሔር ቃል ስለጊዜ የሚናገረው ብዙ ነገሮች አሉት። ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር ጊዜ መልካምና ቅዱስ እንደሆነ ያውቃል። ስለዚህም እግዚአብሔር የጊዜ ፈጣሪ ቢሆንም በጊዜ ተገዢውን ነገር ያደርጋል። እግዚአብሔር ፍጥረተ ዓለምን የፈጠረው በጊዜ በመጠቀም ነው። እግዚአብሔር ፍጥረተ ዓለምንና በአርቦዋ ውስጥ ያሉትን ሕይወት ያላቸውና የሌላቸውን ነገሮች ለመፍጠር ለድስት ቀን ፈጀበት። እነዚህ ለድስት ቀናት እያንዳንዳቸው 24 ለዓታት ያሉዋቸው ወይም አንድ ሺህ ዓመት መሆናቸውን ስሥነመለኮት ተመራማሪዎች በመተው እግዚአብሔር በተወሰነ ጊዜ ሥራውን ሠርቶ እንደጨረሰና በመጨረሻው ቀን ደግሞ እንዳረፈ እንመለከታለን። በእግዚአብሔር እሠራር ውስጥ ለሥራ/እገልግሎት/ እና ለዕረፍት ጊዜ እስው። ከፍጥረተ ዓለም መገኘት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ቅዱስ የተባለው ነገር ጊዜ ነው። እግዚአብሔር ከሥራው ያረፈበትን ቀን ቀደሰው።

ንጉሥ ለሎሞን «ለሁሉም ነገር ጊዜ አለው» (መክ.3:1) በማለት ለምኞ ጊዜያቸውን በዕቅድ እንዲጠቀሙበት ይመክራል። የጊዜ ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር ጊዜን በበላይነት ይቆጣጠራል። ነገሮች በቅደም ተከተላቸው መሠረት የጊዜው ባለቤት እንዳስቀመጣቸው ይፈጸማሉ። የለው ልጆች እግዚአብሔር በመደበላቸው ጊዜ መልካምም ሆነ ክፉ ነገር ማድረግ ይችላሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን ጊዜን ሊጠቀሙበት እንዳንዶች በተገቢው ወቅት ማድረግ የሚገባቸውን ሲያደርጉ ሌሎች ደግሞ ተገቢ ባልሆነ ጊዜ ተገቢ ያልሆነውን ነገር በማድረግ ከእግዚአብሔር አሳብ ጋር የሚለማማ ነገር ሳያደርጉ ያልፋሉ።

እንድን ነገር ለማድረግ ተገቢው ጊዜ መቼ ነው? እግዚአብሔር እንድ አገልጋይ እንድን ነገር እንዲያደርግ የሚፈልገው መቼ ነው? ይህን ተገቢ ጊዜ ለማወቅ ለዎች የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ። እግዚአብሔርን ያላመኑ ለዎች ኮከብ ቆጣሪዎች፣ ሞራ ገላጮች፣ ጠንቋዮችና የመሳለሉት ቤት ይሄዱና መቼ እንዲህና እንዲያ ላድረግ ብለው ይጠይቃሉ። የእግዚአብሔር ለዎች ግን እንድን ነገር ለማድረግ ትክክለኛ ጊዜው መሆኑን ከእግዚአብሔር ዘንድ ይጠይቃሉ። «የጠቢብ ልብ ጊዜን ያውቃል» (መክ.8:5)። ጠቢብ ለው መልካም ወይም ተገቢውን ጊዜ ያውቃል። እንድን ነገር መቼ ማድረግ እንደሚገባ በለሚረዳ እግዚአብሔር የለጠውን መልካም ዕድል ለእርሱ ክብርና ለለው ልጅ ጥቅም ይጠቀምበታል።

«ዘመኑ እጭር ሆኖአል» (1ቆሮ.7:29) ለለዚህ እያንዳንዱ ለው እግዚአብሔር በሕይወቱ ማከናወን የሚፈልገውን ነገር በማወቅ ጊዜውን መጠቀም ይጠበቅበታል። የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ያለን ጊዜ አጭር በመሆኑ የእርሱን ፈቃድ በማወቅ በዓለም ውስጥ ባለው ነገር ሳይጠላለፉ ዓላማ ያለው ሕይወት በመኖር ጊዜን መሻማት ይቻላል። ዓላማ ለሌለው ሕይወጥ ዓለም የለዎችን ዕድል ወይም ጊዜ ለማበላሸት ያዘጋጀችው

«ለድሎች» ብዙ ናቸው። ለለዚህ ባለችን ጥቂት ጊዜ ምን መሥራት እንዳለብን ከሥራው አለቃ ከእግዚአብሔር ለሕይወታችን ተቀብለን በዓላማ ቆራጥነት ተግባራዊ ለማድረግ ቀንና ሌሊት መትጋት ያለፈልገናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ «ዘመኑን ዋጁ» (ኤፌ.5:16) በማለት ምለመናችን ይመክራል። አገልጋይ እንደ ማንኛውም ለው እንዲሠራበትና እንዲጠቀምበት ዘየዕለቱ ተመሳሳይ ጊዜ ተሰጥተውታል። በጊዜ ለጥታ ለዎች አይበላለጡም። እያንዳንዱ ለው አኩል ለዓት ተሰጥተውታል። በለዎች መካከል ያለው ልዩነት ይህን የተሰጣቸውን ለዓት የሚጠቀሙበት ሁኔታ ነው። ጆን ለቶት «በእርግጥ ጥበበኞች ጊዜ ውድ ለታ እንደሆነ ያውቁታል። ሁላችንም ተመሳሳይ የጊዜ መጠን ተሰጥቶናል፣ በእንድ ለዓት ውስጥ 60 ደቂቃዎች እና በእያንዳንዱ ቀን ደግሞ 24 ለዓታት። ማናችንም ጊዜን ማራዘም እንችልም። ነገር ግን ጥበበኛ የሆኑ ለዎች በተቻለ መጠን በሚገባ ይጠቀሙበታል። እነዚህ ለዎች ጊዜ አላፊ እንደሆነ ያውቁታል»[10] በማለት ጽፈዋል። በዚህ አሳብ መሠረት በለዎች መካከል የሚኖረው ያላቸው ጊዜ ልዩነት ሳይሆን የጊዜ አጠቃቀማቸው ልዩነት እንደሆነ እንመለከታለን።

አገልጋይ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ፍሬያማ ለመሆን እግዚአብሔር የሰጠውን ጊዜ በተገቢው መንገድ መጠቀም ይጠበቅበታል። መቼም አገልጋይ በየዕለቱ የተያዙለት መደበኛ የሥራ ወይም አገልግሎት ጊዜያት የታወቁ ናቸው። እነዚህን መደበኛ የሥራ ጊዜያት ተዐማርቶ በሚያገለግልበት ቤተክርስቲያን ደንብ መሠረት ይጠቀምበታል። ነገር ግን የአገልግሎትንና ቤተሰብን ሚዛን ለመጠበቅ የሚረዳው አገልጋይ ከእነዚህ መደበኛ የሥራ ለዓታት ውጭ ያሉትን ጊዜያት የሚጠቀምበት ሁኔታ ነው። እንዳንዶች ጊዜውን እንደሚገባ ሲጠቀሙበት ሌሎች ደግሞ ጊዜያቸው ምንም ሳይጠቀሙበት እንዲሁ ያልፍባቸዋል። እንዳንድ አገልጋዮች ጊዜያቸውን በተገቢው መንገድ ለመጠቀም ችሎታ ሲኖራቸው እንዳንዶች ደግሞ ለተሰጣቸው ጊዜ ታማኞች ባለመሆን ጊዜያቸውን በከንቱ ያባክናሉ። የተሰጣቸው ችሎታ የተለያየ ቢሆንም እንደ እቅማቸው ጊዜያቸውን መጠቀም ይችላሉ። እግዚአብሔርም የሚጠይቃቸው በእቅማቸው የተሰጣቸውን ጊዜ ምን ያህል እንደተጠቀሙበት ነው።

አገልጋይ እግዚአብሔር የሰጠውን ጊዜ የእርሱን ሥራ በመሥራት ማሳለፍ ይገባል። ጊዜ ዕድል ነው። ይህ ዕድል ደግሞ ቆሞ አይጠብቅም። ጊዜ እንደ ወራጅ ውኃ ነው። አገልጋይ ያልተጠቀመበትን ጊዜ እንደገና አያገኝም። ጊዜን ባንክ ቤት ማስቀመጥ አይቻልም። ጊዜን ወደፊትም በማለተላለፍ ሌላ ጊዜ ሊመች መጠቀም አይቻልም። ጊዜን ለመጠቀም ጊዜው አሁን ነው። ለለዚህ እንደገና የማትገኘውን ጊዜ መልካም፣ ጠቃሚና እንደ እግዚአብሔር አሳብ የሆነ አገልግሎት በማገልገል ማሳለፍ ብድራት አለው።

ጌታ ኢየሱስ በጊዜ አጠቃቀም የአገልጋዮች ዋነኛው ምሳሌ ነው። ኢየሱስ እንደ እኛ በምድር ረጅም ዕድሜ አልኖረም። ነገር ግን የኖረበትን ጊዜ በሚገባ በመጠቀም በዓለም ታሪክ ውስጥ ወደርየለሽ ሥራ መሥራት

[10] Stott, John. *The Message of Ephesians*. Inter varsity Press, 1989, p.202

ችሏል። እርሱ ከልደት እስከ እርገቱ ድረስ ጊዜን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል አሳይታል (ዮሐ. 9:4፣ 17:4፣ 7:6፣ 12:23.27፣ 13:1፣ 17:1)

የጊዜ አጠቃቀም መርሆዎች

ጊዜን በሚገባ ለመጠቀም አንዳንድ መርሆዎችን ማወቅ ይጠቅማል። ከእነዚህም መርሆዎች መካከል የሚከተሉት አሳቦች ስለአገልጋይ ጠቃሚ ናቸው። ስለዚህ አያንዳንዱ አገልጋይ ከችግሩ አኳያ የሚሰማማውን መርሕ አሳብ በመቀበል ጊዜውን ፍሬ ሊያስገኝ በሚያስችለው በተሻለ ሁኔታ መጠቀም ይችላል።

1. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

እግዚአብሔር በዚህ ዓለም አማኞች በተሰይም በአገልጋዮች በኩል ሊፈጽም የሚፈልገው ሥራ አለው። ይህ እግዚአብሔር ልጆቹና አገልጋዮች እንዲሠሩት የሚፈልጋቸው ነገሮች በቃሉ ውስጥ ተጠቅሰዋል። በቃሉ ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ማድረግ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ሆኖም አንድ ሰው ሁሉን ነገር ማድረግ አይችልም። እግዚአብሔር በእያንዳንዱ አማኝና አገልጋይ መሥራት የሚፈልገው ነገር አለው። ስለዚህ «ለእኔ እንደ አገልጋይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድነው? አሁን ባለሁበት ሁኔታ እግዚአብሔር ምን እንዲሠራ ይፈልጋል?» የሚለውን ጥያቄ በመመለስ የእግዚአብሔርን አሳብ ማወቅ ይቻላል። ይህ አንድ አገልጋይ እንዲሠራው የተሰጠው አገልግሎት የሕይወት ዓላማው ይሆናል። አገልጋዩ መኖር የሚጀምረው ስዚህ እግዚአብሔር ላሳየው ዓላማ ይሆናል ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ለሕይወት አቅጣጫን ስለሚሰጥ ጊዜን በተገቢው ሁኔታ ለተገቢው ሥራ ማዋል ይቻላል። ከእግዚአብሔር የሕይወት አቅጣጫ ያገኘ አገልጋይ ያገኘውን ሥራ ከመሥራት ይልቅ እግዚአብሔር እንዲሠራ ያሰየውን ሥራ ይሠራል። እርሱ በየዕለቱ የሚሠራው ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ወዳሰየው ግብ የሚመራው ይሆናል። አገልግሎት የሚለጠው ከዓላማው አኳያ በማየት ነው። ከዓላማው ጋር ግንኙነት ለሌለው ሥራ ቅድሚያና ትኩረት አይሰጥም። ጊዜውን የሚጠቀመው እግዚአብሔር በልቡ ያስቀመጠውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ነው።

2. ራስን መግዛት

አንድ አገልጋይ ጊዜውን በሚገባ ለመጠቀም ቢፈልግ ራሱን ሥርዓት ባለው ሁኔታ መምራት መጀመር ይኖርበታል። አገልጋይ ጊዜን መቆጣጠር አይችልም። መቆጣጠር የሚችለው ራሱን ብቻ ነው። ጊዜ ስጦታ ስለሆነ አገልጋይ መቆጣጠር የሚችለው ጉዳይ አይደለም። ጊዜን መጨመር፣ መቀነስ፣ ወደፊት ማሳለፍ፣ ወደኋላ መመለስ ፈጽሞ የማይቻል ነው። ነገር ግን አሁን ያለችውን ጊዜ መጠቀም የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ይችላል። ይህም የሚሆነው ራስን በመግዛት በአስፈላጊ ወቅት አስፈላጊውን ነገር ለመሥራት በሚያስችል ሥርዓት ያለውን ሕይወት በመስማመድ ነው።

ጊዜን ፍሬያማ በሆነ መልክ ለመጠቀም ራስን ለሥርዓት በማስገዛት ራስን ማስልጠንን ይጠይቃል። ብዙዎች ጊዜና ችሎታ አያላቸው ራሳቸውን በመግዛት አንድ የተወሰነን ሥራ በጥሞና በተከታታይ መሥራት ባለመቻላቸው በአገልግሎታቸው የሚጠበቅባቸውን ያህል ስኬታማ ሳይሆኑ ቀርተዋል። በቅርብ ጊዜ አንድ በሀገራችን ደረጃ ጥሩ ትምህርት ያለው ሰው «አንተ አንዱት ነው አስካሁን አንድ የሚታይና ለትውልድ የሚተርፍ ሥራ ያልሠራኼው?» ተብሎ ሲጠየቅ «አግሮቼን ከወንበር ጋር ካለሠሩኝ በስተቀር አንድ ቦታ ለረጅም ጊዜ ተቀምጬ አንድን ነገር መሥራት አልችልም» በማለት መናገሩ ትዝ ይለኛል። ለአንድ ነገር ትኩረት ሰጥቶ ጊዜን በአንድ በተወሰነ ነገር ላይ ማዋል ራስን መግዛትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። በአገልግሎታቸው ዓላማ ያላቸውና ራሳቸውን በመግዛት ለዓላማቸው የተሰጡ አገልጋዮች ከሰዎች የላቀ ችሎታ ባይኖራቸውም ባላቸው ነገር ብዙ ሰዎችን እንዲሁም የሚቀጥለውንም ትውልድ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሥራዎችን መሥራት ይችላሉ።

3. ብድራት/ስኬት/ በአልግሎት ብዛት አለመሆኑን ማወቅ

በእግዚአብሔር መንግሥት አንድ አገልጋይ ብድራት የሚያገኘው ባገለገለው የጊዜ መጠን አይደለም (ማቴ.20:1-16)። እግዚአብሔር ከጧት እስከ ማታ ድረስ በአገልግሎት መጠመድን ሳይሆን እርሱ እንዲሠራ የሚፈልገውን ሥራ መሥራትና የተሠራው ሥራ ጥራት ያለው መሆኑን ነው። የእግዚአብሔር ትኩረት ለሥራው የዋለው ጊዜ ላይ ሳይሆን የእርሱ አሳብ መከናወኑ ላይ ነው።

በአገልግሎት ስኬታማ ለመሆን በትጋት መሥራት አስፈላጊ ነው። ያለትጋት ስኬት አይገኝም። ዳተኛና ታካች ሰው ስኬታማ መሆን አይችልም። ሆኖም ግን አንደ ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ ትጋት ወይም ትጉህ ሠራተኛ መሆን ለብቻው ወደ ስኬት አያደርስም። ስኬት በእግዚአብሔርና በሰው የጋራ ሥራ ይገኛል። አገልጋይ የራሱን ድርሻ ሲያከናውን እግዚአብሔርም የራሱን ድርሻ ያበረክታል። አገልጋይ ሰው ማድረግ የሚገባውን ነገር ያደርጋል። አገልጋይ ዘሩን ይዘራል፣ እግዚአብሔር ያበቅላል፣ አገልጋይ ይኮተኩታል እንዲሁም ውኃ ያጠጣል፣ እግዚአብሔር ያለድጋል እንዲሁም ፍሬ እንዲያፈራ ያደርጋል። ሁለቱም በጋራ በመሥራት መልካም ፍሬ ያገኛሉ (1ቆሮ.3:5-9)። አገልጋይ በትጋት ላይሠራ እንዲሁም እግዚአብሔር ላይባርከው ስኬትን አያገኝም (ምሳ.23:4፣ መክ.11:6)። እግዚአብሔር ግን የሚባርከው በትጋት የሚሠራውን አገልጋይ ነው።

4. ከመጠን በላይ በሥራ አለመጠመድ

መሥራት የሚገባቸውን ነገሮች የማይሠሩ አገልጋዮች አንዳሱ ከመጠን በላይ በአልግሎት ተጠምዶ ለሌላ ነገር እንዲሁም ስቤተሰቦቻቸው ጊዜ የሌላቸው አገልጋዮች ሞልተዋል። ብዙ አገልጋዮች በሳምንት አንድ ሠራተኛ መሥራት ከሚገባው አርባ ስዓት በላይ ይሠራሉ። አገልጋዮች በአገልግሎት የሚጠመዱባቸው ምክንያቶች የተለያዩ ናቸው። አንዳንዶቹ ምክንያቶች ከራሳቸው ከአገልጋዮቹ የሚመነጩ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ከውጭ ተጽዕኖ የሚመጡ ናቸው። አነርሱም፦

የብቃት ማነስ ስሜት፡- በአገልግሎት የሚጠመዱ አገልጋዮች በራስ የመተማመን መንፈሳቸው አናሳ ነው። በውስጣቸው አገልግሎትን በሚገባ ያገለገሉ ስለማይመስላቸው የብቃት ማነስ ስሜት ይሰማቸዋል። ይህን የብቃት ማነስ ስሜታቸውን ለማስወገድ ደግሞ ሌሊትና ቀን ሲሠሩ ይታያሉ። ሰራሳቸው ዕረፍትን በመንፈግና በሥራ በመጠመድ የአገልግሎት ብቃት ማነሳቸውን ለማካካስ ጥረት ያደርጋሉ።

ፍርሃት፡- አገልጋዮች ከፍርሃት የተነሳ በአገልግሎት ይጠመዳሉ። አንዳንዶች ዕድሜያቸው እያረጀ ሲሄድ ከዚህ ዓለም ወደ ዘላለም ዕረፍት የሚሄዱበት ጊዜ ቅርብ ሆኖ ይታያቸውና ከመሄዳቸው በፊት መሥራት የሚገባቸውን ሥራ ቶሎ ሠርተው ለመሄድ ይተጋሉ። ጊዜውን በደንብ ይሸማሉ። እነዚህ ሰዎች ሥራ የሚያቆሙበት የመጨረሻ ቀጠሮ እንደተቀጠረለት ሰው በትጋት ይሠራሉ። በትምህርት ቤት ውስጥ የቤት ሥራ ተሰጥቶ ቶሎ ቶሎ ሠርቶ በጊዜው ለማድረስ እንደሚደረገው ዓይነት ሩጫ ያደርጋሉ። ይህን የሚያደርጉት ከዕቅድ አኳያ ሥራዎችን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በመሥራት ሳይሆን የተገኘውን ሥራ መሥራት ጊዜያቸውን አገልግሎት ብለው በሚያስቡት ላይ በማሳለፍ ነው። የሚነዳቸው የውስጣቸው የሞት ፍርሃት እንጂ ከሥራው የሚገኘው ውጤት ወይም እርካታ አይደለም።

አንዳንድ አገልጋዮች ደግሞ የአገልግሎት አለመሳካትን በመፍራት በሥራ ይጠመዳሉ። በቤተክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎት በአብዛኛው በተጨባጭ ሁኔታ መሰካት ወይም መገምገም አዳጋች ነው። ስለዚህ አገልጋዮች አገልግሎታቸው ውጤታማ መሆኑንና አለመሆኑን በእርግጠኝነት ማወቅ ያስቸግራቸዋል። ምናልባት በአገልግሎታቸው ወድቀው እንዳይገኙ በሚል ሰጋት አብዛኛውን ጊዜያቸውን በአገልግሎት ላይ ያውላሉ።

ብቻቸውን መሆን በመፍራት በአገልግሎት የሚጠመዱ እንዳሉ እንዲሁ ከሌሎች ሰዎች በተለይም ከቤተሰብ ሰመሸሽ አገልግሎት የሚያበዙ አገልጋዮችም ይገኛሉ። ለብቻ መሆን በመፍራት ሰዎች ያሉበትን ሁኔታዎች ይፈልጋሉ። በቤተክርስቲያን ያለው አገልግሎት በአብዛኛው ከሰዎች ጋር የሚያገናኝ ስለሆነ በአገልግሎት መወጠር ከችግሩ የማምለጫ አንዱ መንገድ ነው። በቤተሰብ ውስጥ ችግር ያላቸው ሰዎችም ከችግሩ ሰመሸሽ አገልግሎት የማስተባበያ ምክንያት ይሆንላቸዋል። ሰቤተሰብ «አገልግሎት አለኝ» ብለው ይወጣሉ። ቆይተው ሲመጡ ሰምን አይባሉም ወይም ከተባሉም «አገልግሎት ላይ ቆይቼ ነው» የሚል ምላሽ ይሰጣሉ። የእግዚአብሔርን ሥራ በትጋት እየሠሩ እንደሆነ ስለሚታሰብ ማንም አይጠይቃቸውም። ቤተሰብ ቢጠይቅም እንደተሳሳተ የሚታሰበው አገልጋዮቹ ሳይሆኑ የሚጠይቁአቸው ቤተሰቦቻቸው ናቸው።

ምሥጋና ለማግኘት፡- በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚሠሩት ሥራ በሌሎች ሰዎች ዘንድ ምሥጋና ለማግኘት በሥራ የሚጠመዱ አገልጋዮች ዘወትር በመትጋት አገልግሎታቸው ከሌሎች ተሽሎ እንዲታይ ይፈልጋሉ። በውስጣቸው ከሌሎች ሰዎች ጋር ይፎካከራሉ። «ከአገሉ እንሹ እንዳልገኝ» በሚል ምክንያት ሌሎች ማድረግ የሚገቡአቸውን ነገሮች በመተው በአገልግሎት ይጠመዳሉ። አንዳንዶች ደግሞ «ጎሽ ጥሩ ሠርተሃል!» የሚሰውን አድናቆት ለማግኘትም ብለው ሌሊትና ቀን ይሠራሉ።

የሥራው ፭ባይ፡- በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው አገልግሎት/ሥራ/ ብዙ ጊዜን የሚጠይቅ ነው። ሥራዎቹ ብዙ ናቸው። አገልጋዮች እንዲሠሩ የሚጠበቁባቸው የተጻፉና ያልተጻፉ የሥራ ድርሻዎች አሉ። አገልጋዮች በጽሁፍ የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ ብቻ ሳይሆን እንዲሁ አገልጋዮች መሥራት አለባቸው ተብለው የሚጠበቁትንም ሥራዎች መሥራት ይጠበቅባቸዋል። አገልጋዮች እንደምንም በጽሑፍ የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻቸውን ቢጨርሱም የሚጠበቅባቸውንም መሥራት አለባቸው። ስዚህ ደግሞ መሥራት ከሚገባቸው ጊዜ በላይ መሥራት የግድ ይሆንባቸዋል። መቼም ቢሆን ሥራ ተሠርቶ አያልቅም።

አገልጋዮች ከመጠን በላይ በአገልግሎት ሲጠመዱ በሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖራል። ያለምንም አረፍት በአገልግሎት የሚጠመዱ አገልጋዮች አገልግሎታቸውን ሲያበላሹ የሚችሉ ሰህተቶችን ሰመሥራት የተጋለጡ ናቸው። የላቀ ሥራ በአገልግሎት ተወጥሮ ከደከመ ሰው አይጠበቅም። መልካም አገልግሎት ለመስጠት ከውጥረት ነጻ መሆንን ይጠይቃል። አገልጋዮች በሥራ ሲወጠሩ የማሰብና አዲስ ነገርን የማፍለቅ ችሎታቸው ይቀንሳል። የተሰመደውን የዕለት ሥራዎችን በድካም ስሜት ውስጥ ሆኖ ከመሥራት ያለፈ አዲስ ራእይን ማፍለቅ ይሳናቸዋል። በሕይወታቸውም ይዝላሉ። አካሳዊና መንፈሳዊ ሕይወታቸው ይደክማል። ይህ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ሰዎች ጋር በተሰይም ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት የሠመረ አይሆንም። ምክንያቱም የአገልግሎት ውጥረቱ ነጭናጫና ቁጡ ያደርጋቸዋል። ቀድሞ ያልነበራቸውን መጥፎ ባሕርያትን ያላድጋሉ። ከዚህም የተነሳ ሰዎች ሲቀርቡአቸው ይቸገራሉ።

እነዚህ ከውስጥ የሚነሱ ምክንያቶች በአገልግሎት ላይ ሰመጠመድ ምክንያት በሚሆኑበት ወቅት አገልጋዮች መፍትሔ መፈለግ ያዋጣቸዋል። መፍትሔ ሊሆኑ ከሚችሉ ነገሮች አንዱ ቆም ብሰው በአገልግሎት እንዲጠመዱ ያደረጋቸው መሠረታዊ ምክንያት ምን እንደሆነ መሰየት ነው። ይህ መሠረታዊ መንስኤ ፍርሃት ከሆነ እግዚአብሔር እንዲያሰወግደው በመጸለይና አስፈላጊውን የማማከር አገልግሎት በማግኘት መቋቋም ወይም ማስወገድ ይችላል።

5. ሥራዎችን ለመሥራት ቀጠሮ አለመስጠት

ጊዜን ወደፊት ሰመጠቀም ማስቀመጥ አንደማይቻል ተመልክተናል። ላሬ መሠራት የሚገባው ሥራ ሰወደፊት ቀጠሮ ሲሰጠው እያንዳንዱ ዕለት የራሱ የሆነ አጀንዳ ይዞ ስለሚመጣ ከሌላ ቀን ተሳልፎ የመጣውን ሥራ መሥራት አስቸጋሪ ይሆናል። ሰምሳሌ ያህል አንድ አገልጋይ አሁድ የሚሰብከውን ሰብክት ከሰኞ ጀምሮ ማዘጋጀት ከመጀመር ይልቅ እስከ ቅዳሜ ምሽት መቆየት ጤናማ አይደለም። ሥራዎች በወቅቱ ሲሠሩ ውጤታማ ይሆናሉ።

አገልጋዮች ሰሥራ ቀጠሮ ሳይሰጡ አንዴት መሥራት አንዳለባቸው ከመመልከታችን በፊት አገልጋዮች ሰምን ለሥራ ቀጠሮ አንደሚሰጡ መመልከቱ የተሻለ ይሆናል። ከዚህም አኳያ አገልጋዮች በወቅቱ መሥራት የሚገባቸውን ሥራ ወደፊት የሚያስተላልፉበት ምክንያቶች ጥቂቶቹ፡-

- ✓ ለሥራው ትኩረት ወይም ከብደት እለመስጠት ወይም ሥራው ቶሎ እንዲሠራ የሚያስገድድ ሁኔታ አለመኖር ነው።
- ✓ ሥራው መሠራት የሚገባው ነገር ሆኖ እያለ ሥራውን መርሳት - እገልጋዮች መሥራት የሚገባቸውን ሥራ የሚረሱት ከሆነ ከሥራው ጋር የተያያዘ የሆነ ችግር መኖሩን ያመለክታል። እንዳንድ የሥነልቦና ባለሙያዎች ለዎች አንድን ነገር የሚረሱት ነገሩ ለእነርሱ አርካታ ወይም ደስታ ስለማይሰጣቸው እንደሆነ ይናገራሉ። በዚህ መሠረት አገልጋዮች የተሰጣቸውን ሥራ የሚረሱት ሥራውን ስለማይወዱት ወይም ሥራውን በመሥራት የሚያገኙት መልካም ነገር እንደሌለ በመገመት ይሆናል።
- ✓ ሥራው ከባድና አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ቶሎ ከመጀመር ይልቅ ያቆዩታል። ሥራውን ከመፍራት የተነሳ መሥራት እንዳለባቸው እያወቁ ግን ሳይሠሩ ይቆያሉ።
- ✓ በሁለት እሳብ መወጠር ማለትም ሥራውን ልሥራው ወይስ ልተወው የሚል የሚያመነታ ልብ ካላቸው ሥራውን በጊዜው አይጀምሩትም። ሥራን በወቅቱ ለመሥራት ውሳኔ ማድረግን ይጠይቃል።

እነዚህና ሌሎች ምክንያቶች በሚኖሩበት ወቅት ሥራዎችን እንዴት በወቅቱ መሥራት ይቻላል? ተገቢውን ሥራ በተገቢው ወቅት ለመሥራት የሚረዱ እንዳንድ ጠቃሚ አሳቦች እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል። እነርሱም:-

☞ የሥራውን አስፈላጊነት አስቀድሞ ማወቅ መልካም ነው። ይህም የሚቻለው ስለሥራው በቂ መረጃ በመሰብሰብ ነው። የሥራው አስፈላጊነት ከታመነበት በኋላ ተገቢውን ውሳኔ ወዲያውኑ መወሰን ያስፈልጋል።

☞ በጸጥታ መንፈስ ውስጥ ሆኖ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጸሎት መፈለግና ማወቅ ሥራው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥያቄ ቶሎ ለመመለስ ይረዳል። የእግዚአብሔርን እሳብ ደግሞ ልብን ከፍቶ ማዳመጥ ያስፈልጋል። ከዚያ በኋላ ሥራውን በሙሉ ኃይል መሥራት ይቻላል።

☞ ሥራው እንዲረሳ የሚያደርግ ወይም እንዳይሠራ የሚያደርግ የተሰወረ ዓላማ ካለ መፈተሽ አስፈላጊ ነው። እገልጋይ ሥራውን ቶሎ መሥራት የማልፈለገው ለምንድነው? ብሎ ራሱን በመጠየቅ ትክክለኛውን ምላሽ ሊያገኝ ይገባል።

☞ የሥራው ጥራት ማጣትን በጊዜ እጥረት ለማስተባበል ብሎ ሥራውን እስከ መጨረሻው ወቅት ማቆየት መልካም እለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። እንዳንድ ስዎች የተሰጣቸውን ሥራ በሚገባ እንደማይሠሩት ሲገባቸው ሥራውን ሆን ብለው ያቆዩትና ጥቂት ጊዜ ሲቀራቸው ይሠሩና ሥራቸው ጥራቱ የጎደለው ሆነው ሲጠየቁ ቶሎ ቶሎ ስለተሠራ ነው ይላሉ። ይህ ደካማ የሆነ እካሄድ ስለሆነ ሲታረም ይገባል። ሥራውን መሥራት ካልቻሉ መሥራት ለሚችል ለው መስጠት ያስፈልጋል። ጊዜንም ለመጠቀምና ጥራት ያለው ሥራም እንዲሠራ ያደርጋል።

☞ አንድን ሥራ በአንድ ጊዜ ሠርቶ ለመጨረስ ከማሰብ ይልቅ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ጥቂት በጥቂቱ መሥራት የተሻለ ነው። የሚፈለገው ሥራ ብዙ ሳያስጨንቅ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል።

6. ጊዜን ከነጣቂዎች መዋጀት

ጊዜን በሚገባ ለመጠቀም ጊዜን ሲያባክኑ ከሚችሉ ነገሮች መቆጠብ ያስፈልጋል። ጆን ካልቪን «ጊዜው የተበላሸ በመሆኑና ዲያብሎስም ስለሚዋጋ ጊዜን ላይዋጁ ለእግዚአብሔር መስጠት አይቻልም። ጊዜን ለመዋጀት ደግሞ ዋጋው ምንድነው? ብለው በመጠየቅ ጊዜ ለእግዚአብሔር እንዳይዋጅ እንቅፋት ከሚሆኑ ከማናቸውም ፈተናዎች መራቅ፣ ራሳችንን ዓለም ለምትለጠው ምኞት አለመስጠትና በእጭር ንግግር ማንኛውንም መሰናክል ማውገዝ ነው» በማለት ምዕመናን ጊዜያቸውን ለእግዚአብሔር ክብር እንዲጠቀሙበት ይመክራቸዋል።[11] በዚህ ዘመን ዲያብሎስ የአገልጋዮችን ጊዜ እንደ ልቡ እየተጠቀመበት ይገኛል። እገልጋዮች ለእግዚአብሔር ሥራ የተቀጣጠለ ልብ እንዳይኖራቸው ስልቾዎች እንዲሆኑ ስማድረግ እንዲሁም ከአርስ በርሳቸውና ከዜተክርስቲያን መሪዎች ጋር እንዳይስማሙና አንዱ ስሰሌላው ከፋት እያወራ እግዚአብሔር የስጣቸውን ጊዜ እንዲያባክኑ እያደረጋቸው ነው። ስለዚህ የከፋውን ዓላማ ባለመዘንጋት በጸሎት እየተዋጉ ጊዜን ለእግዚአብሔር በጎ ሥራ ላይ ማዋል ትልቅ ብድራት ይኖሯል።

7. እምቢ ማለትን መማር

አገልጋይ እላስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለመሥራት ፈቃደኛ ባለመሆን ጊዜውን ለመልካም ነገሮች ላይ ማዋል ይችላል። እገልጋይ ለአንዳንድ እገልግሎቶች ለምንና እንዴት አምቢ ማለት እንዳለበት ከመመልከታችን በፊት እምቢ ማለት ምን እንደሆነና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እሳብ መሆኑን በማየት እንጀምራለን።

እምቢ ማለት ለአገልግሎት ወሰን ወይም ገደብ ማበጀት ማለት ነው። በምድራችን ላይ የብስና የውኃ አካለት ወሰን አላቸው። ሀገራት የየራሳቸው ወሰን አላቸው። በድንበር ይገባኛል ጥያቄ ብዙ ጦርነቶች ተደርገዋል። አንዱ የሌላውን ወሰን ጠብቆ ሲኖር በሀገራት መካከል ሰላም ይኖራል። ለመልካም ጉርብትናና ግንኙነት ወሰንን ማክበር አስፈላጊ ነው። በሕይወት ውስጥም ወሰን አስፈላጊ ነው። እንድ ለው መሆንና መሆን የማይችለውን እንዲሁም ማድረግ የሚችለውንና የማይችለውን ነገር ለይቶ ማወቅ የራሱን ገደብ ወይም ወሰን እንዲያውቅ ያግዟል። እገልጋይ በአገልግሎቱ ከየት እስከ የት መሄድ እንደሚችል ሲያውቅና ያን ገደብ ሲያከብር ብዙ ይጠቀማል።

እምቢ ማለት ወይም ለአገልግሎት ወሰን ማበጀት አስፈላጊ የሆነበትን እንዳንድ ነጥቦችን መጥቀስ ይቻላል። አነርሱም:-

- እገልጋይ ላይባክን አገልግሎት መስጠት ይችላል። የራሱን ጸጋና ኃይሉን በመጠበቅ ማገልግል ይችላል። በአንድ ጊዜ ውልቅልቁ ላይወጣ በሕይወት ዘመኑ አገልግሎቱን ይሰጣል።

---

[11] Parker, T.HL. *Calvin's Commentaries*. Grand Rapids, MI: Wm.B. Eerdmans Publishing Company, 1965, p. 202-203.

- በቅድሚያ ምን መሥራት እንዳለበት ስለሚያውቅ ጊዜውን በሚገባ መጠቀም ይችላል። ጠቃሚ የሚመስሉትን ነገሮች ወደ ጎን በመተው የተጠራበትንና ለእርሱ የተሰጠውን ሥራ ለመሥራት ጊዜውን ስለሚጠቀምበት የጊዜ እጥረት የለውም። የሚያደርገውንም ነገር በዕቅድ ያደርጋል።
- አገልጋዩ ጸጋውና ችሎታውን በአንድ ተግባር ላይ ስለሚያውል ስኬታማነት ያገኛል። የእርሱ የሆኑትንና ያልሆኑትን ለይቶ ያውቃቸዋል። የእርሱ የሆኑትን ነገሮች በሚገባ ይሠራል። ትኩረቱንና ኃይሉን ለሌሎች ነገሮች ስለማይለጥ ውጤታማ ይሆናል።
- አገልጋዩ የራሱን ስለሚያውቅና የሌሎችን ሥራ ስለማይሠራ ከሌሎች አገልጋዮች ጋር አይጋጭም። አገልግሎትን ሁሉ እጠቃልሎ ለመያዝና የአገልግሎት ሁሉ ባለቤት ለመሆን ጥረት አያደርግም። አገልጋዮች በጸጋቸውና በችሎታቸው እንዲያገለግሉ ዕድል ይሰጣቸዋል፣ አገልግሎታቸውንም ያከብራል። የእርሱ አገልግሎት ከሚያስፈልጉ አገልግሎቶች ውስጥ አንዱ እንደሆነ እንጂ ያለእርሱ አገልግሎት እንደሌለ አያስብም። በዚህም ከአገልጋዮች ጋር መልካም ግንኙነትን ያፈራል።

እምቢ እለማለት የሚያስከትለው ችግር ምንድነው? አገልጋይ የሚያገለግለው ሕዝብ ከእርሱ የሚጠብቀውን ሁሉ መፈጸም አይችልም። ሕዝቡ ከእርሱ የሚፈልገውን ነገር ማወቁ በአገልግሎቱ በምን ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባው ስለሚያሳየው ጠቃሚነት አለው። ሆኖም ሕዝቡ ከእርሱ የሚጠብቀውን ሁሉ ለማድረግ ጥረት ማድረግ ራሱን እለማወቅ ነው። በዚህ መንገድ ከቀጠለ ይህ እንደማይቻል ይረዳና «እኔ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከእኔ የሚፈልገውን ማድረግ የማልችል ከሚጠበቀው ደረጃ በታች ዝቅ ብዬ የምኖር አገልጋይ ነኝ» ብሎ ራሱን እንዲገምት ያደርጓል። ይህ ደግሞ የሕሊና ወቀሳ ከዚያም የበታችነት ስሜት እንዲለማው ያደርጋል።

ስለዚህ አገልጋይ ማድረግ ለማይችለው ነገር ራሱን ላለመለጠት እስቀድሞ ለራሱ እምቢ ማለትን መማር ይኖርበታል። «እኔ ይህን ማድረግ አልችልም ወይም የለብኝም» ማለትን መለማመድ ይገባዋል። ከዚያም በመሠረተ አሳብ ደረጃ ማድረግ የማይገባውንም ሆነ በወቅቱ ማድረግ ለማይችለው ተግባር ምንም የሕሊና ወቀሳ ላይሰማው እምቢ ማለት ይችላል።

አገልጋይ አንድን ተግባር ለመፈጸም እምቢ የሚለው የራሱን ምቾት ለመጠበቅ ብቻ መሆን የለበትም፣ አገልጋይ እምቢ ሊል እምቢ ላለበት ነገር በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂነት እንዳለበት በማወቅ ሊሆን ይገባል። ስለዚህ ለአንድ አገልግሎት ወይም ተግባር እምቢ ለማለት የሚረዱ መመዘኛዎች ሊኖሩ ይገባቸዋል። ከእነዚህም መመዘኛዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም፦

- አገልግሎቱ ከእርሱ አቅምና ችሎታ በላይ እንደሆነ ሊገባው
- እርሱ ማድረግ የሚችለው ነገር ግን እርሱ ባለበት የአገልግሎት ሁኔታ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር እንዳልሆነ ያረጋገጠ ሲሆን

- ተግባሩ እንዲፈጸም የሚያደርጉ አጣዳፊ የሆኑ እካባቢያዊ ሁኔታዎች አለመኖራቸው
- ሌሎች ይህን ሥራ በተሻለ ሁኔታ መሥራት የሚችሉ ብቃት ያላቸው አገልጋዮች ሲኖሩ

እንግዲህ አገልጋይ ለሁሉም ነገር እሺ የሚል ሰው መሆን የለበትም። አገልጋይ «ባሪያ» ቢሆንም ባሪያ የሆነው ለጠራው ጌታ ለእግዚአብሔር እንጂ የሚያገለግላቸውን ምዕመናን ፍላጎትና ምኞት ለማሟላት አይደለም። አገልጋይ እንደ ጌታ ባሪያ እግዚአብሔር ለሚያዘው ነገር ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እሺ ማለት ሊጠበቅበት ከለዎች ለሚመጣበት ትዕዛዝና የአገልግሎት ጥያቄ ግን ለየትኛው እሺና ለየትኛው ደግሞ እምቢ ማለት እንዳለበት መለየት እጅግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ አኳያ እንድ አገልጋይ በቢተክርስቲያን በሚደረገ በሁሉም አገልግሎቶች ላይ መገኘ ት አይኖርበትም። አገልጋይ በሁሉም የሠርግ ሥርዓቶች ወይም ለቅሶዎች ላይ መገኘቱ የሚጠበቅ ከሆነ ለሌሎችም እገልግሎቶች ጊዜ አይበቃውም። እንድ አገልጋይ ዘወትር ለባኪ ሆኖ በየእሁዱ ወይም በተለያዩ የሰብክት እገልግሎቶች ላይ መቆም የለበትም። ለሌሎች በማካፈል ሌሎችን ማስተፍ ለእርሱም ሆነ ለአገልግሎቱ ለሚሳተፉ ሰዎች ይጠቅማል።

አገልጋይ ከሚያገለግልበት መደበኛ አገልግሎት ውጭ የሚመጡለትን የአገልግሎት ጥያቄዎች ከመቀበሉ በፊት ያለውን ጊዜ ለሚገባ ማጤን ይኖርበታል። አገልጋይ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ አባል ሆኖ መመረጥ የለበትም። በእነዚህ ሁኔታዎች ላይ ቁጥጥር ማድረግ ከቻለ ጊዜውን ማዳን ይችላል። አገልጋይ በግሉ ሁሉንም አገልግሎት ማገልገል አይችልም። ነገር ግን የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠት የሚችሉትን ሰዎች በማፍራት ማለማራት ይኖርበታል። የአንድ አገልጋይ ዋና ተልዕኮውም ሌሎች ምዕመናን ለአገልግሎት እንዲበቁ ማስታጠቅ ነው (ኤፌ.4:11-17)።

ፀ. ቅድሚያ ለምን እንደሚሰጥ ማወቅ

አገልጋይ ሁሉን ነገር ለመሥራት ቢያስብ የሚፈልገውን ሁሉ መሥራት አይችልም። ምክንያቱም በመጀመሪያ አገልጋይ በልቡ ያለውን ሥራ ሁሉ ለመሥራት የሚያስችለው ችሎታ ወይም ጸጋ ላይኖረው ስለሚችል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አገለጋይ ለሁሉም ዓይነት ሥራዎች የሚበቃ ጊዜ ስለማይኖረው ነው። ስለዚህ የትኞቹን ሥራዎች ቅድሚያ ለጥቶ መሥራት እንዳለበት በተገቢው ሁኔታ መለየት ይኖርበታል። አገልጋይ በጊዜ አጠቃቀም የሚችገረው በአብዛኛው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ቅድሚያ የሚሰጠው ሥራ ምን እንደሆነ በግልጽ ሰይቶ አለማወቅ ነው። በአገልግሎት መስክ ላይ ስለሚገኝ ሁሉንም መንፈሳዊ የሆነውን ሥራ መሥራት የሚጠበቀው ስሚመስለው አገልጋይ ጊዜ አይበቃውም። በሕይወቱ ምን መሥራት እንዳለበት ስሚያውቅ አገልጋይ ግን ከተለያዩ አገልግሎቶች በምን ላይ ትኩረት ማድረግና ምንን ከምን ማሰቀደም እንደሚገባው ስለሚያውቅ ጊዜውን ለዚያ ዓላማ ከግብ መድረስ ይጠቀማል።

አገልጋይ ለሚሠራቸው ሥራዎች እንደ አስፈላጊነታቸው ቅድሚያ መሰጠት ይገባዋል። በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ ቅድሚያ መስጠት

ያለበት ለምን ዓይነት ሥራ ነው። ለትምህርት ዝግጅት፣ ለጉብኝት፣ ለማማከር፣ ለጸሎት፣ ለአስተዳደራዊ ሥራዎች ወይስ ለምንድነው? አገልጋይ ከእነዚህ ሥራዎች ቅድሚያ ለጥቶ ለመሥራት በራሱ መወሰን ይችላልን? አገልጋይ ከመሪዎች የተሰጡትን ሥራዎች የሚተገብር ነው ወይስ በራሱ ቅድሚያ ሊሰጡ የሚገባቸውን ነገሮች መርጦ መሥራት ይችላል? አገልጋይ እንዲሠራቸው የተሰጡት ሥራዎች ቅደም ተከተል አላቸውን? የቤተክርስቲያን መሪዎችና ምዕመናን አገልጋይ ከሁሉም በላይ መሥራት አለበት ብለው የሚያስቡት ሥራ ምንድነው? አገልጋዩ ራሱስ ምን በቅድሚያ መሥራት እንደሚገባው ያስባል? ለአንድ ሥራ ቅድሚያ ለመስጠት እነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ሊያገኙ ይገባቸዋል።

አገልጋዮች በተጠሩበትና በተሠማሩበት አገልግሎት በኬታማ የሚሆኑት በአገልግሎቱ የሚጠበቅባቸውን ቀዳሚ ሥራ በቅድሚያ መሥራት ሊችሉ ነው። ለምሳሌ ከመጋቢው የሚጠበቀው ለምዕመናን ተመጣጣኝ የሆነ መንፈሳዊ ትምህርት አዘጋጅቶ ማስተማርና ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዋህዱ በግልም ከእነርሱ ጋር መነጋገር፣ መጸለይና ወደ እግዚአብሔር ፍጹም አሳብ እንዲያድጉ ማገዝ ቢሆንና መጋቢው ግን አገልግሎቴ ነው ብሎ የያዘው ፕሮግራም ማውጣትና አገልጋዮችን አየጋበዘ መመደብ፣ ስብሰባዎችን ማካሄድና መካፈል፣... ከሆነ የሚጠበቅበትን አገልግሎት አገልግለዋል ለማለት አዳጋች ነው።

አንድ አገልጋይ ለየትኛው አገልግሎት ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባው ካለወቀና ካላደረገ ጊዜውን እንዲሁ ያባክናል። አገልግሎትን ይሰጣል ነገር ግን የሚሰጠው አገልግሎት እርሱ ከፍተኛ ትኩረት ሊያደርግበት የሚገባ ላይሆን ይቀራል። ሰዎች ከእርሱ የሚጠብቁትንና የአገልግሎት ሥፍራው ከእርሱ የሚፈልገውን ነገር ሳያከናውን ሌሎች ነገሮችን ሊሠራ ይከርምና ውጤቱን መገምገም ሲጀምር ጠብ የሚል ነገር ላይሠራ መቅረቱን ይረዳል። አገልጋይ እግዚአብሔርና ቤተክርስቲያን ባስቀመጠችው ቦታ መሥራት የሚገባውን ሥራ ለመሥራት በአገልግሎት ቦታው ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠውን ለይቶ ማወቅና ማድረግ አለበት።

በአገልግሎቱ ምን ዓይነት ሥራ መቅደም እንደሚገባ ያላወቀ ወይም አያወቀ ተግባራዊ የማያደርግ አገልጋይ ሰነፍ ነው ማለት አይደለም። በአብዛኛው ለየትኛው ሥራ ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት የማያውቅ አገልጋይ ብዙ ሥራዎችን ይሠራል። ጉልበቱንና ኃይሉን አይቆጥብም። የሚመለከተውንና የማይመለከተውንም ሥራ ይሠራል። የሚሠራው ሥራ ለቤተክርስቲያን ከሚኖረው ጥቅም አኳያ አይመረጥም። ትጉ ሠራተኛ ነው። ከእርሱ ጋር የሚያገለግሉ ሌሎች አገልጋዮች እንደ እርሱ የማይተጉ ከሆነ በተለይም እርሱ ትኩረት በሰጠባቸው ሥራዎች ላይ ትኩረት የማያደርጉ ከሆኑ ይነጫነጫል። ከዚህም የተነሳ ከእነርሱ ጋር ያለው ግንኙነት ይሻከራል።

እንግዲህ ሚዛን የጠበቀ አገልግሎት ለመስጠት ጊዜን በሚገባ መጠቀም መቻል ከፍተኛ ድርሻ አለው። ጊዜ ውድ ነው። አገልጋይ ይህን መልሶ ሊያገኝ የማይችለውን ውድ ጊዜ ለእግዚአብሔር ከብር፣ ለሰዎች መታነጽ፣ ለግል የሕይወት ዓላማ በኬት ለመጠቀም እግዚአብሔር በሕይወታችን ለማከናወን የሚፈልገውን ዋነኛ ዓላማ ማወቅና ለዚህም ተግባራዊነት ራስን በሥርዓት መምራት እጅግ አስፈላጊ ነው።

ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ።

1. አገልጋይ ጊዜውን በሚገባ ተጠቅሞበታል የሚባለው ወይም አልተጠቀመበትም የሚባለው ጊዜውን እንዴት ሲጠቀምበት ነው?
2. የአገልጋይን ጊዜ የሚነጥቁ ነጣቂዎች ምን ምን ናቸው?
3. አገልጋይ ተገቢ ነው ብሎ ለሚያስባቸው ሥራዎች ወይም ጥያቄዎች አምቢ ማለትን የሚፈራበት ምክንያቶች ምንድናቸው?

እንግዲህ አገልጋይ እግዚአብሔር የሰጠውን ጊዜ ሥርዓት ባለው መንገድ የማይጠቀምበት ከሆነ የእግዚአብሔርን ዓላማ ሳይፈጽም ከመቅረቱም በላይ ዛሬ በምድር ባለው አገልግሎቱና ሕይወቱ ከፍተኛ ኪሣራ ይደርስበታል። ከጊዜ አጠቃቀምና አገልግሎትን ሚዛን ባልጠበቀ ሁኔታ ማገልገል በሕይወት፣ በቤተሰብና በአገልግሎት ፍሬያማነት ላይ ሊያመጣ የሚችላቸውን ችግሮች፣ የችግሮቹ ምልክቶች እንዲሁም በዚህ ችግር ውስጥ የገቡ አገልጋዮች እንዴት መውጣት እንደሚችሉ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ እንመለከታለን።

ምዕራፍ 8

በአገልግሎት መዳሸቅን መከላከል

አንዳንድ ጊዜ አገልግሎት መልካም ቢሆንም በሚዛን ካልተያዘ በስተቀር ሕይወትን ሊያዳሽቅ ይችላል። በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ በአብዛኛው ከባድና አስቸጋሪ ሆነው ከሚታዩ ችግሮች መካከል አንዱ ዘወትር ለአገልግሎት ንቁና ትጉ ሆኖ አለመገኘት ነው። አንዳንድ አገልጋዮች መንፈሳዊ አገልግሎት በጀመሩበት የተነቃቃ መንፈስና ሰሜት አይዘልቁም። በሂደት በድካም ነፍስ ይመቱና በፊት የነበረው መነቃቃታቸውና የልብ መነሳሳታቸው ይቀዘቅዝባቸዋል። ከዚያም አንኳን ሌሎች ሰዎችን ማገልገል ቀርቶ በግል ሕይወቱም ከአግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ይበላሻበታል። አንደዚህ ዓይነት አገልጋይ ስለወደፊት ሊያስብ ተስፋ አይታየውም። አነዚህ ምልክቶች አንድ ጥያቄ እንድንጠይቅ ያደርገናል።

በአገልግሎት መዳሸቅ ምን ማለት ነው? በአገልግሎት መዳሸቅ በአገልግሎት ከመወጠር የተነሳ የሚከሰት አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ዝለት ነው። በአገልግሎት መዳሸቅ አንደ ባሎን ራስን መወጠርና መፈንዳት ነው። ባሎን ከመጠን በላይ በአየር ተሞልቶ ሲወጠር በቀላሉ ይፈነዳል። ውጥረቱ እየጨመረ ሲሄድ አደጋ የመከላከል አቅሙ እየተዳከመ ይሄዳል። አገልጋይም መሄድ ከሚገባው ገደብ በላይ በአገልግሎት ሲወጠር ተመሰሳይ ዕድል ፈንታ ይገጥመዋል።

በአገልግሎት መዳሸቅ ማለት ለማገልገል የሚያስፈልገውን ኃይልና ብርታት ማጣት ነው። ዱሮ ለመሥራት የሚቻለውን ሥራ ለመሥራት የሚያስችል ኃይል ይከዳና ባዶ መሆን ነው። አንድ ሰው መነሳትና መቀመጥ ይችል ነበር። አሁን ግን ከተቀመጠ በኋላ ለመነሳት ኃይል ያጣል። በአገልግሎት መዳሸቅም አንድ አገልጋይ አንደ በፊቱ ስማገልገል የሚችልበትን ጸጋ ማጣት ነው።

አገልጋይ ስአገልግሎት ያለው ትጥቅ ምን ያህል እንደሆነ አስቀድሞ ሳይገምትና ምን ያህል እንደተጠቀመበት ሳይከታተል ይቀርና በአገልግሎት ላይ አያለ ትጥቆቹ ያልቁበትና ነዳጅ እንዳለቀበት መኪና ያለቦታው ይቆማል። አንዳንድ ጊዜ በተለይም ተሳፋሪ በሚበዛበት ጧትና ማታ የከተማ ታክሲ ሹፌሮች ቶሎ ቶሎ ሠርቶ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ነዳጅ ሳይቀዱ ይቀራሉ። አሳባቸው ሠርቶ በሚያገኙት ገንዘብ ላይ አንጂ በታክሲው ደህንነት ላይ አይደለም። ታክሲው አየሄደ ድንገት ቀጥ ይላል። ችግሩ ምንድነው ተብሎ ሲታይ ነዳጅ የለውም። ምናልባት በአቅራቢያው የነዳጅ ማደያ ከሌለ «መያላው» ትንሽ ጃርኬን ይዞ ወደ ነዳጃ ማደያ ጣቢያ ይሮጣል። ይህ ሲሆን ተሳፋሪዎች በታክሲው ውሰጥ ይቀመጣሉ ወይም ከቸከሉ ገንዘባቸውን ክሰረው በሌላ ታክሲ ይሄዳሉ።

ትጥቆቹን እንደገና ማግኘት የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ በአገልግሎት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው። ምዕመናን ከአገልጋዩ በገዜው ማግኘት የሚፈልጉትን ነገሮች ማግኘት አይችሉም። ለእነርሱ የሚሰጠውን ነገር ከስልጪው አልተቀበለም ወይም ከመንፈሳዊ ማደያ አልቀዳም። ምዕመኑ መድረስ ከሚፈልግበት ግብ ድረስ ላይደርስ

ሲቀር ደግሞ ይነጫነጫል። ይህ ደግም በአገልጋይና በምዕመኑ መካከል ግጭት እንዲፈጠርም ምክንያት ይሆናል።

በአገልግሎት መዳሸቅ እንደ ብረት ዝገት ነው። ዝገት ብረትን በአንድ ጊዜ አያበላሽውም። ነገር ግን ብረት ሰተከታታይ ጊዜያት ለዝገት ከተጋለጠ ከጥቅም ውጭ ሲሆን ይችላል። ማንኛውም መሣሪያ ተገቢውና አድሰት ካልተደረገለት በስተቀር አየተበላሸ በመጨረሻ ላይ ደግሞ ጥቅም ሲሰጥ በማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። በተመሳሳይ መልኩ በአገልግሎት ውስጥም አገልጋይ አያገለገለ እያለ ለራሱ ተገቢውን እንክብካቤ የማይሰጥ ከሆነና ሕይወቱን የሚያድስበት ልምምድ ከሌለው ቀስ በቀስ ከጥቅም ውጭ ይሆናል። በአገልግሎት ንቁ ሆኖ ለመቀጠል በአካል፣ በአዕምሮ፣ በስሜትና በመንፈሳዊ ሕይወት እየታደሱ መኖር አስፈላጊ ነው። እንዲህ ካልሆነ ዝገት ብረትን እንደሚያበላሽ ሁሉ በአገልግሎት አየባከኑ ራስን መጣልም የዛገ ብረት ያህል ተቀባይነት ያሰጣል።

በአገልግሎት መዳሸቅ ውጫዊና ውስጣዊ ይiት አለው። ውጫዊ ገጽታው በአካል ላይ በሚታየው ዝለት ሲገለጥ ውስጣዊው ደግሞ የሥነልቦና ምላሾችን ለምሳሌ የስሜት፣ አመለካከት፣ ዓላማና ተስፋ በአሉታዊ ጎን መለወጥን ያመለክታል።

በማንኛውም ሥራ ውስጥ እንደሚኖር ሁሉ ከፍታና ዝቅታ በአገልግሎት ሕይወት ውስጥም ያጋጥማል። አገልጋይ በአገልግሎቱ ውስጥ ካጋጠመው ስኬት የተነሳ ራሱን እንደ «አምላክ» የሚቆጥርበት እንዲሁም ምዕመናን «አንደ እርሱ ያለ አገልጋይ የለም» እሰኪሉ ድረስ የሚደርሱበት ጊዜ አለ። በዚህ ጊዜ አገልጋይ በኃይል የተሞላ፣ ከራሱ ተርፎ ለሌሎች ጸጋን የሚሰጥ መልዕክት ያለው፣ መልዕክቱን ለማቅረብ ጸጋና ጥበብ የተሞላ ይሆናል። በተቃራኒው ደግሞ አገልጋይ ባዶነት ተሰምቶት እንኳን ለሌሎች የሚበቃ ጸጋ ያለው መሆን ቀርቶ ለራሱም የሚደርቅበት ጊዜ ያጋጥማል። ከዚህም የተነሳ «ለምን ወደዚህ አገልግሎት ገባሁ» «በዚህ ሁኔታ እንዴት አገልጋይ ሆኜ መቀጠል አችላለሁ?» «ይህን ውርደት እንዴት መሸከም አችላለሁ?» እያለ ጭንቀትና ግራ መጋባት ውስጥ ይገባል።

በአገልግሎት መዳሸቅና በዝቅታ ውስጥ መሆን ምን እንደሚመስል ለማሰየት የአንድ አገልጋይ ሕይወትን እንመልከት። ጌታን ማገልገል ከጀመረ ወደ ሃያ ዓመታት አስቆጥሯል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በውሰጡ እንግዳ የሆነ ስሜት እየተሰማው መጣ። አገልግሎት ሲሰጠውም ለማገልገል ፊቃደኛ አይደለም። ሰዎች ቀድሞ የነበረውን መልካም ነገሩን እያሰቡ ይጋብዙታል። እርሱ ግን አሁን ያለበት ሁኔታ በቀድሞ ሥፍራ ሳይሆን ለራሱም ምን እንደሆነ በማያውቅበት ሁኔታ ነው። «በአጥቢያዬ የእሁድ ስብከት ሲሰጠኝ በጣም አዝናለሁ። ሰዎች ልቤን አያውቁም እንጂ እኔ በግራ መጋባት ውስጥ ነኝ። እነርሱ እንደ ቀድሞ ዘመን ትጉና በውስጤ በመንፈስ የምቃጠል ይመስላቸዋል። የተሰጠኝን አገልግሎት እምቢ ማለት ደግሞ ሌላ ችግር ሲያመጣብኝ ይችላል በማለት ብቻ እሺ ብዬ አገልግሎትን እቀበላለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ከፍቼ ማንበብ ስጀምር ከዚህ ቀደም ያየሁትና መልዕክት ያገኙበት መሆን ቀርቶ አንድም ቀን ክፍቼ ያነበብኩት ዓይነት መጽሐፍ አይመስለኝም። ዱሮ ከፍቼ ማንበብ ስጀምር በውስጤ የሚፈሰው መልዕክት አሁን የለም። ደረቅ ይሆንብኛል። ለጸሎት ስንበረከክ

የምጸልይበትንም ርዕስ አላገኝም። እንደ ነገሩ ከዚህም ከዚያም አላቦኝን በመለቃቀም ሰአሁድ ስብከት ዝግጅት አደርኩና ወደ ጸሎት ቤተ ሄድኩኝ። በጸሎት ቤት ጢም ብሎ ሞልቶ ካለው ምዕመን ፊት ለፊት ከአግዚአብሔር ለእነርሱ መልዕክት አንዳለው አገልጋይ በቀመጥ ውስጤ ይረበሻል። ሕዝቡ ባሬ አግዚአብሔር ይናገረኛል ብሎ ያስባል። እኔ ግን ከአግዚአብሔር ምንም መልዕክት የለኝም። የስብከት ጊዜው ላይደርስ የሆነ እንግዳ ነገር መጥቶ ላልሰብክ ብቀር ደሰ ይሰኝ ነበር። ግን ማምለጫ ሰሰሌሰኝ ለመስበክ ወጣሁ» በማሰት ይናገራል።

ይህ አገልጋይ አንዲህ ዓይነት ሰሜት አንዲሰማው ያደርገው እግዚአብሔር በውስጡ ያስቀመጠው ጸጋ በሚገባ መፍሰቅ የሚችልበትን ዓውድ ባለማዘጋጀቱ ነው። እግዚአብሔር ለአገልጋይ የሰጠው ስጦታ የሚያድገው በአገልግሎት በመባከን ሳይሆን በጸጥታና በአርጋታ በአግዚአብሔር ፊት በመሆን፣ አካሄድን በመፈተሸና ስጦታን በተገቢው ሥፍራ በመጠቀም ነው። በአገልግሎት ሰም መባከን በአገልግሎት የሚያቆይ ላይሆን ሁለንተናዊ ሕይወትን በማሳሸቅ ባዶ የሚያስቀር፣ ሕይወትን ትርጉም የለሽ የሚያደርግና የሕይወትን አቅጣጫ የሚያጠፋ ይሆናል።

ለአገልግሎት የመዳሸቅ ምልክቶች

በአገልግሎት መዳሸቅና የመንፈስ መለሳቸት ተመሳሳይነት አላቸው። በሁለቱም ውስጥ ለአገልግሎት ኃይል ማጣት፣ ቀድሞ የሚወዱትን አገልግሎት ለማገልገል የልብ መነሳሳት ማጣት፣ የለመቻል ስሜትና ተስፋ ቢስነት ይታያሉ። ሆኖም የመንፈስ መለሳቸት የሕይወት ገጽታን ሁሉ የሚነካና ብዙ መንስኤዎች ሲኖሩት በአገልግሎት መዳሸቅ ግን በአብዛኛው ከአገልግሎት ጋር የተያያዘ ነገር ነው። በአገልግሎት መዳሸቅ ከሚታወቅባቸው ምልክቶች ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል። እነርሱም፦

በአገልግሎት የዳሸቀ አገልጋይ ለውነቱ ይደክሚል። ብዙ ጊዜ ከፍተኛ የድካም ስሜት ይለማዋል። በቀን ውስጥ ብዙ ለዓታትን በአገልግሎት ሳይ ያሳልፋል። አንድ ለው በተከታታይ ሲሸከመው ከሚችለው በላይ በአገልግሎት ይወጠራል። ከዚህም የተነሳ አካሉን የሚያሳርፍበት ጊዜ የለውም። እንኳን ለማረፍ ምግብንም በተገቢው ለዓት አይመገብም። ምላውን መብላት የሚገባው በምላ ለዓት ሆኖ አያለ እርሱ ግን በከለዓት በኋላ በመክለስ ጊዜ ይመገባል። ብዙ ጊዜ የጨጓራ ሕመም አንዳለው ይናገራል። ለውነቱ ከመዛሉ የተነሳ ማታ አምሽቶ ወደ ቤት ሲገባ እንቅልፍ መተኛት አይችልም። እንቅልፍ አይወስደውም። ማለዳ ሳይ ከአልጋው ሳይ ለመነሳት በጣም ይቸገራል። ለውነቱ እንደሚገባ ባሰማረፉ የማይሰቀው የራስ ምታት ይለማዋል። በአብዛኛው ጤነኛ አንደሆነ አይለማውም። እርሱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጤንነት እንደማይለማው ይናገራል።

በአገልግሎት የዳሸቀ አገልጋይ አዕምሮውን ለኬታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ይሳነዋል። ቀድሞ አዲስን ነገር ለማወቅና ለመማር የነበረው ጉጉት ይጠፋበታል። በአገልግሎት ውስጥ የሚያጋጥሙትን ጉዳዮች አያነሳ ከሌሎች አገልጋዮች ጋር ይነጋገር ነበር። አሁን ግን ከሌሎች ጋር መነጋገር፣ መከራከርና የልምድ ልውውጥ ማድረግ ያስጠላዋል። በአገልግሎት ተወጥሮ ጊዜ ከማጣቱ የተነሳ አዳዲስ ጽሑፎችን በማንበብ

አዕምሮውን መገንባት አይታይበትም። አዳዲስ ነገሮችን ተምሮ አገልግሎቱን ለማሻሻል ምንም ትጋት የለውም። በአገልግሎቱና በሕይወቱ ውስጥ ለገጠሙት ተግዳሮቶች ዘሳቂ መፍትሔ ለማምጣት ተከታታይነት ያለው ትምህርት ከመፈለግ ይልቅ በአቋራጭ ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉትን መንገዶች ይፈልጋል። አገልጋዩ አዳዲስ ነገሮችን መማር ቀርቶ እርሱ ቀድሞ የሚያውቃቸው ነገሮች አንኳ ጠፍቶበታል።

በአገልግሎት የባከነ አገልጋይ ብዙ ጊዜውን ለሌሎች ለለሚሰጥ ለራሱ ጊዜ የለውም። በቤተክርስቲያን ወቄጥ ችግር ያሳቸውን ሰዎች አየተከታተለ አስፈላጊውን እንክብካቤ ይለጣቸዋል። ዘወትር የሚያስበው ለለሌሎች ለዎች ነው። ከዚህም የተነሳ የራሱን ውስጣዊ ለሜቶች የሚያዳምጥበት ጊዜ የለውም። ለራሱ ምን እንደሚፈልግ አያውቅም። የራሱን ፍላጎት አለማወቁ ደግሞ ከጊዜ በኋላ ለሌሎችም ትኩረት እንዳይሰጥና ግድየለሽ እንዲሆን ያደርጓል። አገልግሎቱ ውስጣዊ እርካታ አያለጣው ሲሄድ ቀስ በቀስ ለሌሎች ለዎች ጉዳይ ቀዝቃዛ የሆነ ምላሽ መስጠት ይጀምራል። ከምዕመናን ጋር የማይገናኝበትን ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ያደርጋል።

አገልጋዩ ለለራሱና ለለሌሎች ሰዎች ያለው አመለካከት አሉታዊ ይሆናል። በአገልግሎቱ እንደ ቀድሞ ትጋት በማጣቱ ራሱን ይኮንናል። በአገልግሎቱ አንድ መልካም ነገር አንደሠራ ለሰማይታየው ለራሱ የሚለጠው ዋጋ ይቀንሳል። «አሁን እኔ የምጠቅም አገልጋይ አይደለሁም» «የእኔ ጊዜ አልፏል» ብሎ ሲናገር ይለማል። አገልግሎት ለእርሱ ማንነት ዋጋ ማግኘት ምንም አስተዋጽአ እንደሌለው ለለሚያስብ በተቻለ መጠን ከአገልግሎት ራሱን ለማግለል ይፈልጋል።

በአገልግሎት መዳሸቅ ውስጥ የገባ አገልጋይ *ለለአገልግሎት ከጓደኞቹና ከቤተሰብ አባላት ጋር መነጋገርን አይፈልግም*፡ ጓደኞቹ ለለአገልግሎት ሲጠይቁት አገልጋዩ ምንም ለመናገር ፈቃደኛ አይሆንም። በተቻለ መጠን ለለአገልግሎቱ እንዲናገር የሚያደርጉትን ርዕሶች ወደ ሌላ ጉዳይ ለመቀየር ጥረት ያደርጋል። ለለአገልግሎት መናገር የማይፈልገው ሰውለጡ ለለአገልግሎት የነበረው አመለካከት ለለተለወጠ ነው።

አገልጋይ ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄድ አርሱ ወጣ ብሎ በነበረበት ወቅት ሰልከ የደወሉ ለዎች መኖራቸውን አይጠይቅም። ከዚህ በፊት ከቢሮ ወጣ ብሎ ሲመለስ ለዎች መደወላቸውን ይጠይቅና ደውለው አርሱን ላጡት ለዎች መልስ ይደውልላቸው ነበር። አሁን ግን እንዲህ ለማድረግ ፍላጎት የለውም። አርሱን የፈለጉት ለዎች ምንም የሚያስደስት ነገር እንደማያመጡለት ነገር ግን ሁላቸውም ሰራላቸው ጥቅም እንደሚፈልጉት በማሰብ ይዘጋቸዋል። ለአርሱ በማስብ የሚፈልገው ሰው እንደሌለ ያስባል። ለዎች ለአርሱ ሸክም እንደሆኑ ይገምታል። ለሰዚህ ማን እንደፈለገው ለማወቅ ከተትል አያደርግም።

ምዕመናን በተመደበሳቸው ፕሮግራሞች መገኘት አለመቻላቸውን ሲገልጹ ወይም በሆነ ምክንያት ፕሮግራም ሲሰርዙ ደስ ይለዋል። ሳያውቅ በውስጡ «ጌታ ሆይ ተመስገን!» ይላል። ይህ ማገልገል ምን ያህል እንደለለቸው ያመለክታል።

አገልጋዩ በሚያገለግልበት ቤተክርስቲያን ውስጥ *ጥቃቅንና ተሳልቆ ችግሮች ይከሰታሉ*። ምዕመናን በፊት የነበራቸውን ሕይወት በመልቀቅ በሕይወታቸው ግራ መጋባት ውስጥ በመግባት ከእግዚአብሔርና ከአርስ በርሳቸው ጋር ያላቸው ችግሮች መብዛት የአገልጋዩ ሕይወት ነጸብራቅ ነው። የምዕመናኑ ሕይወት መልካም አስመሆን የአገልጋዩ ሕይወትና አገልግሎት መዳከምን ያሳያል። ምዕመናን አገልጋዩ ሳያውቅ ከአርሱ ተስፋ መቁረጥን፣ መነጫነጭን፣ ምክንያት አየፈጠሩ አስፈላጊ ነገሮችን አለማድረግንና የመሳሰሉትን ነገሮች ከአርሱ ይማራሉ። ስለዚህ ምዕመናን ያሉበት የሕይወት አቋም የአገልጋዩ ሕይወት ግልባጭ ነው።

አገልጋይ *በተከታታይ ለአሳብ ይዋጣል*። ቁጭ ብሎ ስብዙ ደቂቃዎች ያሰባል። በአዕምሮው ውስጥ ብዙ ነገሮችን ያወጣና ያወርዳል። ቢሮ ገብቶ ቁጭ ብሎ ስመሥራት ሲያስብ አንድ አሳብ ብልጭ ይልበትና ዓይኑ በተተከለበት ሥፍራ ፍንክች ሳይል ስደቂቃዎች ይቆያል። አርሱ ዘንድ ስማማከር የሚመጡ ስዎች ከፊቱ ቁጭ ብለው አያሉ አርሱ በአሳቡ ሌላ ቦታ ይሄድባቸዋል። አሳቡ በአንድ ቦታ አይያዝለትም። አንድን ነገር ለመሥራት ትኩረት ስማግኘት ይቸገራል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአሳቡ ወደኋላ ይመለስና በአገልግሎቱ ፍሬያማ የሆነበትን ጊዜ ያስባል። አዕምሮው በዚህ ከመያዙም የተነሳ ስለአነዚያ የቀድሞ ዘመናት ማውራትን ይወዳል። የአሁኑ ነገር አንዲነሳበት አይፈልግም።

አገልጋዩ *ጊዜውን በተገቢው ሁኔታ መጠቀም* አይችልም፡ ተኝቶ ከአልጋ ላይ መነሳት በራሱ ትልቅ ተግዳሮት ይሆንበታል። ቶሎ ስአንቅልፍ ስለመነሳት ብዙ ምክንያቶችን ይደረድራል። ወደ አገልግሎት ሥፍራው ከሄደም በኋላ ፍጥነት የለውም። ነገሮችን በዝግታ ስማድረግ ይፈልጋል። ብዙም ሳይሠራ የድካም ሰሜት ይሰማዋል። ሥራውን አቋርጦ ቡና ፍለጋ ይሄዳል። ከመደበኛ አገልግሎቱ ውጭ የሆኑትን ነገሮች በማድረግ ብዙ ጊዜን ያጠፋል። ቡና ሲጠጣ አያወራ ስዓታትን ያባክናል። በዚህም ምንም ቅር አይለውም።

አገልጋዩ *ሰብምዕመናን መልካም ያልሆኑ ነገሮችን መናገር ይጀምራል*። አርሱ የሚያገለግላቸው ምዕመናን ተምረው አውነትን ወደማወቅ የማይደርሱ፣ በሕይወታቸው ለውጥ የማይታይባቸው፣ ብዙ ደካማ ጎኖች አንዳሉአቸው ይናገራል። የምዕመኑን ደካማ ጎን ከመሸፈን ይልቅ ለሌሎች ገልጦ በማሳየት ይስቅባቸዋል። ስለምዕመኑ ተገቢ ያልሆኑ ቀልዶችን ይናገራል።

አገልጋዩ ሲያገለግል *አገልግሎቱ ሕያው እንቅስቃሴ የለውም*። አርሱም ለእግዚአብሔር መቅናት አይታይበትም። ሲያስተምር ወይም ሲሰብክ የነበረው ደስታ አሁን የለም። ምዕመናን ዝም ብለው ይሰማሉ። ብዙ አንቅስቃሴ አይታይም። ላቅ የለም። የአገልጋዩ ድምጽ ተመሳሳይ ነው። የለሰቸውና የደከመው ለው ድምጽ ይመስላል። ምዕመናን ከአገልግሎቱ ሲወጡ «የዛሬ ስዓት እንዴት ረዘመ?» «አቤት ሲደክም» «ዛሬስ በጣም ተጫጫነኝ» ይላሉ።

አገልጋዩ *በአገልግሎቱ ወደኋላ ይቀራል*። አርሱ መሥራት የሚገባቸው ሥራዎች በወቅቱ አይሠሩም። ደብዳቤዎች በጊዜው ምላሽ አይስጣቸውም። ከመሪዎች የተስጡትን ሥራዎች አይሠራም። ለምን

እንደሆነ ሲጠየቅ ለበብ ያበዛል። ከአርሱ ጋር የሚያገለግሉ አገልጋዮች በነገሩ ግራ ይጋባሉ።

አገልጋዩ *ለብቻው ማሳለፍን ይፈልጋል*። ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ አንድን ነገር ከመሥራት ወይም ከመዝናናት ይልቅ አቤቱ ውስጥ ሆኖ ቴሰቪዥርን ያያል ወይም ገጠር ከሆነ ደግሞ ጫካ ውስጥ ገብቶ ቁጭ ይላል። ከስዎች ጋር የሚያገናኘውን ጉዳይ ይረሳል። የተሰጠውን መንፈሳዊ ፕሮግራሞችን ይረሳል። ስብሰባ እንዲመጣ ሲነገረው በመርሳት ሳይሄድ ይቀራል። ከቤተሰብ ጋርም በፊት የነበረውን መልካም ግንኙነት ያጣል። በቤተሰብ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ ከመግባትና የራሱን ኃላፊነት ከመወጣት ይልቅ የዳር ተመልካች መሆንን ይመርጣል።

አገልጋዩ ያስበትን ትክክለኛ ሁኔታ በመገንዘብ *ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ የተሰያዩ ምክንያቶችን ለየጠቀሰ ለችግሩ ውስጥ ይመላሰላል*። በአገልግሎት የነበረውን ደስታ የወስደበትን ምክንያት በትክክል ከመፈለግ ይልቅ ሌሎች ሰዎችን ተጠያቂ ያደርጋቸዋል። ሌሎች ሰዎችን መክሰስ መፍትሔ ባይሆንም ይህን ሲያደርግ ይታያል። በችግር ውስጥ የወደቁትን ስዎች በረዳበት መንገድ ራሱን መርዳት ያቅተዋል። «ሁዳ ስለራስ አያውቅም» እንደሚባለው ይሆናል። በዚህ ወቅት የሚደርሰለት የቅርብ ጓደኛ ወይም መንፈሳዊ ሞግዚት ከሌለው ከብዙ ሰዎች ጋር በመጋጨት እንዲሁም ሕይወቱ በማጉረምረም ይሞላና ከፍሬያማ ሕይወት ውጭ ይሆናል።

በአገልግሎት የመዳሸቅ መንስኤዎች

ስአገልግሎት መዳሸቅ አንዲሁ በድንገት የሚመጣ ክስተት አይደለም። አገልጋይ ሚዛኑን ባልጠበቀ ሁኔታ አገልግሎት ሲጀምር ቀስ በቀስ ራሱንና አገልግሎትን ሲያጣ ወደሚችልበት ሁኔታ ውስጥ እየገባ ይሄዳል። ሰለዚህ በአገልግሎት መዳሸቅ ረጅም ሂደት ያለው ሲሆን ቶሎ ካልተነቃበት በስተቀር የውስጥን ኃይል በእዝጋሚ ሁኔታ እየበላ በመጨረሻ ላይ ሕይወትንና አገልግሎትን አደጋ ላይ ይጥላል። የአገልግሎት መዳሸቅ በተሰያዩ ምክንያቶች ሲመጣ ይችላል። አንዳንዶቹ ምክንያቶች ከአገልጋዩ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ አገልጋዩ ከሚያገለግልበት አውድ ጋር የተገናኙ ናቸው።

1. በአገልግሎት መዳሸቅ የሚመጣው አገልጋዩ በሚቀበለውና በሚሰጠው መካከል ልዩነት ሲፈጠር ነው። አገልጋይ ሌሎችን የሚያገለግለው ከእግዚአብሔር በመቀበል ነው። የአገልግሎት ኃይል ምንጭ እግዚአብሔር ነው። አገልጋይ ከእግዚአብሔር የሚቀበለው አርሱ ለለሎች ከሚሰጠው አንሶ ከተገኘ አገልጋዩ እያለቀ ይሄዳል። አናት ስወለደቸው ሕጻን በቂ የጡት ወተት ለመስጠት ከፈለገች በቂ ምግብ መመገብ ይኖርባታል። ለራስዋ በቂ ምግብ ሳትመገብ ሕጻኑዋን ማጥባት ከቀጠለች ስውነትዋ አየተጎዳ ይሄዳል። የምትጎዳው አርስዋ ብቻ ሳትሆን ሕጻኑዋም ጭምር ነው። አናት ተገቢውን ምግብ ካላገኘች የሁለቱም ሁኔታ አስጊ ይሆናል። አንዳንድ አናቶች በሕጻንነት ብቻ ሳይሆን ልጆቻቸው ካደጉ በኋላም ለራሳቸው ምግብ መመገብ ትተው ስልጆቻቸው በመስጠት ይጎዳሉ።

«የእናት ምግብ መቀነትዋ ነው» እየተባለ ለራሳቸው ትኩረት አይሰጡም። ከዚህም የተነሳ በበሽታ ይጠቁና «ያሰቢኪያቸው» ይሞታሉ።

አገልጋይም ከእግዚአብሔር ሳይቀበል ለምዕመናን የሚሰጠው ነገር የለም። ስለዚህ ለምዕመኑ የሚሆነውን ነገር ከእግዚአብሔር ዘወትር ሊቀበል ይገባል። እርሱ ከእግዚአብሔር የሚቀበለው ነገር ለራሱና ለሌሎች የሚበቃ ካልሆነ አገልጋዩ ይራባል፣ ለሌሎችም የሚያጠግብ መንፈሳዊ ምግብ መስጠት አይችልም። በትንሽ ቧንቧ ወደ ቤት ውስጥ የሚመጣን ቧንቧ ትልቁ ቢገጠምለት ተገቢ አይሆንም። በትንሽ ቧንቧ ውስጥ የመጣው ውኃ በትልቁ ውስጥ ይጠራቀማል እንጂ ኃይል አግኝቶ አይወጣም። እንደዚሁም አገልጋይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለራሱ በቅቶ ለሌሎች የሚተርፍ ነገር ካልተቀበለ ከእርሱ አልፎ ሌሎችን የሚባርክና የሚገነባ መልዕክት ማስተላለፍ ይሳነዋል።

2. በአገልግሎት ውስጥ የሚያረካና ትርጉም ያለው ነገር ማጣት ነው። አገልጋዩ እያገለገለ እያለ በውስጡ የነበረው ደስታና እርካታ እየተሟጠጠ ያልቃል። ለመንፈሳዊ አገልግሎት ኃይል የሚገኘው አገልግሎቱ ለአገልጋዩ ውስጣዊ መንፈሳዊ እርካታ በማምጣቱ ላይ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ሆኖ ይህን መንፈሳዊ ሥራ በመሥራቱ ያገኘ የነበረው ትርጉም ሲያጣ ለአገልግሎት የሚያነሳሳው ኃይል ይጠፋል። ይህ ሲሆን ደግሞ ጥቂት የሚባለውን ሥራ እንኳ ለመሥራት ከባድ ሸክም ይሆናል።

3. አገልግሎት ተዳጋጋሚና ተመሳሳይ ዓይነት እንዲሁም ተግዳሮት የሌለበት ሲሆን ነው። ተመሳሳይ የሆነ ሥራ ሁልጊዜ ሲሠራ ይሰለቻል። አገልግሎቱ በፊት የነበረውን የማስደሰት ኃይል ያጣል። አገልጋይ በመጀመሪያ በአገልግሎት ላይ ሲሠማራ የሚሠራቸው ሥራዎች ሲያስደስቱት ይችላሉ። በአገልግሎት ውስጥ ሲቆይ ግን ተደጋጋሚ የሆኑ ሥራዎች ይበዛሉ። በየዕለቱ ትናንት፣ ከሳምንት በፊት የሠራቸው ሥራዎችን ይሠራል። አገልጋይ ምዕመናንን ይጎበኛል፣ ስብከትና ትምህርት ያዘጋጃል፣ ይሰብካል፣ ያስተምራል፣ ሥርዓቶችን ይፈጽማል፣ እነዚህ ነገሮች ዘወትር ተመሳሳይ ከመሆናቸው የተነሳ ይሰልቹታል።

4. ምዕመናን አገልግሎት ለመቀበል ፈቃደኛ ላይሆኑ ሲቀሩ ወይም በአገልግሎቱ ፍላጎት ሲያጡ ተስፋ ያስቆርጣል። ምዕመናን ቀድሞ ሲያገለግላቸው ከነበረው አገልጋይ ይልቅ ሌሎችን እየመረጡ ሲሄዱ በፊት ከእነርሱ ጋር የነበረው አገልጋይ የነበረው የአገልግሎት ፍላጎትና የልብ መነሳሳት ይወድቃል።

5. አገልጋዩ ወደ አገልግሎት ሲገባ እንደሚያገኝ ጠብቆ የገባውን ነገር ሳያገኝ ሲቀር ወይም ሲዘገይበት ተስፋ ይቆርጣል። አንዳንድ ጊዜ አገልጋዩ ጠብቆ የገባው ነገር ተጨባጭ ሆነው ሳይገኙ ሲቀሩ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከተግዳሮቶች ብዛት የተነሳ የተጠበቀው ነገር ሳይገኝ ይቀራል። የጠበቁትን አለማግኘት ደግሞ ስሜትን ይጎዳል። አገልጋይ ቤተክርስቲያን ወይም እርሱ ራሱ ከራሱ የሚጠብቀው ውጤት ተጨባጭ ካልሆነ የራሱን ሁኔታ ከአካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር በማቀናጀት ፍሬያማ አገልግሎት መሰጠት አይችልም። አገልጋዩ ከፍተኛ ውጤት እንደሚያመጣ ለራሱ ዓላማ አድርጎ ቀንና ሌሊት እየሠራ ወደሚፈልገው ግብ ሊደርስ ይችላል። ሆኖም ይህ በተከታታይ ሲሆን አገልጋዩን ማዳሸቁ አይቀርም።

አገልጋይ በመጀመሪያ ወደ አገልግሎት ሲገባ ለአግዚአብሔር ክብር ለመዋል፣ ምዕመናን ለማነጽ እንዲሁም አዳዲስ ነፍሳትን ወደ ጌታ ለማምጣት ነው። ይህ በዓላማ ደረጃ ያለውን እሳብ ተግባራዊ ማድረግ ትልቅ ትግልን ይጠይቃል። አንዳንድ ጊዜ አገልግሎት አገልጋዩ እንደሚፈልገው ሳይሄድለት ይችላል። በዚህ ወቅት አስቀድሞ የነበረው ዓላማ በአገልጋዩ ውስጥ እየሞተ ይሄዳል። የራእዩ መሞት ደግሞ የአገልጋዩንም ማንነት ይጎዳል። ሕይወት ራእይ ከሌሳት ወይም ራእይዋ ካልተሳካለት ትርጉም ታጣለች። አገልጋይ ራእዩውን ለመተግበር የተለያዩ ነገሮችን አድርጎ ካልተሳካለት ባዶነት ይሰማዋል። አገልግሎትና ለሕይወቱ የሚሰጠው ዋጋ ተያያዥነት ስለሚኖራቸው አገልግሎት አልተሳካም ማለት ሕይወትም ትርጉም ስለምታጣ ቢኖርም ባይኖርም ዋጋ እንደሌለው ማሰብ ይጀምራል።

6. በተፈጥሮ በአገልግሎት ውስጥ የድካምና የትጋት ጊዜያት ያጋጥማሉ። በሕይወትና በአገልግሎት ውስጥ የሚመጡትን ቀውሶች በመቋቋም ማለፍ ካልተቻለ ቀውሶቹ ሥፍራን የሚያስለቅቁ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ እንደ አገልጋዩ የመንፈስ ጥንካሬና ችሎታ ይለያያል።

7. አገልጋዩ በሚያገለግልበት ቤተክርስቲያን ውስጥ ለረጅም ጊዜ ይሠራበት የነበረ የአሠራር ሁኔታ ሲለወጥና እዲስና እንግዳ የሆነ አሠራር ሲተካ ቀድሞ የነበረው አገልጋይ ከዚህ ከአዲሱ አሠራር ጋር ለመልመድ ይቸገራል።

8. የአገልጋዩ የስብዕና አቋም፡ በቀላሉ የሚረበሽ፣ ችግርን ለመቋቋም የሚችገርና ግትር እቋም የሚይዝ ሲሆን ሁኔታው ከሰዎች ጋር እንዲጋጭ ያደርገዋል።

9. አገልጋዩ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣና በትጋት እያገለገለ ነገር ግን ቤተክርስቲያን ዕድገት ሳታሳይ ትቀራለች። አዳዲስ ምዕመናን ወደ ቤተክርስቲያን የማይጨመሩ ከሆኑ የአገልጋይ የውስጥ መነሳሳት እየወረደ ይሄዳል። አገልጋይ በአገልግሎቱ ፍሬ የማያይ ከሆነ ብዙ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይጀምራል። «ምናልባት እግዚአብሔር አልጠራኝ ይሆንን?» «እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ያለምን?» «በዚህ ሥፍራ መሆኔ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለምን?» ብሎ መጠየቅና መጠራጠር ይጀምራል። ለእነዚህ ጥያቄዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ግልጽ በሆነ መንገድ መልስ ካላገኘ ለአገልግሎት ያለው መነሳሳት ይጠፋል።

10. በቤተክርስቲያን ውስጥ በአገልጋዮችና በመሪዎችም አካባቢ የሚታየው የከፍተኛ ሥፍራ፣ የሥልጣን፣ የተቀባይነት ፍለጋ በግልጽና በስውር የሚደረገው ትግል እውነተኛ መንፈሳዊ ለሆነ አገልጋይ እንቅፋት ነው። ምሳሌ መሆን የሚገባቸው አገልጋዮች በዚህ ተራ በሆነ ትግል ውስጥ ገብተው ሲያይ መንፈሱ ይረበሻል። ከዚህ ሁኔታ እንዴት ማምለጥ ይቻላል? ከእነዚህ ሰዎች ጋርስ እንዴት ማገልገል ይቻላል? የሚሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይጀምራል። ይህ ደግሞ በቀላሉ መልስ የሚያገኙ ነገሮች ባለመሆናቸው የአገልጋዩን መንፈሳዊና የአገልግሎት ትጋት ክፉኛ ይጎዳል። ለሰቆዩት መንፈሳዊ አገልጋዮችና ስሰቤተክርስቲያን የነበረው መልካም

አመስካከት ይለወጣል። ለካስ ቤተክርስቲያን ማለት አንዲህ ናት ማለት ይጀምራል።

11. የቤተክርስቲያን መሪዎች በአገልጋዮች መካከል አድልዎ ማድረግ የአገልጋይ ሕይወትና አገልግሎት አንዲጎዳ ያደርጋል። የቤተክርስቲያን መሪዎች በዝምድና በትውውቅና በአንዳንድ ሁኔታዎች ለአንዳንድ አገልጋዮች ሲያዳሉ ይችላሉ። ይህም አድልዎ በምደባ፣ በዝውውርና በደረጃ ዕድገት ላይ ሊንጸባረቅ ይችላል። አገልጋይ ሕይወቱንና አገልግሎቱን ለማሻሻል ጥረት ቢያደርግም የመጣበትን ሁኔታ ግን መለወጥ አይችልም። ለምሳሌ የተወለደበትን ሥፍራና ብሔር መለወጥ አይችልም። እርሱ መለወጥ በማይችልባቸው ነገሮች አድልዎ ከተደረገበት ስጣም ያዝናል፣ መንፈሱ ይወድቃል፣ ተስፋ ይቆርጣል። አግዚአብሔርን በንጹሕ ልብ ከማገልገል ይልቅ ወደማይፈልግ ግጭት ውስጥ ይገባል።

12. የቤተክርስቲያን አመራርና አሠራር አገልጋይ ተጠያቂነት ባለው ነጻነት ከአግዚአብሔር የተቀበለውን አደራና ራእይ ከግብ እንዲያደርስ እንቅፋት የሚሆን ከሆነ አገልጋይ ተስፋ ይቆርጣል፣ ለአገልግሎት የነበረው በውስጡ የሚቀጣጠለው መንፈስ ይጠፋበታል። አገልጋይ የታዘዘውን እንጂ በውስጡ ያለውን ነገር ተግባራዊ ለማድረግ ዕድል ከሌለው የልብ መነሳሳቱ ይሞትበታል። እርሱ የሚሠራበት መመሪያ አገልጋይ ምንም አሳብ ሳይጠየቅ በሌሎች ተሠርቶ የሚሰጠው ከሆነ አገልግሎቱን የሌሎች እንጂ እንደ ራሱ አድርጎ አያስብም። ይህ ደግሞ በሙሉ ልቡ እንዳያገለግል ያደርገዋል።

13. የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን በአገልግሎታቸው አለማድነቅ በትጋት የሚያገለግለውን አገልጋይ ጥያቄ ውስጥ ይከታል። አገልጋይ በቅድሚያ ለእግዚአብሔር ብሎ እንዲሁም ምሥጋናና ብድራት ከእርሱ ለመቀበል እንደሚያገለግል ይታሰባል። አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ አገልግሎቱን በትጋት ሠርቶ አመርቂ ውጤት ሲታይ «እግዚአብሔር ይባርክህ» የሚያሰብል ነገር እየታየ ቸል ተብሎ ሲታለፍ አገልጋይ ስሜቱ ይጎዳል። ሌላ ጊዜ ደግሞ አገልጋይ አጅግ ብዙ በተጫባጭ የሚታዩ ፍሬዎች እያፈራ ካደረጋቸው መልካም ነገሮች ይልቅ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ያለው ደካማ ጎን ተጋንኖ ሲወራ ይሰማል። በዚህ ጊዜ አገልጋዩ «ለካስ እኔ ለዚህ ቤተክርስቲያን ጠቃሚ አይደለሁም ወይም እኔ አልፈለግም» ማለት ይጀምራል። ይህ ደግሞ ቀስ በቀስ ለአገልግሎት ያለው ትንዓትና የልብ መነሳሳት እንዲሸረሸር ያደርጋል።

በአንዳንድ ቤተክርስቲያን የአገልግሎት ስኬት ሲገኝ የአገልጋይ ስም አይነሳም። ለስተገኘው ስኬት የሚመሰገነው ኮሚቴ ነው። በተለይ አገልጋይ ምሥጋና የሚያሰጠው አገልግሎት ሠርቶ የቤተክርስቲያን መሪዎች ተገቢውን አድናቆትና ምሥጋና አለመስጠት ክፉኛ ይጎዳል። ቤተክርስቲያን በትጋት ለሚያገለግል አገልጋይ አድናቆት መስጠትን ስምን ትፈራለች?...

14. የቤተሰብ ድጋፍ ማጣት፡ አገልጋይ አርሱን የሚንከባከብ፣ የሚረዳውና አርሱን የሚወደውን አካል ይፈልጋል። አነዚህን ለማድረግ ደግሞ ቤተሰብ ዓይነተኛ አካል ነው።

15. የመንፈሳዊ አገልግሎት ፍሬ በቶሎ አለመታየት፡- አገልጋይ በቤተክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ሥራዎችን ይሠራል። አብዛኛው የአገልጋይ ሥራ መዝራት ነው። የአገልግሎቱን ፍሬ ወዲያውኑ ማየት አዳጋች ነው። ምናልባት አገልግሎቱ በሰዎች ሕይወት ላይ ያመጣው ለውጥ ከረጅም ጊዜ በኋላ የሚታይ ይሆናል። በአገልግሎት ውስጥ የሚታየው መዘራት ሆኖ ማጨድ የማይከተል ከሆነ ተስፋ ሊያስቆርጥ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ «እስከ መቼ ያስምንም ተጨባጭ ፍሬ አገለግላለሁ?» ያስኛል። ከዚህም የተነሳ ለአገልግሎት የነበረውን የቀድሞ የልብ መነሳሳት ያጣል።

16. መንፈሳዊ አገልግሎት የማያልቅ መሆኑ ለአገልግሎት መዳሸቅ ያጋልጣል። አገልጋይ በትጋት ቢያገለግልም ከአገልግሎት ለፋት የተነሳ «የምሠራውን ጨርሻለሁ» የሚባልበት ሁኔታ አይታይም። ዘወትር ሲታይ ሥራው ክፍት ነው። በአንድ ጊዜ ተጀምሮ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ ፕሮጀክት አይደለም። የዕለት አገልግሎትም ቢሆን አገልጋይ «ዛሬ አነዚህን አሠራለሁ» ብሎ በማቀድ ያቀዳቸውን ሥራዎች ጨርሶ ወደ ቤቱ ለመሄድ ሲነሳ መንገድ ላይ ከአንድ የቤተክርስቲያን ምዕመን ጋር ይገናኛል። ምዕመኑ ከሚስቱ ጋር አንደ ተጋጨና ግንኙነታቸው በአሁኑ ጊዜ በመጥፎ ደረጃ ላይ አንደሆነ ያጫውተዋል። ከዚያም ወደዚያ ምዕመን ቤት በመሄድ ከአነርሱ ጋር በመነጋገር የማማከር አገልግሎት ለመለጠት ቀጠሮ ሰጥቶአቸው ይሄዳል። ከዚያ ሲወጣ ደግሞ አንድ ምዕመን በሞባይል በመደወል ወንድሙ ታሞ ሆስፒታል አንደገባ በመንገር መጥቶ እንዲጸልይለት ይጠይቁል። ከቢሮው ሲወጣ የዕለት ሥራውን የጨረሰ መለሎት ነበር። ሆኖም ሥራው ማለቂያ የሌለው አንደሆነ ይረዳል።

ይህ የአገልግሎት ባሕርይ ለንፍና ወይም ተስፋ መቁረጥን ያመጣል። አገልጋዩ «ይህ የማይገፋ ሥራ ለለሆነ ምንም ለውጥ ማምጣት አልችልም» በሚል ለሜት ከተያዘ ተግቶ በመሥራት የበኩሉን ድርሻ ከማበርከት ችላ ማለት ይጀምራል። አገልጋዩ የአገልግሎቱን ለፋት ለማየት ለውጥ ለማምጣት ቀንና ሌሊት በትጋት አያገለገለ አደለ ውጤቱን ለሚያይበት ጊዜ ከአገልግሎት ለፋቱ አንጻር ሲታይ ምንም ሥራ አንዳልተሠራ በማለብ በተለፋ መቁረጥ ለሜት ይጠቃል።

17. የቤተክርስቲያን ምዕመናን ችግር የአገልጋይን ኃይልና ጸጋን ይሟጥጣል። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ምዕመናን አብዛኛዎቻቸው በተለያዩ ችግር ውስጥ ያሉ ከመሆናቸው የተነሳ መፍትሔ ፍለጋ ወደ አገልጋይ ይመጣሉ። ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጡ ለለዎች ለችግሮቻቸው መፍትሔ ፍለጋ ነው ባይባልም ግን ለችግሮቻቸው መፍትሔ ፍለጋ የሚመጡና አሁንም መፍትሔ የሚፈልጉ ምዕመናን ቁጥር ብዙ ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ሊለጥሙ የተዘጋጁ ለዎች አሉ። እነዚህ ምዕመናን ችግሮቻቸውን ይዘው ወደ አገልጋይ ይመጣሉ። አገልጋይ ከአነዚህ ምዕመናን ሁሉ ጋር ያምጣል፣ አነርሱን ከለጠሙበት ነገር ለማውጣት እገዛ ያደርጋል። በውኃ ውስጥ የለጠመን ለው ማውጣት ተግዳሮት አለው። በጥበብ ካልተደረገ በስተቀር ለመውጣት የሚሞክረውንም ለው ሲያለጥም ይችላል። አንዳንዶች ችግሮቻቸውን የሚፈቱባቸው የመፍትሔ አትጣጫዎች ቢኖሩም በዚያ መንገድ ለመሄድ አይፈልጉም። ችግር ካላቸው ምዕመናን ጋር ብዙ ከማላሰፉ የተነሳ በልቡ ሲያደርግ ያለባቸውን ዕቅዶች ተግባራዊ ላያደርግም ይቀራል። አገልግሎት ማለት «በተለያየ ችግር ውስጥ ያሉ ምዕመናንን መንከባከብ ይመለለዋል። ሁልጊዜ

ስለምዕመናን ችግር መስማት አያለደስትም። አንዳንድ አገልጋይ ከዚህ ሁኔታ ይሸሻል። ምክንያቱም ችግሮቹን ሲሰማ የደስታ ስሜት ያጣል፣ ሊበዛበት ይለለቸዋል፣ መፍታት ካልቻለ የተስፋ ቢስነት ስሜት ይሰማዋል፣ አገልግሎቱ ችግረኞችን «ማከም» እንደሆነ አንዲያስብ ያደርጋል፣ የጥናና አገልግሎት አንዲ ለውጥ የማያመጣ ሥራ እንደሆነ ያሳስበዋል። ይህ ሁኔታ አገልጋይ ለአገልግሎት ያለውን መልካም አመለካከት ይሰውጣል።

18. ትክክለኛ ያልሆነ ግንዛቤ መያዝ ለሕይወትና አገልግሎት መዳሸቅ ያጋልጣል። አገልጋይ ዋጋ አንዳለው ለማስመስከር አንዲሁም ተቀባይነት ለማግኘት ብሎ በአገልግሎት ከመጠን በላይ የሚተጋ ከሆነ ምንም ያህል ቢያገለግል በውስጡ የተፈጠረውን የሕይወት ባዶነት መመሉት አይችልም። በአገልግሎት ብዛት ዋጋ አንዳለውና ተቀባይነት ማግኘት ካልቻለ ደግሞ በውሰጥ የሚለማው ባዶነት ለአገልግሎት የነበረውን ኃይል እየሸረሸረ ይጨርሳል። ለአገልግሎት መዳሸቅ የሚያጋልጠው ብዙ መሥራት ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ ላልሆነ ዓላማም ማገልገል ነው። ጥቂት ማገልገል መፍትሔ አይሆንም። መፍትሔው በትክክለኛ ዓላማ ማገልገል ነው።

የአገልግሎት መዳሸቅ መፍትሔዎች

በአገልግሎት መዳሸቅ ውሰጥ የገባ አገልጋይ ያለበትን ሁኔታ ከተቀበለ መፍትሔ ማግኘት ይችላል። በአብዛኛው አገልጋዮች ችግር አንዳላቸው መቀበል ይቸግራቸዋል። ምዕመናን ችግር ይዘው ወደ አነርሱ ሲመጡ መፍትሔ ሲለጡአቸው ቆይተው ዛሬ ደግሞ አነርሱ ራሳቸው በችግር ውሰጥ መግባታቸውን መቀበል ይከብዳቸዋል።

📖 አገልጋይ በአገልግሎት አንዳይዳሸቅ ከአግዚአብሔር ጋር መሆን ያስፈልገዋል። ለአገልግሎት የሚጠራና የሚልከ አግዚአብሔር ከመሆኑም በላይ በአገልግሎት ሥምሪት ላይ ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን ጸጋ የሚለጠው አርሱ በመሆኑ ከአግዚአብሔር ጋር በቂ ጊዜ ማለለፍ እጅግ አለፈላጊ ነው። አግዚአብሔር የለጠው ራእይ ከግብ አንዲደርስ ከጠራውና ከላከው አገልጋይ ጋር ለመሆን ተሰፋ በጥቷል። እርሱ ይህን የተስፋ ቃሉን አያጥፍም። ነገር ግን አገልጋዩ ዘወትር ወደ አግዚአብሔር መቅረብ ይኖርበታል። ጉድለትን የሚሞላ፣ አስፈላጊውን መልዕክት የሚለጥ፣ ድካምን በኃይል የሚለውጥ አግዚአብሔር እያለ በጉድለት፣ ያለወቅታዊ መልዕክትና በድካም መኖር አለፈላጊ አይደለም። ለአግዚአብሔር ጊዜ መስጠትና ከሕያው ምንጭ ለግልና ለምዕመናን የሚሆነውን ጸጋ መቅዳት አያንዳንዱ አገልጋይ መዘንጋት የሌለበትና ትኩረት ሲለጠው የሚገባ ቀዳሚ ጉዳይ ነው።

📖 አገልግሎትን ከዚህ በፊት ይሠራ ከነበረበት ትንሽ ለየት አድርጎ ለማገልግል ጥረት ማድረግ ተመሳሳይ አገልግሎትን በተለየ መንገድ በመሰጠት መሰወጥ ይቻላል። አንዳንድ ጊዜ የአገልግሎት አለጣጥ ለምለሌ የትምህርት አለጣጥ መንገድ ካልተለወጠ በስተቀር ምዕመናን ሊለለቹት ይችላሉ። አገልጋይ የአገልግሎት አለጣጡን ሁኔታ በየጊዜው አያሻሻለ የሚሄድ ከሆነ አርሱም ሆነ ምዕመኑ አይለለቸውም። አገልጋይ የለመደውን መንገድ መለወጥ የማይፈልግና የዱሮ ብቻ መልካምና ከሁሉም የተሻለ እንደሆነ የሚያለብ ከሆነ ተፈላጊነት አያጣ ይሄዳል። በአንድ ወቅት

መልካምና ተወዳዳሪ የማይገኝለት የአገልግሎት አለጣጥ መንገድ ተደርጎ የተቆጠረ ነገር ከጥቂት ዓመታት በኋላ ደግሞ ተፈላጊነት ያጣል። አገልጋይ የለመደውን ነገር መልቀቅ ዋለትና ለለሚያለጣው ቀላል ባይሆንም ካልተለወጠ ደግሞ በአገልግሎት ውስጥ መቆየት አይቻለውም።

ከለመዱት ነገር ወዳልተለመደ ሁኔታ መግባት አስፈሪ ነው። አገልጋይ በሚገባ የሚያውቀውን ነገር ትቶ አዲስ ነገር ሲጀምር እንደ ለማጅ ይሆናል። በአዲሱ ሁኔታ አገልግሎት የጀመሩ ደግሞ ከአርሱ ይበልጡታል። በቀድሞው መንገድ ብቃት ያለው የነበረው አገልጋይ አሁን ደግሞ ገና ጀማሪ ይሆናል። ከለመዱት የአገልግሎት ዘይቤ መውጣትና አዲስ ነገር መጀመር አስፈሪ ነገር ቢሆንም ብቸኛው በአገልግሎት የመቆያ መንገድ እንደሆነ ግን ሲታወቅ ይገባል።

📖 አገልጋይ አገልግሎቱ በምዕመናን ዘንድ ተቀባይነት እንዳጣ የሚያሳዩ ምልክቶች መኖራቸውን ሲያለተውል ወዲያውኑ ምክንያቶቹ ምን እንደሆኑ ማጥናት ይኖርበታል። ምዕመናን በፊት ለአገልግሎቱ ፍላጎት ከነበራቸው አሁን ለምን ፍላጎታቸው ቀነሰ? የአገልግሎቱ ይዘት ነው ወይስ አቀራረቢ ወይስ አገልግሎቱ ከምዕመናን አውዳዊ ሁኔታ ጋር ተዛምዶ ባለመኖሩ በማለት የችግሩን መንለኤ መፈተሽ ይገባል። ምዕመናን ለአንድ አገልጋይ አገልግሎት ያላቸው ፍላጎት ሲቀንስ ለሌላ አገልጋይ ግን ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል። በዚህ ወቅት አገልግሎቱ ተቀባይነት አያጣ የመጣው አገልጋይ ምዕመናን የሚያደንቁአቸውንና በአነርሱ ለመገልገል የሚመርጡአቸውን አገልጋዮች ሁኔታ ማጥናት አስፈላጊ ነው። አነዚህን አገልጋዮች ደካማ ጎናቸውን በማንለት በምዕመናን ዘንድ ከመንቀፍና ከመተቸት ይልቅ ከመልካም ነገራቸው መማር የሚችለውን በመለየት ምዕመናን ከአነርሱ ማግኘት የሚፈልጉትን ነገሮች ለአነርሱ ማቅረብ መቻል ብልህነት ነው።

አንድ አገልጋይ በአገልግሎታቸው ከተላካላቸው ሌሎች አገልጋዮች የሚማራቸው ብዙ ነገሮች ይኖራሉ። አንዳንድ ጊዜ ምዕመናን የሚያደንቁአቸው አገልጋዮች ከቃሉና ከቤተክርስቲያን ወግና ሥርዓት አኳያ ሲታዩ ብዙ ደካማ ጎኖች ሲኖራቸው ይችላሉ። ሆኖም መልዕክታቸውን በመተው ከአሠራራቸው፣ አቀራረባቸውና የአገልግሎት ስልቶቻቸው ብዙ መልካም ነገሮችን በመማር አገልግሎትን ማሻሻል ይቻላል። ስለዚህ አገልጋይ ምዕመናን ፕሮግራም እንደማይመጡ ብዙ ከማውራት ይልቅ ምዕመናን እንደሚፈልጉት ሆኖ መገኘት መልካም ነው። ከአርሱ አንዳት መልካም ነገር እንደሚያገኙ ካለቡ አያሸተቱ እንደሚፈልጉት የታወቀ ነው (ማቴ.24፡28)። ለምዕመናን ተገቢውን ነገር ለመስጠት ብታት ለማግኘት ደግሞ አገልጋይ በራሱ ማድረግ የሚገባውን ማድረግ ያለፈልጎል። የልብ ዝግጅት ሲኖር አግዚአብሔር አስፈላጊውን ጸጋ ሲሰጥ ዝግጁ ነው።

📖 አገልግሎትን በአንድ አቅጣጫ ብቻ ላይሆን ከብዙ አቅጣጫዎች በማየት መገምገም መቻል በአገልግሎት መዳሸቅን ያስወግዳል። አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ ፍሬ አያሰው ነገር ግን በትክክለኛ መንገድ የአገልግሎት ውጤቱን ባለመገምገሙ ተስፋ ሊቆርጥ ይችላል። ይህ እንዳይሆን ባለብዙ ፈርጅ መስፈርት አዘጋጅቶ የራስን አገልግሎት መፈተሽ መልካም ነው። ምዕመናን ስለአገልግሎቱ የሚናገሩት ነገር ብቻ ሰመልካምም ሆነ ለክፋ ምላሽ በቲ አይደለም። አገልጋይ ከአርሱ ጋር አብረው የሚያገለግሉ ሌሎች

አገልጋዮች ሰሰእርሱ አገልግሎት የሚሉትን ነገር ማዳመጥ ጠቃሚ ነው። የቤተክርስቲያን መሪዎችስ ስለእርሱ አገልግሎት ምን ይላሉ? የሚሰውን መጠየቅ ተገቢ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ በተሰይም አደርጋለሁ ብሎ ካቀዳቸው ዕቅዶች አንጻር ምን ያህል ስኬታማ እንደሆነ መገምገም ይችላል።

📖 አገልጋይ ወደ ተግባር ሊሰወጥ የማይችል ዓላማና ግብ ይዞ የሚታገል ከሆነ ተግባራዊ ሊሆን ወደሚችል አቅጣጫ ቢለውጥ የተሻለ ነው። እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠውን ጸጋ መጠን በመረዳት በጸጋው ልክ ማቀድ ተገቢ ነው። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚሠራው እንደ አቅሙ ሳይሆን እንደ አቅማችን ነው። እኛ መሸከም የምንችለውን ያህል ያሸክመናል። ለሰዚህ የራስን ውስንነት ማወቅ ከመጠን በላይ አቅዶ ዕቅዱ ሳይሳካ ሊቀር ደግሞ ላለመጎዳት ይረዳል። አገልጋይ የሁሉን ቻይ እግዚአብሔር አገልጋይ ቢሆንም ሁሉን ነገር ሰማድረግ አይችልም። እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠውን የመከሊት መጠን ማወቅና በተሰጠው መሥራት ከሆነው በላይ ወይም እግዚአብሔር ከሰጠው በላይ ራሱን እንዳያስጠ ይረዷል።

📖 ከአገልግሎት የተወሰነ ጊዜ አረፍት በመውሰድ ማረፍ ጉልበትንና ኃይልን ከሚመጥ ሥራ ሰጊዜው ሰመሰየት ይረዳል። ኢየሱስ ሥራ ሊበዛበት፣ የእርሱን አገልግሎት የሚፈልጉ ሰዎች ሊበዙበት ከሰዎች ተሰይቶ ያርፍ ነበር። አገልጋይ ከአጥቢያው ቤተክርስቲያን እረፍት ወስዶ ሌላ ቦታ ሄዶ ማገልገል እረፍት አይደለም። አገልጋይ በእረፍት ጊዜ ሰግል ሕይወቱ ገንቢ የሆኑትን ነገሮች ማድረግ ይኖርበታል። ከእነዚህም ነገሮች ቃሉን ማጥናት፣ በቂ ጊዜ ወስዶ መጸለይ፣ በተረጋጋ አዕምሮ ስለሕይወቱና አገልግሎቱ ማቀድ፣ መንፈሳዊ መነቃቂያና ሌሚናሮችን መካፈል ይገኝ ብታል። ከቤተሰቡ ጋር መሆንም ይጠበቅበታል።

📖 አገልጋይ እምቢ ማለት በመማር ራሱን በአገልግሎት ከመዳሸቅ ያድናል። በእግዚአብሔር መመራት እንጂ ሰዎችን ሰማስደሰት ሰዎች ሰሚጠይቁት ሁሉ እሺ ማለት ተገቢ አይደለም። መሥራት የምንችለውም ቢሆን ሁሉን ነገር ለመሥራት እሺ ማለት አይገባም። አገልግሎት መሰጠት ለለምንችል ብቻ ሳይሆን አገልግሎቱን በዚያን ወቅት እንድንሰጥ የእግዚአብሔር ምሪት ተቀብለናል ወይ? መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ምን ይለናል? ብለን ተገቢውን ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል። ለተገቢው ነገር እምቢ ማለት የሚሳናቸው አገልጋዮች በአገልግሎት ለመዳሸቅ የሚኖራቸው ዕድል ከፍተኛ ነው። በዚህም በዚያም ሲባክኑ ከዓመታት በኋላ ራሳቸውን እንዲሁም አገልግሎታቸውን ከጀመሩበት ሥፍራ ያጡታል። አሁን ሕይወታቸውንና አገልግሎታቸውን ሊመለከቱ ከትልቅ ተራራ ላይ ወደ ጥልቅ ሸለቆ እንደመውረድ ያህል ወርዷል። እንዲህ ላለመሆን ራስን በአስፈላጊው ጊዜ በትሕትና መንፈስ ሆነን እምቢ ማለትን እንማር።

📖 የአገልግሎት ሸክምን ለሌሎች አገልጋዮች ማካፈል ሸክምን ለመቀነስ ይረዳል። ምናልባት አገልግሎትን ለመካፈል የደረሱ ምዕመናን ከሌሎ አገልጋዮችን በማናራት ላይ ትኩረት በመስጠት ምዕመናንን ለአገልግሎት ማሰታጠቅ አስፈላጊ ነው። እነዚህንና የመሳሰሉትን እሳቦች በመጠቀም አገልጋይ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ኃላፊነት ራሱን፣ ቤተሰቡንና አገልግሎቱን ሳይጎዳ ለዘላቂነት ማከናወን ይችላል።

ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ።

1. *በሕይወትህ ከተሰማመድክው ሁኔታ ዘመነሳት በአገልግሎት መዳሸቅን እንዴት ትገልጠዋለህ?*
2. *በአገልግሎት እግዚአብሔር ሲጠቀምብህና ዝናህም ሲወጣ ብዙ አብይተ ዘርስቲያናት ለአገልግሎት ሲፈልጉህ በውስጥህ ግን «አረፍ» የሚል ድምጽ ቢትሰማ ምን ዓይነት እርምጃ ትወስዳለህ?*
3. *በዓውድህ ለሕይወትና ለአገልግሎት መዳሸቅ መንስኤ የሚሆኑ ነገሮች ምንድናቸው? እነዚህን ነገሮች መከላከል ወይም ማስወገድ ይቻላል?*
4. *በሕይወትህ በአገልግሎት ምክንያት መዳሸቅህን የሚታውቅባቸው ምልክቶች ምንድናቸው? እነዚህን ምልክቶች ሲታይ ምን ዓይነት እርምጃዎችን ትወስዳለህ?*

እንግዲህ በአገልግሎት መዳሸቅ ማለት ሕይወት ባዶ ሆና ሳለች በውጫዊ ሁኔታዎች ግፊት ማገልገል ነው። ይህ የአገልጋይን ሕይወትና አገልግሎት ቀሰ በቀስ የሚገድል አደገኛ ነቀርሳ ነው። የዚህ በሽታ መንስኤዎች የተሰያዩ ቢሆኑም በአጠቃላይ መልኩ ውስጣዊ ኃይል ተሟጦ ማለቁና የኃይል ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር የሚመጣው ኃይል መቀነስ/መቋረጡ/ እና እንዲሰጥ የሚፈለገው አገልግሎት ደግሞ መብዛት ነው። በአገልግሎት መዳሸቅ በአገልጋይ ሁለንተናዊ ሕይወት ላይ በሚታዩ ለውጦች ይታያል። አገልጋዩ እነዚህን ለውጦች ቶሎ ተገንዝቦ ራሱን ለማዳን ቢነሣ መፍትሔ ሊኖረው ሊችል እንዲህ ካልሆነ ግን በቁም የሚገድል በሽታ ነው። ከዚያም ለምንም የማይጠቅም እንደሆነ ይገመትና ይጣላል። ራስን ማዳን በሚቻልበት ጊዜ ተገቢውን እርምጃ እለመውሰድ ከጊዜ በኋላ መልካም ፍሬ የሌለበት ጸጸትን ብቻ ይወልዳል። ለሰዚህ አገልጋይ በአገልግሎት እንዳይዳሸቅ ራሱን መከላከል፣ ከመጣበት ደግሞ ራሱን ለማዳን ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ራስን፣ ቤተሰብንና አገልግሎትን ማዳን ነው።

ክፍል ሁለት

የክርስቲያን ሕይወት

በክፍል አንድ ውስጥ አገልጋይ አንዲት አድርጎ ሚዛናዊ ሕይወትና አገልግሎት ሊኖረው እንደሚችል ተመልክተናል። በዚህ ክፍል ውስጥ ስለአገልጋይ አብዛኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች ስማንኛውም በክርስቶስ አምኖ የእርሱ ተከታይ ለሆነ ሰው ሊሠራ እንደሚችል የታመነ ነው። አገልግሎትን እንደ ማንኛውም ሥራ ብናስብ መርሆዎቹ ለማንም መሥራት ይችላሉ። ሆኖም በእግዚአብሔር ተጠርቶ የወንጌልን ሥራ መሥራት በዓለም ውስጥ ለኑሮአችን ብለን ከምንሠራው ሥራ በዓይነትና በአሠራሩ የተለየ ነው። በመሆኑም የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይ ላልሆኑ ክርስቲያኖች ሕይወት፣ ትዳርና ሥራ እንዲሁም በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚለጠትን መንፈሳዊ አገልግሎት በሚዛናዊነት ለመመጠበቅ ጥቂት ነገሮችን ማንሳቱ ተገቢ ነው።

ከዚህ ቀጥለው የሚኖሩት ሁለት ምዕራፎች ማንኛውንም ክርስቲያን በሚመለከት ሁኔታ ላይ ትኩረት በማድረግ ለሰግል ሕይወት፣ ትዳር፣ ሥራና መንፈሳዊ አገልግሎት ሚዛናዊነት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ማብራሪያ ይሰጣል።

የመጀመሪያ ምዕራፍ ማለትም ምዕራፍ ዘጠኝ ትኩረት ያደረገው በዚህ ዓለም ስለሚሠራው የተለያዩ ሥራዎች ክርስቲያኖች ምን ዓይነት አመለካከት ሊኖራቸው እንደሚገባ፣ ለምን መሥራት እንደሚገባቸው፣ ምን ዓይነት ሥራ አንዲሁም በሥራ ላይ ሊያላዩ የሚገባቸውን ባሕርያት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ያብራራል።

ምዕራፍ አሥር ደግሞ ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም አንደ መጽሐፍ ቅዱስ የሆነውን ሥራ በትጋት በሚሠሩበት ወቅት ለግል ሕይወታቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው አንዲሁም በቤተክርስቲያን ውስጥ ስሚሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎት ጊዜ ሊሰጡ ይገባቸዋልን? ክርስቲያኖች ከላይ ለተጠቀሱ ነገሮች በቂ ጊዜ መስጠት አንደሚገባቸው መናገር ይቻላል። ነገር ግን ለእያንዳንዱ የሚበቃው ጊዜ ምን ያህል ነው? ጊዜውን ምን ዓይነት የቅደም ተከተል አሰጣጥ መርሕ በመከተል መሰጠት ይገባቸዋል? ተከታዩ ምዕራፉ ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል።

ምዕራፍ 9.

ክርስቲያንና ሥራ

በዚህ ክፍል ውስጥ ክርስቲያኖች ስለሥራ ያላቸውን አመለካከት ለመዳሰስ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሥራ የሚሰውን አላብ እንመለከታለን። ሥራ የሚለው አላብ ለዎች ለኑሮአቸው የሚያከናውኑትን ማንኛውንም በአእምሮ ወይም በአካላዊ ኃይል የሚተገበሩ ድርጊቶችን ያጠቃልላል።

አንድ ጊዜ ከአንድ ክርስቲያን ወንድም ጋር ተገናኘን። የተለመደውን ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ሻይ እየጠጣን ስለሕይወቱና ሥራው መጠየቅ ጀምርኩ። ይህ ወንድም በቀለም ትምህርት ከፍተኛ ትምህርት ያለው ሰው ነው። የሚሠራው ብዙ ሰዎች መሥራት የሚመኙበት መሥሪያ ቤት ውስጥ ነው። «ሥራ እንዴት ነው? በሥራህ ምን ያህል ደስተኛ ነህ?» ብዬ ለጠየኩት ጥያቄ «ምን ዋጋ አለው፣ እኔ እየሠራሁ ያለሁት ለምታልፈው ዓለም ነው» ብሎ መለሰልኝ። ለጠየኩት ጥያቄ አንዲህ ያለ ምላሽ ይመልሳል ብዬ አልጠበኩትም ነበር። ምላሹ በጣም ለሰገረመኝ አሳቡን ለጥልቀት ለመረዳት ተጨማሪ ጥያቄዎችን ጠየኩት። በአርሱ እይታ ለዓለማዊ መሥሪያ ቤት ውስጥ መሥራት ለለይጣን መንግሥት እንደ መሥራት ያህል እንደሆነ ገለጸልኝ። እግዚአብሔር የሚከብርበት ሥራ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሠራ ሥራ እንደሆነ ገለጸልኝ። የዚህ ወንድም አመለካከት ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ይኖረዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ክርስቲያኖች ስለሥራ የሚኖራቸው አመለካከት ትክክለኛ መሆኑ የሚለካው የእግዚአብሔር ቃል ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር መጣጣሙ ምን ያህል እንደሆነ በመገምገም ነው። ሰዎች ስለሥራ ያላቸው አመለካከት የሚመነጨው በሥራ ቦታቸው ከሚገጥማቸው ሁኔታ ላይሆን ከልባቸው ውስጥ ነው። በልባቸው ውስጥ ለለሥራ ያላቸው አላብ ደግሞ አእምሮአቸውን ከሞላው መረጃ ይመነጫል።

> *አስቲ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ጊዜ እንውሰድና ስለሥራ ያለንን አመለካከት እንቃኝ። ሥራ የኃጢአት ውጤት ነው ወይስ ኃጢአት ወደ ዓለም ባይገባም ይኖር ነበር?*

በመካከለኛው ዘመን የነበሩ እንዲሁም በአሁኑ ዘመንም አንዳንድ ክርስቲያኖች ሥራ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ለኃጢአታቸው መቀጫ የሰጣቸው እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። ይህ ፍጹም የተሳሳተ አመለካከት ነው። ሥራ እግዚአብሔር ለዎች ኃጢአት በመሥራታቸው የተሰጣቸው ፍርድ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ሥራ የተፈጠረው የሰው ልጅ በኃጢአት ከመውደቁ በፊት እንደሆነ በግልጽ ይናገራል።

ክርስቲያኖች ለለህብት በሚያስቡበት ወቅት ሁለት ነገር በአእምሮአቸው ውስጥ ይመላለሳል። የመጀመሪያው ነገር ክርስቲያን እግዚአብሔር በሰጠው መልካም ዕድል ሁሉ ተጠቅሞ ህብት ማፍራት አስፈላጊ ነው የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጌታ ቶሎ ሊመጣ

ስለሚችልና ዘመኑ አጭር በመሆኑ ብዙ ሀብት ማፍራትን ወደ ጎን በመተው ለዕለት የሚበቃቸውን ያህል እያገኙ መኖር ያስፈልጋል የሚል ነው።

ክርስቲያን ከሥራ ተለይቶ የሚኖርበት ወቅት አይኖርም። አንዳንድ ምዕመናን የዓለም ነገር አስጠልቶአቸው በቅድስና ለመኖር ወደ ገዳም ሲገቡ እንኳ ሥራ ይሠሩ ነበር። በገዳም ውስጥ የሚኖሩ ምዕመናን ከመንፈሳዊ ሥራ በተጓዳኝ ለራሳቸው የሚሆነውን የዕለት ጉርሻ ለማግኘት በትጋት ይሠሩ ነበር።

ክርስቲያኖች ስለሥራ ያላቸው አመለካከት መልካም ወይም መጥፎ እንደሆነ ለመናገር ያስችል ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሥራ የሚያስተምረውን መሠረታዊ እውነት መመልከት አስፈላጊ ይሆናል። የእግዚአብሔር ቃል ስለሥራ ምን ያስተምራል?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለሥራ ምን ይላል?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የመጀመሪያው ሠራተኛ እንደሆነ ያስተምራል። ሥራን የፈጠረው እግዚአብሔር ራሱ ሥራን የሚወድና የሚሠራ ትጉህ ሠራተኛ ነው። እግዚአብሔር ሥራን ሲሠራ አይደክምም፣ ኃይሉ በምንም ተዓምር አያልቅበትም። እግዚአብሔር በሚሠራው ሥራም ይደሰታል።

እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው በኤደን ገነት ውስጥ እንዲንፈላሰስ ብቻ ሳይሆን እርሱ ባስቀመጠው ሥፍራ ኃላፊነት ተሰምቶት እንዲሠራም ነው። እግዚአብሔር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፣ ሁለቱም ይኖሩበት ዘንድ፣ በተሰጣቸው ምድር ላይ ሥራ ሠርተው ይኖሩ ዘንድ ኃላፊነትን ሰጣቸው። «ምድርን... ግዙአትም» (ዘፍ.1:28) የሚል ትዕዛዝ ሰጣቸው።

> *እግዚአብሔር የሰው ልጅ ሥራ እንዲሠራ የፈለገበት ምክንያት ምን ነበር? እግዚአብሔር ሰው እንዲሠ ቁጭ ብሎ ማለትም ምንም ሥራ ሳይሠራ እንዲኖር ለምን አላደረገም?*

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሥራን የሰጠበት ዓላማው ለበረከት እንጂ ለመርገም አልነበረም። ምክንያቱም ሥራ ለሰው ልጅ የተሰጠው ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ነበር። አዳም በኤደን ገነት ውስጥ እንዲቀመጥ ሲያደርግ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው» (ዘፍ2:15) በማለት ተናግሯል። እግዚአብሔር ለአዳም ሔዋንን የፈጠረበትም አንዱ ምክንያት እርሱ ብቻውን እንዳይሆንና በሥራውም እርሱን እንድታግዝ እንደሆነ ማሰብ ይቻላል። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው የመጀመሪያው ሥራ የግብርናና የእካባቢ ጥበቃ ሥራ እንደሆነ እንመለከታለን። ብዙዎች የግብርና ሥራ የሚሠሩ ሰዎች እፈር መግፋትን እንደ እርግማንና ከሥራ ሁሉ በታች እንደሆነ ቢያስቡትም ይህ ግን ለሰው ልጅ የተሰጠ የመጀመሪያው ሥራ ነበር።

ከዘፍጥረት ታሪክ መጀመሪያ የምንረዳው አንድ እውነት ሥራ መርገም ሳይሆን ለሰው ልጅ የተሰጠ በረከት እንደሆነ ነው። እንደዚሁም እግዚአብሔር አምላክ በመሆኑ ለሰው ልጅ የሚያስፈልገውን ነገር በየዕለቱ እየሰጠው ሰው ግን ቁጭ ብሎ እንዲጸልይ ማድረግ ይችል ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲህ አላደረገም። እግዚአብሔር የሰው ልጅ ሠርቶ መኖር እንዲችል የሚያስፈልጉ የሥራ ግብአቶችን አዘጋጀ፣ ለሰው ልጅም የማወቅ፣ የመመራመር፣ የመፈልሰፍና የመፍጠር ችሎታ ሰጠው። ከዚያም አእምሮውንና ጉልበቱን በመጠቀም በአካባቢው ያሉትን ግብአቶችን በማቀናጀት ለኑሮው የሚያስፈልገውን ነገር ለማግኘት እንዲሠራ ኃላፊነት ሰጠው። በዚህ አሠራሩም እግዚአብሔር የሰው ልጅ በእግዚአብሔር በመታመን እርሱ በሰጠው ነገር ራሱን እንዲመራ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ሰው ሆኖ መሥራት ጤናማ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች ሥራን አለመሥራት ግን ከጤናማ ሕይወት መውጣት ነው። ሥራ የጤናማ ሕይወት ምልክት ነው። እያንዳንዱ ሰው ስድስት ቀን መሥራት እንዳለበት ታዟል። ይህም ከጧት እስከ ምሽት ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል። «ሰው ወደ ተግባሩ፣ እስኪመሽም ድረስ ወደ ሥራው ይወጣል» (መዝ.104:23)። እግዚአብሔር ጠዋት ፀሐይን ሲያወጣ «ወደ ሥራ ሂዱ« ማለቱ ሲሆን ምሽት ላይ ፀሐይ እንድትጠልቅ ሲያደርግ ደግሞ «አሁን ከሥራው እረፉ» ማለቱ ነው። ተፈጥሮ ራሱ የሰው ልጅ መሥራትም ማረፍም እንዳለበት ታስተምራለች። እያንዳንዱ ሰው በየዕለቱ መሥራት የሚገባው ነገር አለ። ይህን ሥራው ከጠዋት እስከማታ ድረስ ይሠራል። ሌሊት ደግሞ አርፎ በነጋታው ደግሞ ወደ ሥራው ይሄዳል። ይህ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የፈጠረው የተፈጥሮ ውደት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በስንፍና ምክንያት አለመሥራትን ወይም ታካችነትን እጅግ ይቃወማል። የመጽሐፈ ምሳሌ ጸሐፊ ታካችነት ማለትም ያለሥራ መኖርን መፈለግ፣ እንምሮን ያለምንም ሥራ ማስቀመጥ፣ ራስን ዓላማ ካለው ተግባር ጋር ሳያያይዙ፣ እንድ ለውጥ ለማምጣት ጥረት ለማድረግ መነሳሳት ማጣትን፣ ለሥራ ግድየለሽ መሆንንና ያለሥራ መዝናናትን መሻትን ይኮንናል። ታካችነት ወይም ስንፍና የድህነት ዋነኛ መንስኤ ነው። ደሃ ለመሆን ከስንፍና የተሻለ መንገድ የለም። በተቃራኒው ደግሞ ሲታሰብ ከድህነት ለመውጣት ተግቶ መሥራት ዓይነተኛ መንገድ ነው። ታካችነትን ለማስተማር ከተሰጡት ምሳሌዎች መካከል የሚከተለው ክፍል አንዱ ነው።

አንተ ታካች ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ
መንገድዋንም ተመልከተህ ጠቢብ ሁን።
አለቃና አዛዥ ገዢም ሳይኖራት
ምግብዋን በበጋ ታሰናዳለች
መኖዋንም በመከር ትሰበስባለች።
አንተ ታካች እስከ መቼ ትተኛለህ?
ከእንቅልፍስ መቼ ትነሣለህ?
ጥቂት ትተኛለህ፣ ጥቂት ታንቀላፋለህ
ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ
ችጋርህም ሰይፍ እንደ ታጠቀ ሰው ይመጣብሃል። (ምሳ.6:6-11)

በስንፍና መንፈስ የተያዘ ሰው ስዚህ ባሕርይው ስመላቀቅ መማር ይኖርበታል። በዚህ ክፍል ታካች እንዲማር የተመከረው ከንብረ ጉንዳን ነው። የሰው ልጅ በተፈጥሮም ሆነ በትምህርት ከእንስሳት የተሻለ ነው። የሰው ጥበብ ከእንስሳት ጥበብ ይልቃል። ሆኖም የስነፍ ሰው ጥበብ ከንብረ ጉንዳንም ያነሰ እንደሆነ መመልከት ይቻላል። ሰው ሆኖ ከንብረ ጉንዳን ስመማር ወደዚህ ነፍሳት መሄድ ውርደት ነው። ከደረጃ በታች ሄደው እንደመማር ያህል ነው። ሰነፍ ሰው ከንብረ ጉንዳን እንዲማር መጠየቁ ከደረጃ በታች ሄደው እንደመማር ቢቆጠርም ሰራሱ መልካም ትምህርት ከእነርሱ መማር ይችላል።

ከንብረ ጉንዳን ሰመማር ከፍተኛ ትኩረት መስጠትን ይጠይቃል። ንብረ ጉንዳን የምትሠራውን ሥራ በሚገባ መመልከትና ማስተዋል ከእርስዋ ጥበብን ሰመማር መሠረታዊ እርምጃ ነው። የሰነፍ ሰው ችግሩ ሁኔታዎችን በትኩረትና በጥልቀት እስመመልከቱ ነው። ጠቢብ ሰመሆን ደግሞ አንዱ ዓይነተኛ መንገድ ሁኔታዎችን በማስተዋል መመልከት ነው። ሰነፍ በጥሞና መመልከት ቢችል እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ከእነዚህ ነፍሳት ብዙ ቁምነገሮችን መቅሰም ይችላል።

ሰዎች መልካምን ነገር መማር ከሚችሱባቸው መንገዶች አንዱ ሌሎች ለዎች የሚያደርጉትን መልካም ሥራዎችን በመመልከት የእነርሱን ምሳሌነት መከተል ነው። የሌሎችን ሰዎች መልካም ሕይወትና ድርጊት አይቶ መከተል መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጥበብ መማሪያ መንገድ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም ምዕመናን የእርሱንና እርሱን የሚመስል ሕይወት የሚኖሩትን እገልጋዮች ሕይወትና ድርጊት እንዲከተሉ ምዕመናንን ይመክራቸው ነበር። «ወንድሞች ሆይ እኔን የምትመስሉ ሁኑ፣ እኛም እንደ ምሳሌ እንደምንሆንላችሁ እንዲሁ የሚመላለሱትን ተመልከቱ» (ፊልጵ.3:17) ይላል። ሐዋርያው ጳውሎስ ለሥራ ከማስተማርም በተጨማሪ በመሥራትም ለሌሎች ሰዎች መልካም ምሳሌ እንደነበር በቀደሙት ምዕራፎች ውስጥ ተመልክተናል።

ሌሎች የሚያደርጉትን መልካም ነገር ተመልክቶ ለመማር የሚያሰፈልጉ እርምጃዎች አሉ። እነርሱም፦

- የሚደረገውን መልካም ነገር በትኩረት መመልከትና ማስተዋል፣
- ያስተዋሉትን ነገር በአእምሮአቸው መያዝና ማስታወስ መቻል፣
- ያገኙትን ወይም የቀሰሙትን መልካም ነገር በድርጊት መግለጽ፣
- በልባቸው ተነሳሽነት ድርጊቱ ሁልጊዜ እንዲቀጥል ማድረግ ናቸው።

እንግዲህ ሌሎችን ተመልክቶ መማር አንድ የመማሪያ መንገድ እንደሆነ ስተረዳን ሰነፍ ሰው ከንብረ ጉንዳን እንዲማር የተፈሰገው ነገር ምንድነው? የትምህርቱ ይዘት ምንድነው? ሰነፍ ንብረ ጉንዳንን አይቶ ጠቢብ እንዲሆን ነው የተፈሰገው። ስሰዚህ እንዲማር የተፈሰገው ጥበብን ነው። ምናልባት ጥበብ ምንድነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ጥበብ ከእውቀት ያሰፈ ነገር ነው። ሰስአንድ ነገር ማወቅና አንድን ነገር ለማድረግ የሚያሰችል ሰልት እውቆ ተግባራዊ ማድረግ በተሰያዩ ደረጃዎች የሚመጡ

ናቸው። ጥበብ አንድን ነገር አስተውሎ በመረዳት ያንን እውቀት ተግባራዊ ስማድረግ የሚያሰችል ብቃት ማግኘት ነው።

ሰነፍ ንብረ ጉንዳንን በመመልከት የሚማረው ጥበብ ምንድነው? ንብረ ጉንዳ አለቃና አዛዥ ሳትፈልግ ማድረግ የሚገባትን ነገር በወቅቱ ታደርጋለች። የምታደርገው ነገር ለራሰዋ እንደሚጠቅማት በሚገባ ታውቃለች። በሥራዋም ሌላ አካል እንዲያዛት አትፈልግም። በራሰዋ ተነሳሽነት ከራሰዋ የሚጠበቅባትን ተግባር ማንም ሳያዛት ታከናውናለች። የምትሠራውን ነገር የምትሠራው ለራሰዋ በማለት እንጂ በሌላ አካል ሰለታዘዘች አይደለም። በዚህ ሁኔታ እለቃ ቢኖርም ባይኖርም ሥራው በወቅቱ ይሠራል ማለት ነው። ለሥራዋ የባለቤትነት ስሜት ተሰምቶአት ትሠራለች።

በሥራው ትጋት የሌለው ሰው ከንብረ ጉንዳን በመማር ለራሱ ለሚያሰፈልገው ነገር ሌላው ሰው ሳይነግረውና ሳያዘው በራሱ ተነሳሽነት መሥራት አለበት። እሠሪን ወይም የሥራ መሪን በመፍራት መሥራት ከእንድ ትጉ ሠራተኛ የሚፈለግ ባሕርይ አይደለም። ትጉ ሠራተኛ በተሰይም ክርስቲያን የሆነ ሰው ሰውን ፈርቶ ሳይሆን ለሕሊናው በመታዘዝ ሥራውን በትጋት መሥራት ይጠበቅበታል። በዓውዳችን በአብዛኛው ሰዎች ሥራን በትጋት የሚሠሩት አሠሪው በአጠገብ ሲኖር ነው። አሠሪ ዘወር ሲል ሠራተኞቹ እንዲሁ ጊዜውን ያጠፋሉ። ደመወዝ ሲከፈል ግን በትጋት እንደሠራ ሠራተኛ ደመወዝ ይቀበላሉ። ይህ ከሰው ልጅ የሚፈለግ ባሕርይ አይደለም። ሰው መፍራትና መታዘዝ ያለበት ሕሊናውን ሲሆን የተገባ ነው። የትጉ ሠራተኛ አለቃው ሕሊናው ነው። ሕሊናውን በመታዘዝ የሚሠራ ሠራተኛ ሥራውን የሚሠራው መሥራት ኃላፊነቱ መሆኑን በመገንዘቡ ነው። እንዲህ ዓይነት ሰው ያሰውን ችሎታ፣ አውቀትና ልምድ በመጠቀም የሚቻሰውን ሁሉ በማድረግ የሚሠራው ሥራ ፍሬያማ እንዲሆን ጥረት ያደርጋል።

> *አንዳንድ ሰዎች ሕይወታቸውን የሚጠቅመውን ሥራ በትጋት እንዲሠሩ ሲመክሩ ምክሩን ተግባራዊ አድርገው ኑሮአቸውን ከማሻሻል ይልቅ «ለምን እንዲህ ይለኛል?» ብለው ያኮርፋሉ። እንዲህ ዓይነት ባሕርይ ከምን የሚመነጭ ይመስለችኋል? እንዲህ ዓይነት ባሕርያቸውንም እንዲለውጡ ምን መደረግ አለበት?*

ንብረ ጉንዳን ምግቢን በበጋ ታሰናዳለች። ንብረ ጉንዳን በበጋ እንደ ልብዋ በመንቀሳቀስ ምግብዋን ማሰናዳት ትችላለች። በበጋ ወቅት ያሰናዳችውን ምግብ በሙሉ በእንድ ጊዜ በልታ አትጨርሰውም። ነገር ግን ለክረምት መቀመጥ የሚገባው ምግብ ይቀመጣል። ንብረ ጉንዳን እንኳ ሰለወደፊቱ በማሰብ በዕቅድ ትመራለች ማለት ነው። ዓላማዋ ሰዕሰታዊ ኑሮዋ የሚያስፈልገውን ነገር መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን ከዕሰታዊው ፍጆታ ያሰፈውን ቀሰ በቀሰ በመቆጠብ ለክፉ ቀን ታሰቀምጣለች።

> *አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያኖችንም ጭምር በትጋት እየሠሩ ገቢ ያገኛሉ። ነገር ግን ያገኙትን ነገር በቁጠባ ባለመጠቀማቸው ኑሮአቸው ከቀን ወደ ቀን ሲሻሻል አይታይም። እንደ ክርስቲያን ስለቁጠባ ያለን አመለካከትና ልምምድ ምን ይመስላል? ለነገ ብሎ መቆጠብ*

ለነፍ ለው ከገብረ ጉንዳን የሚማረው ሌላው ትምህርት በምቹ ጊዜ በትጋት በመሥራት ለኑሮ የሚያስፈልገውን ነገር ማግኘት ነው። ለነፍ ጊዜው ምቹ ሆኖ ሳለ መሥራት ይጠበቅበታል። በምቹ ጊዜ መሥራት ብቻም ሳይሆን የሥራውን ፍሬ በአንድ ጊዜ በልቶ መጨረስ የለበትም። ነገር ግን ለዕለት የሚያስፈልገውን ነገር እየተጠቀመ፣ ለነገም ማበቀመጥን መማር ይገባዋል። ከድህነት የመውጫው መንገድ አንዱ ተግቶ መሥራት ሲሆን ከዚህ ባልተናነሰ ሁኔታ ሌላው አስፈላጊ ነገር ደግሞ መቆጠብ ነው። በትጋት መሥራትና በዕቅድ መቆጠብ የአድገት መርሆዎች ናቸው። በትጋት ሠርቶ ብዙ ፍሬ ማፍራት የቁጠባ ባሕል ካልታከለበት ዘላቂነት ያለውን የአድገት ሰውጥ ማምጣት አይቻልም። ቁጠባ ለነገ ከመጨነቅ የተነሳ የሚደረግ ላይሆን በሥራ የተገኘው ፍሬ ዛሬውን ማሰቅ እንደሌለበት መረዳትና አርቆ የማሰብ ውጤት ነው። አንድ ሰው አውቀትና የሥራ ልምድ ቢኖረውም መሥራት የማይችልበት ወቅት ሲመጣ ይችላል። ይህም ከአካባቢ ሁኔታ የተነሳ ወይም ከዕድሜ ማርጀት ወይም ከሌሎች ሁኔታዎች ሲሆን ይችላል። በዚህ ወቅት መጠቀም የሚቻለው በቁጠባ የተቀመጠውን ሀብት ነው። ለነፍ ይህን አያደርግም። ከገብረ ጉንዳን የሚማር ለው ግን ይህን ማድረግ የሚያስችለውን ጥበብ ይማራል።

በበጋ መሥራት ድካም አለው። በጋ የሙቀት ወቅት ስለሆነ በዚያ ሙቀት በትጋት ከመሥራት ይልቅ አቤት ውስጥ ወይም ጥላ ሥር ማረፍ ደስ ይላል። አስቸጋሪ ነገር ቢኖርም ግን የሥራ ወቅት ነው። በዚህ ወቅት በትጋት በመሥራት ለክረምት ጊዜ የሚበቃን ምግብ ማከማቸት ይቻላል። ሥራውን በመተው በተለይም ባለው አካባቢያዊ ሁኔታ በማላበብ ጊዜው ካለፈ ቢፈለግም መሥራት የማይቻልበት የክረምት ወቅት ይመጣል። «ሙሱ በጋ ስትዘል ክርማ ላታስብ ወደኋላ፣ ክረምት ገባ ጉዱዋ ፈላ» እንደሚባለው መሆን ይመጣል። ክርስቲያን በማንኛውም የዕድሜ ደረጃ ላይ ቢገኝ ለመሥራት ያለውን ዕድል ላይጠቀም መቅረት የለበትም።

ለነፍ ከገብረ ጉንዳን መማር ያለበት ሌላው ትምህርት ደግሞ ከሌሎች ሰዎች ጋር በትብብር መሥራት መቻልን ነው። ገብረ ጉንዳን በመተባበር ለጋራ ዓላማና ጥቅም ትሠራለች። አንድ ጉንዳን አንድ ትልቅ ለምግብ የሚሆን ነገር ተሸክማ የምትሄድ ከሆነች ሌላዋ መጥታ ትረዳታለች። በመተባበር ያን ትልቅ ነገር ወደ መጋዘን ያስገባሉ። የሚጠቀሙበት ጊዜ ሲደርስ ደግሞ በጋራ ይጠቀሙበታል። ለነፍ ለው ከሌሎች ሰዎች ጋር በመተባበር ለጋራ ዓላማ መሥራት አይፈልግም። ከዚህ ዓይነት አንድነት የሚሸሸውም ሥራ አንዳያሠሩት ነው። ወደ አንድነቱ ቢገባም ሥራውን በተለያዩ መንገዶች በመለገም ሥራው ከሚፈለግበት ግብ አንዳይደርስ ምክንያት ይሆናል። ከዚህም የተነሳ ትጉ ሠራተኞች ለነፍ ለውን አያስጠጉትም።

«ለንድነት ኃይል ነው» ይባላል። በዓውዳችን ክርስቲያኖች ምን ያህል በገብረት ሠርተው ኑሮአቸውን ለመለወጥ ጥረት እያደረጉ ነው? በመሠረተ አሳብ ደረጃ ክርስቲያኖች ከሌሎች ሰዎች ይልቅ የሚያስተሳስራቸው የክርስቶስ ፍቅርና ሥልጣን አያስ አነርሱ ግን

በገብረት ለመሥራት ሲቸገሩ ይታያል። ይህ ለምን እንዲህ ይሆናል? በገብረት ሠርተው ፍሬያማ በመሆን ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን ምን ቢያደርጉ ይሻላል?

ከዚህ ክፍል መረዳት እንደሚቻለው ለሥራ ምቹ በሆነበት ወቅት ተገቢውን ዋጋ በመክፈል በትጋት መሥራት ከተረ ችጋር ወይም ድህነት መሣሪያ እንደ ታጠቀ ወንበዴ ድንገት ይመጣል። ድህነት ጨካኝ ወንበዴ ነው። የድህነት ለይፍ የሚበላው የማይሠራውን ለው ነው። ከዚህ ለይፍ ከታጠቀ ወንበዴ ማምለጥ የሚቻለው ተግቶ በመሥራት ነው። መሥራት በሚገባበት ወቅት ያለሥራ መቀመጥ የታጠቀ ወንበዴ መጥቶ አደጋ እንዲያደርስ መፍቀድና ቀጠሮ መስጠት ነው። ክርስቲያን ለዚህ ወንበዴ ራሱን መስጠት እንዲሁም ሌሎች ለምችም ራሳቸውን እንዲሰጡ መስጠት የለበትም። ይህንን ለማድረግ ራሱ ተግቶ በመሥራት ለሌሎች ለምች መልካም ምሳሌ በመሆን ማሳየት ይጠበቅበታል።

«የክርስቲያን ደሴት» በሚባል አገር ውስጥ እያለን በዓለም ግን በድህነታችን የታወቅነው ለምን ይሆን? እግዚአብሔር ስለማይወደን ወይስ በዓለም ካሉት ሕዝቦች ሁሉ ኃጢአተኞች በመሆናችን ወይስ ለሥራ ያለን አመለካከት ትክክል ባለመሆኑ ወይስ በትጋት መሥራት የሚገባንን ያህል ስለማንሠራ ወይስ ሌላ? እንደ ክርስቲያን የድህነታችን ምንጭ ምንድነው ብለን መናገር ላንችላለን? ተደጋግፈን በትጋት ብንሠራ ከድህነት ለይፍ ማምለጥ የምንችል አይመስላችሁምን?

ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ተከታዮች በሥራ መትጋት እንደሚገባቸው በግልጽ ያዛቸዋል። እማኞች በትጋት ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እንዲሁም ከዚያ አልፈው ሌሎች ሰዎችን መርዳት እንደሚገባቸው ይመክራቸውና 'ያዛቸዋል። በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ዳግመኛ የተወለዱ ሰዎች መልካም ያልነበረውን ባሕርያቸውን በመተው በአዲስ የሕይወት ዘይቤ መመላለስ ይገባቸዋል። የባሕርይ ለውጥ ማሳየት ከሚገባቸው ነጥቦች አንዱ በሥራ ላይ ባሉቸው አመለካከትና ትጋት ነው። ሐዋርያው «የሰረቀ ከአንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፣ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለኀደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም» (ኤፌ.4፡28) በማለት ይናገራል።

የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው ውስጣዊ ሕይወቱ ማለትም አእምሮው ሲታደስ የቀድሞ ባሕርይውን እርግፍ አድርጎ መተው ይጠበቅበታል። በራሱ ጥረት ቢሆንም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለጥቅም የሚሆን ነገር መፈለግ የለበትም። በኃይልም ሆነ በጥበብ ተገቢ ያልሆነ ሥራ መሥራት የለበትም። በማንኛውም መልኩ በሰርቆት ተግባር ላይ መሳተፍ አይገባውም። ባለው ሥልጣን ወይም ጥበብ በመጠቀም በሕጋዊ መንገድ የእርሱ ያልሆነውን ንብረት መውሰድ ወይም መጠቀም አይገባም።

ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የሰዎችን/የድርጅቶችን ሀብት አለመውሰድ በራሱ እንድ መልካም ነገር ቢሆንም በቂ ግን አይደለም። ይህ የክርስቶስ ተከታይን ባሕርይ ለማሳየት ግማሽ መንገድ የመሄድ ያህል ነው። እንደ ክርስቲያን ኃጢአት የሚባለውን ነገር መተው በራሱ ሙሉ ለውጥን

አያመለክትም። አንድ የሚቀር መሠረታዊ ነገር አለ። ይኼውም በፊት ይሠራ የነበረው ድርጊት ተቃራኒ የሆነ ነገር መሥራት ነው። ከላይ በተጠቀሰው ክፍል ውስጥ አንደተጠቀሰው ይለርቅ የነበረ ለው የክርስቶስ ተከታይ ከሆነ በኋላ አለመሰረቁ መልካም አርምጃ ነው። በስርቆት ላይ ተለማርቶ ለነበረ ሰው መስረቅን ማቆም ሙሉ ለውጥን አያላይም። ሌሎች የሚቀሩት አወንታዊ እርምጃዎች አሉ።

የሥነልቦና ችግር ካላጋጠማቸው በስተቀር በአብዛኛው ለዎች በስርቆት ላይ የሚለማሩት ባለመሥራታቸው ማለትም ሥራ ሠርተው ለራሳቸው ኑሮ የሚበቃቸውን ነገር ካለማግኘታቸው የተነሳ ነው። በመካከለኛው ዘመን የነበረ አንድ መንፈሳዊ መሪ «ስርቆት የሥራ መፍታት ውጤት ነው» በማለት ተናግሮ ነበር። ሥራ የማይሠሩ ለዎች ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለማግኘት ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች አንዱ መለመን ነው። ነገር ግን በለዎች ታይተው ይሉኝታን ለብረው፣ ለማኝ መባልን በመቻል በዚህ ተግባር ላይ መለማራት ያሸማቅቃቸዋል። ከዚህም የተነሳ የለዎችን ንብረት ወደ መስረቅ ይሄዳሉ። ይህ ግን ዘለቂታ ያለው መፍትሔ አይሆንም። የእግዚአብሔር ቃል መፍትሔው ተግቶ መሥራት እንደሆነ ያስተምራል። በተለያዩ መንገዶች የሚደረገውን ስርቆት በማቆም ተግቶ መሥራት ያስፈልጋል። ስለዚህ ቀድሞ ይለርቅ የነበረ ለው ዳግመኛ አንዳይስርቅ ለርቆትን ማቆም ብቻ ላይሆን በእጆቹ ተግቶ መሥራትን መጀመር ይኖርበታል። ዳግመኛ ወደ ስርቆት ተግባር ላለመመለስ ዓይነተኛ ው መንገድ ሠርቶ ህብት ማፍራት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህም በላይ አንድ አርምጃ አንደሚቀር ያመለክታል። ሠርቶ ንብረትና ህብት ማፍራት ብቻ ላይሆን በመሥራት ራሳቸውን መቻል ያልቻሉትን/የማይችሉትን ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ችግር ውስጥ የሚገኙትን ሌሎች ለዎችን መርዳት መጀመር ነው። ይህ ሲሆን ወደ ቀድሞ መጥፎ ባሕርይ መመለስ ይቀራል። በሕይወት ውስጥ የተጀመረው ለውጥም ሙሉ ይሆናል።

ከድህነት ለመውጣት ክርስቲያኖች መጸለይ ወይም የእግዚአብሔርን በረከት መጠበቅ ወይም ተዓምራዊ ተሐድሶ መመኘት ብቻ በቂ ነውን? ከጸሎት በተጨማሪ ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል? በገዛ እጆቻችን በሥራ መድከም ምን ያህል ድርሻ ይኖረዋል?

ጳውሎስ ክምክርና ከትዕዛዝም አልፎ መሥራት እየቻሉ በትጋት ሠርተው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን የማይረዱ አማኞች ከቤተክርስቲያን ጎብረት እንዲገለሉና ቤተክርስቲያን ለአንዲህ ዓይነት ለዎች ምንም ዓይነት አርዳታ ማድረግ አንደማይገባት አጥብቆ ይናገራል (2ተሰ.3:6፣ 14፣ 3:10)።

ጳውሎስ እንዲህ ዓይነት ትዕዛዝ በድፍረት የሚለጠው ሠርቶ ራስንና ሌሎች ለዎችንም መርዳት አንደሚቻል ራሱም ምሳሌ ሆኖ በማሳየት ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ትጉህ የወንጌል መልዕክተኛ ከመሆንም በተጨማሪ ትጉህ ሠራተኛ ነበር (2ተሰ.3:7-9፣ የሐዋ.20:33-35፣ 1ተሰ.2:9)።

ከእነዚህ ከተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለሥራ የምንማራቸው ጠቃሚ ሓሳቦች አሉ። ከእነዚህም የመጀመሪያው ሥራ መልካምና ለለው ልጅ የሚጠቅም መሆኑ ነው። ሥራ መርገም ሳይሆን በረከት ነው። ሥራ ለሚሠራው ለው አንዲሁም ለጎብረተሰቡ ይጠቅማል።

የለው ልጅ በሚሠራበት ጊዜ ለኑሮ የሚያስፈልገውን ማለትም የሚበላውንና የሚጠጣውን ነገር ከማግኘቱም በላይ ሥራው ራሱ ደስታን ይሰጠዋል። ለው የማይሠራ እንዲሁም በሥራው የማይደሰት ከሆነ ትርጉም ያለውን ሕይወት መምራት አይችልም። እግዚአብሔር የለው ልጅ ሥራን እንዲሠራና በሥራውም እንዲደሰት ዕድል ፈንታ ለጥቶታል። ይህ የሚያሳየው ሥራ መልካምና ደስታን ሊሰጥ የሚችል ነገር ሲሆን የለው ልጅ ያለሥራ እንደ ለው ሕይወትን በሙላት መኖር አለመቻሉን ነው። በመጽሐፈ መክብብ ውስጥ «... ለው እግዚአብሔር በሰጠው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ይበላና ይጠጣ ዘንድ ከፀሐይ በታችም በሚደክምበት ድካም ሁሉ ደስ ይለው ዘንድ ነው፣ ይህ አድል ፈንታው ነውና» (መክ.5:18) የሚል ቃል ይነበባል።

ሁለተኛው ሥራ ከእግዚአብሔር ለለው ልጅ የተሰጠ ኃላፊነት ነው። ሠርቶ መኖር ለለው ልጅ የተሰጠ ሞራላዊ ግዴታው ነው። ሥራን ሳይሠራ የለው ልጅ የራሱን ፍላጎት የሚያረካበት ሌላ አማራጭ መንገድ ከእምላክ ዘንድ አልተሰጠም። የለው ልጅ በዚህ በተሰጠው ምድር ላይ የሚፈልገውን አግኝቶ መኖር ከፈለገ በትጋት መሥራት ይኖርበታል። እግዚአብሔር ለውን በገነት ውስጥ አስቀምጦም «ሁሉን ነገር አደርግልሃለሁና አንተ ቁጭ ብለህ ብቻ ብላ፣ ጠጣ፣ ተዝናና» አላለውም። እንኳን ከዚህ በኃጢአት በተበላሸ ዓለም ቀርቶ እግዚአብሔር ለው በኤደን ገነትም ሠርቶ እንዲኖር አዞታል። ስለዚህ አማኞች «አግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፣ እርሱ የምንፈልገውን ነገር ይሰጠናል፣ ዋናው ነገር መጸለይ ነው...» እያሉ በሥራ ላይተኙ መቅረታቸው ወደሚመኙት ገነት ሳይሆን በዓለም በምድረ በዳ ውስጥ እንደሚኖር ለው እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል። በትጋት ሠርቶ መኖር እግዚአብሔር ለለው ልጅ የሰጠው ዕቅድ ለለሆነ አይሻርም። በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር አማኞች ሳይሠሩ እንደሚበርካቸው፣ በተዓምር እንደሚያኖራቸው እንዲሁም ሌሎች ለዎች ሠርቶላቸው እነርሱም እንዲሁ የሚበሉበትንና የሚጠጡበትን ተስፋ አልሰጠም። አማኞች እንደማንኛውም ለው መሥራት ይገባቸዋል። እንደ እግዚአብሔር ለው መሥራታቸው ግን ልዩነትን ያመጣል። ይህን በተመለከተ በኋላ እንመለስበታለን።

አለመሥራት መብት አይደለም። ሥራን መሥራት ግዴታ ነው። ቢጠላም ቢወድም አማኝ ሥራን መሥራት ይኖርበታል። ካልሠራ ይሞታል። አንድሪው ሙሬ የሚባለው ታዋቂው የወንጌል መምህር ሥራን በተመለከተ፦

> በእርግጥ ሥራ የመኖር ከፍተኛው ደረጃ ነው። ሕይወት ድርጊት ናት። ሕይወት ራስዋን የምትገልጠው በምትሠራው ሥራ ነው። አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ መንፈሳዊ፣ የማህበራዊና ብሔራዊ ሕይወት እያንዳንዳቸው የሚለኩት በሥራዎቻቸው ነው። የሚሠራው ሥራ ባሕርይና ጥራት የሚለካው በሚሠራው ሕይወት ነው። ሥራ የሕይወት ውጤት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሕይወት በሥራ ላይ ጥገኛ ናት። ከዚህ ውጭ የሕይወት ሙሉ እድገት፣ መግለጫ እንዲሁም ፍጹምነት አይኖርም። ሕይወት የሥራ ውጤት ናት።
> ...

ሥራ በሕይወት ላይ ጥገኛ ነው። እንዲሁም ሕይወት ለማደግና ፍጹም ለመሆን በሥራ ላይ ጥገኛ ናት። ሕይወት ሁሉ ግብ አላት። ሕይወት ያለሥራ ዓላማዋን ከግብ ማድረስ አትችልም። ሕይወት ወደ ፍጹምነት የምታድገው በሥራ ነው። የሕይወት የተደበቀው ባሕርይዋና ኃይልዋ የሚገለጥበት ዋነኛው መንገድ በምትሠራው ሥራ ነው። ስለዚህ ሥራ የተደበቀው የክርስትና ሕይወት ውበትና መለኮታዊ ኃይል መገለጫ ትልቅ መሣሪያ ነው[12] በማለት ጽፏል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አሳብ ሥራና የሰው ልጅ ሕይወት ከፍተኛ ቁርኝት እንዳላቸው ያመለክታል። ሰው ሥራን ሲሠራ ራሱንም ይለውጣል። ያለሥራ የሰው ልጅ ሕይወት አይሰወርም። የሰው ልጅ ሕይወት መሰወር ደግሞ ሥራን ይለውጣል። ሥራ ሰውን፣ ሰውም ሥራን እየለወጠ ሂደቱ ይቀጥላል። አንዱ ለማደግ ሌላውን ይፈልጋል። ሥራ ሠሪዋን ትመስላለች፣ ሠሪዋም ሥራውን ይመስላል። ስለሆነም የሰው ልጅ ከሥራ ተለይቶ መኖር የሚችልበትና እግዚአብሔር ወዳቀደለት ግብ የሚደርስበት መንገድ የለም።

ስለዚህ ሰው የሚሠራውን ሥራ ቢወድም ባይወድም መሥራቱ የግድ ነው። የሰው ልጅ የሚመሳሰለው ሥራን እንደ ራሱ ግዴታ በመቀበሉ ላይ እንጂ በሚሠራው ሥራ እኩል ደስታና እርካታ በማግኘቱ አይደለም። ብዙዎች በሥራዎቻቸው ደስተኞች ላይሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን ሥራውን ይሠራሉ። ምክንያቱም ሳይሠሩ መኖር አይችሉም። በተለይ ደግሞ እንደ ክርስቶስ ተከታይ ሥራን ሳይሠራ አንድ ሰው እንዴት መኖር ይችላል? ምናልባት «እግዚአብሔር በተዓምር ያኖራል» እያለ በተለያዩ ዘዴዎች መንፈላዊ ነገሮችን እየቀላቀለ ካልሰረቀ፣ ካላጭበረበረ ወይም ካልለመነ በስተቀር ክርስቲያናዊ ሥነምግባርን በጠበቀ ሁኔታ እንዴት ገቢ ሊያገኝ ይችላል?

የሰው ልጅ መልካም ኅብረተሰብን ለመፍጠር ኃላፊነት ተሰምቶት መሥራት ይጠበቅበታል። በኅብረተሰብ ውስጥ የማይሠራ ሰው እንደ መልካም ዜጋ አይቆጠርም። ምክንያቱም ለመልካም ኅብረተሰብ ግንባታ የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ ባለመሆኑ ነው። ስኅብረተሰቡ ማበርከት የሚገባውን ነገር አለማበርከት ለኅብረተሰቡ ሸክም ያደርጋል። መሥራት እየቻለ በትጋት ሠርቶ ራሱን የማይችል ሰው ወላጅም፣ ቤተሰብም፣ ማኅበረሰብም እይወዱትም። ይህ ማለት ሥራን አለመሥራትና በትጋት አለመፈጸም በኅብረተሰቡ ዘንድም ተቀባይነትን ሲያሳጣ በተቃራኒው ደግሞ ሥራን በትጋት መሥራት በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትንና ክብርን ያስገኛል።

መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአት ወደ ዓለም መግባቱ ለዎች ስለሥራ ያላቸው አመለካከት እንዲለወጥ እንዳደረገ ይናገራል። ኃጢአት ወደ ዓለም በመግባቱ ለዎች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ኃላፊነት ተግባራዊ ለማድረግ ችግር ገጠማቸው። ለሥራ ያላቸው አመለካከት ተለወጠ። ሥራ ከባድና የማያስደስት ሆነባቸው። በመጀመሪያ መልካም የነበረች መሬት ከኃጢአት የተነሣ ተረገመች። ከዚያም እሾህንና አሜከላን አበቀለች (ዘፍ.3፡18)። የሥራ ሁኔታ አስቸጋሪ መሆን ደግሞ ለዎች ስለሥራ ያላቸው አመለካከት

[12] Murray, A. (1983). *How to Work for God.* Whitetaker House. Pp28-29

ከእግዚአብሔር አሳብ ውጭ እንዲሆን አንዱ ምክንያት ሆነ። ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባ በኋላ ሥራ ለሰው ልጅ የሚገባውን ደስታና እርካታ መስጠት አልቻለም። «በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ» (ዘፍ.3፡19) ተብሎለታል።

- ✓ ለዎች ሥራን መናቅና ከተቻለ ደግሞ ላይሠሩ አንዲሁ መኖር የሚችሉበትን ሁኔታ ማፈላለግ ተጀመረ።
- ✓ ለዎች ሥራን ለራሳቸው ጥቅም ብቻ መጠቀም ጀመሩ። የራሳቸውን ጥቅም ለማግኘት ደግሞ የሌሎች ሰዎችን መብትና ጥቅም መርገጥ ጎልቶ ይታያል። ሥራን ለግል የማበልጸጊያ መንገድ ማድረግ ከእግዚአብሔር አሳብ ያፈነገጠ ነው (ሉቃ12:15-21)
- ✓ ሥራን እንደ ጣዖት ማምለክም የኃጢአት ውጤት ነው። ለሥራ ከተገቢ በላይ የሆነ ሥፍራ መስጠት ጥሩ ቢመስልም ዘላቂነት ያለው ጥቅም አይኖረውም። ለሥራ ከፍተኛ ሥፍራ ከመስጠት የተነሣ ለብዓዊ ግንኙነት ክፉኛ ይጎዳል።

በጊታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደት ማግኘትና የኃጢአት ሰርየት መቀበል ክርስቲያኖች ስለሥራ የሚኖራቸው አመለካከትና ድርጊት እንዲለወጥ ማድረግ ይችላል?

ለዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ሲበላሽ በሥራ አማካኝነት ለሕይወት ትርጉምና እርካታ ለማግኘት ሙከራ ያደርጋሉ። ሥራ ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ቢታወቅም ለሰው ልጅ እግዚአብሔርን የመተካት አቅም የለውም። እግዚአብሔር የሚሰጠውን የሕይወት ትርጉምና ዘላቂነት ያለውን እርካታ ሥራ መስጠት አይችልም። ከኃጢአት የተነሳ ለሰው ልጅ የተፈጠረበትን ያህል ደስታና እርካታ መስጠት ያልቻለው ሥራ ከክርስቶስ ጋር መልካም ግንኙነት ሲኖር የደስታ ምንጭ ይሆናል። ምክንያቱም ሥራን እግዚአብሔርን የማገልገያ መንገድ እንደሆነ በመቀበል እንደ ግዳጅ ሳይሆን በፍላጎት በመሥራት ነው።

ክርስቲያኖች ምን ዓይነት ሥራ መሥራት አለባቸው?

ሥራ በዚህ ዓለም ብቻ የሚኖር ላይሆን በመንግሥተ ለማያትም እንደሚኖር ተጠቅሷል። ክርስቲያኖች ሊመጣ ባለው የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ምን ዓይነት ሥራ እንደሚሠሩ ባይታወቅም አብዛኛው በዚህ ዓለም ከሚሠራው ሥራ ለየት ያለ እንደሆነ ማሰብ ይቻላል። ከኃጢአት ተጽዕኖ ነጻ በመሆን እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሥራ እንደሚሠሩ ይታመናል (ራእይ22:3)። በመንግሥተ ሰማያት አማኞች ሥራ ይኖራቸዋል። ይህም ሥራ እግዚአብሔርን ማምለክ ሲሆን ቀንና ሌሊት ይደረጋል (ራእ7:15)። ያስ ሥራ ለዘላለም መኖር ትርጉም የለውም። በዚህም ዓይነቱ ይለያይ እንጂ ሥራ ዘላለማዊ ባሕርይ ያለው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ሥራ ከሰው ልጅ ጋር አብሮ የተፈጠረ ነገር እንደሆነና በዚህ ምድር ላይ ሳይወሰን ሊመጣ ባለውም ዓለም እንደሚቀጥል ተመልክተናል። እንግዲህ ክርስቲያኖች ሥራ መሥራት የሚገባቸው ከሆነ ምን ዓይነት ሥራ መሥራት ይገባቸዋል? እግዚአብሔር እያንዳንዱ ክርስቲያን መሥራት የሚገባውን የሥራ መስክ ለይቶ እንደሚገልጽ በግልጽ የተነገረ ቃል የለም።

ሆኖም እግዚአብሔር እንዳንድ ሰዎችን ለተለየ ሥራ ሲጠራቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንመለከታለን።

ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም እንደ ማንኛውም ሰው መሥራት እንዳለባቸው ተመልክተናል። ነገር ግን ምን ዓይነት ሥራ መሥራት አለባቸው? ክርስቲያኖች ሥራን መምረጥ ያለባቸው በምን መሥፈርት ነው?

ክርስቲያኖች አንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነውን ማንኛውንም ሥራ መሥራት ይችላሉ። ለሥራ የተለያየ ደረጃ በመስጠት እንዳንዱን ሥራ መልካም፣ ሌሎችን ደግሞ መጥፎ በማለት በመፈረጅ ሥራዎችን ከማበላለጥ ይልቅ በቃሉ ውስጥ ከተጠቀሱት የእግዚአብሔር ሕግጋት ጋር የማይጋጩትን መሥራት ይችላሉ። ክርስቲያኖች የሚሠሩት ሥራ ቃሉን የማይቃረን፣ ከሥራው የሚገኘው ውጤት (ምርት) ከክርስቲያን ሥነምግባር ጋር የሚጣጣም፣ በማንኛውም መልኩ ኀብረተሰብን የማይጎዳ፣ እንደ ሠራተኛ ለቤተሰብ የሚለጠውን ጊዜ የማይሻማ እንዲሁም ሰውነትን የማይጎዳ ሊሆን ይገባል።

ከእግዚአብሔር አጠቃላይ እሳብ ጋር የሚጣጣም ማንኛውንም ሥራ መሥራት ለክርስቲያን የተፈቀደ ነው። በግለሰብ ደረጃ የሚስማማን ሥራ ለመምረጥ ወይም ለመሥራት እእምሮን ለእግዚአብሔር ማስገዛት፣ የራስን ፍላጎት ለይቶ ማወቅ፣ በወጣትነት ዕድሜ ከሆነ የተለያዩ ሥራዎችን ሞክሮ ማየት፣ ከችሎታ ጋር የሚመጥን ሥራን መሻት፣ የሌሎች ለዎችን ምክር ማግኘት፣ ለሚፈለገው ሥራ በትምህርት ራስን ማዘጋጀት፣ ከግል ችሎታና ፍላጎት ጋር የሚጣጣምን ሥራ ለማግኘት በትዕግሥት መፈለግ፣ ለእግዚአብሔር ክብርን የሚለጥና ለዎችን ለማገልገል ከፍተኛ ዕድል የሚለጥ ሥራን መምረጥ ይቻላል።

ክርስቲያኖች ለምን ይሠራሉ?

በዚህ ዓለም እንደሚኖሩ ለዎች ክርስቲያኖችም ለመኖር መሥራት ይኖርባቸዋል። ለመኖር ለእነርሱ የተለየ አማራጭ መንገድ የለም። ስለዚህ ክርስቲያኖች ለምን ይሠራሉ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነውን? በእርግጥ ክርስቲያኖች ለመኖር ማለትም ለኑሮአቸው አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማግኘት መሥራት የግድ ነው (ምሳ.12:11፣ 14:23፣ 16:26፣ 1ተሰ 4:12)። ክርስቲያኖች የራሳቸውን የግልና የቤተሰብ መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት መሥራታቸው መልካም ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ምኞታቸውን ለማርካትም ሲሠሩ አንደሚችሉ መታወቅ አለበት። ምኞትን ለማርካትና መሠረታዊ ፍላጎትን ለማግኘት መሥራት የተለያየ ነው።

አስቲ ጥቂት ጊዜ እንውሰድና ለምን እንደምንሠራ እናስብበት። ለሥራ የሚያነሳሳን ውስጣዊ ወይም ውጫዊ ምክንያቶች ምንድናቸው? ሥራ የምንሠራ ምን ለማግኘት ነው? ይህን ማወቅስ ምን ያህል የእግዚአብሔርን ዓላማ በሕይወታችን ከግብ ያደርሳል?

ክርስቲያኖች የራሳቸውን መሠረታዊ ፍላጎት ለማርካት በሚሠሩበት ጊዜ ከራሳቸው የተረፈ ነገር በማግኘት ሌሎች ሠርተው ራሳቸውን መደገፍ የማይችሉትን ለዎች ለመርዳትም በትጋት ይሠራሉ። እግዚአብሔር ለድሆዎች ማሰብ አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራል። ተግተው በመሥራት በአካባቢያቸው ወይም ሩቅ ቦታ ያሉትን ድሆዎች መርዳት በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ተግባር ነው። ክርስቲያኖች የማያውቁትን ወገን መርዳት እንኳ ቢያቅታቸው የገዛ ችግረኛ ዘመዶቻቸውንና የዘመዶቻቸውን ልጆች ለመርዳት በትጋት መሥራት እይገባቸውምን? (1ጢሞ6:18)።

ሆኖም ክርስቲያኖች የሚሠሩት ለመኖር ብቻ ብለው አይደለም። ክርስቲያኖች ሌላ ዓላማ አላቸው። ክርስቲያኖች ሥራ የሚሠሩበት ዋነኛው ዓላማ ለእግዚአብሔር ክብርን ለመስጠት ነው። ክርስቲያኖች የሚሠሩት ሥራ ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣት የሚችለው ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነምግባርን የማጠብቅ ሲሆን እንዲሁም ለሥራ ያላቸው እመለካከት በእግዚአብሔር ፊት እስደሳች ከሆነ ነው።

ሥራን መሥራት ለኑሮ ብቻም ሳይሆን የሥነ ልቦና ጥቅም ይሰጣል። እግዚአብሔር የሰጣቸውን ችሎታ በሚጠቀሙበት ጊዜ ለዎች እርካታንና ደስታን ያገኛሉ። *ሥራ* ለክርስቲያኖች እርካታና ደስታ የሚሰጠው በግዳጅ ሳይሆን በፈቃደኝነት ሲሠሩ ነው። ክርስቲያኖች ለምን መሥራት እንደሚገባቸውና ሥራው ለሕይወታቸው የሚለጣቸውን ብድራት በትክክል ሲረዱ ነው። ይህን ዓይነት ግንዛቤ እንዲኖቸው ደግሞ መንፈሳዊ መሪዎች ስለሥራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ትምህርት ሊለጡእቸው ይጠበቅባቸዋል።

ከዚያም በላይ ለራሳቸው የሚኖራቸው እይታ መልካም ሆኖ ለራሳቸው የሚለጡት ዋጋ ወይም ክብር ይጨምራል። «እኔ እንዲህ ማድረግ እችላለሁ» ሲሉ ለራሳቸው የሚለጡት ክብር እየጨመረ ይሄዳል። ሥራ ካልሠሩ ግን የሚለማቸው አንዲህ ያለ ስሜት ሳይሆን «እኔ የተፈጠርኩት በከንቱ ነው፣ ምንም ፍሬ ያለው ነገር ሳልሠራ አኖራለሁ» የሚል ነው። ይህ ደግሞ ለዎች ስለራሳቸው ያላቸው እይታ ወይም ለራሳቸው የሚለጡት ክብር ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል። በአገር ደረጃ እንኳ ደሃ በመሆናችን የሚሰማን የበታችነት ስሜት አለ (መክ.2:24፣ 3:13፣ 22፣ 5:18-19)። ከዚህ አንጻር ሥራ የማንነትን ክብር ይጨምራል ማለት ነው።

ሥራ መሥራት የክርስቲያኖች ግዴታ እንደሆነ ተመልክተናል። ሥራ ተሠርቶ የሚጠበቀው ለኬት ሲገኝ ደግሞ ለእግዚአብሔር ክብርን መስጠት ተገቢ ነው። ለሥራው የሚያስፈልገውን ችሎታና መልካም ዕድሎችን የሚሰጠው አግዚአብሔር እንደሆነ በመረዳት ለእርሱ የሚገባውን ክብርና ምሥጋና መስጠት ለኬቱ በዘላቂነት ለእነርሱና ለኅብረተሰቡ ጥቅምና በረከት እንዲሆን ወሳኝነት አለው (ዘፍ.26:12፣ 1ቆሮ4:7)። የመልካም በረከት ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነ መረዳት ትሕትናን፣ ምሥጋናን፣ ኑሮዬ ይበቃኛል የሚለውን መርሕ መከተልንና በእርሱ ላይ መታመንን ያመጣል። ክርስቶስን ለማይከተሉ ለዎችም መሥራት የሚችሉበትን ችሎታና መልካም ሁኔታ የሰጣቸው እግዚአብሔር ነው። የእነርሱና የክርስቲያኖቹ ልዩነት ለችሎታውና መልካም ዕድሎቹ ምንጮች

ያላቸው ግንዛቤ ነው። ያላመኑ ለዎች ችሎታው ከራሳቸው እንደሆነ ሲያስቡ አማኞቹ ግን ችሎታውን ያገኙት ከእግዚአብሔር እንደሆነ መረዳት ለእርሱ ክብርን ይሰጣሉ።

እንግዲህ ክርስቲያኖች ሥራን የሚሠሩት በዚህ ዓለም በሚኖሩበት ጊዜ ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ከማግኘት ያለፈ ነገር አለው። ሥራ ክርስቲያኖች የተፈጠሩበትና የተፈጠሩለት መስክ ነው። ክርስቲያን ሳይሠራ ለሌሎች ሸክም መሆን የለበትም፣ ይልቁን ሠርቶ ለሌሎች ማካፈል ይኖርበታል። እግዚአብሔር ክርስቲያኖች ሀብታሞች እንዳይሆኑ አልከለከለም። ሀብት ግን የሚገኘው በእግዚአብሔር በመታመን በመጸለይ ብቻ ሳይሆን በመሥራት ነው። ተሠርቶ የሚፈለገው ሀብት ሲገኝ ደግሞ ዓይንን በሀብት ላይ ከመጣል ይልቅ ለሥራው የሚያስፈልገውን ኃይልና ችሎታ ሰጥቶ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር መስጠት ይጠበቃል (1ጢሞ.6:17-19)።

ክርስቲያኖች በሥራ ላይ ሊያሳዩት የሚገባቸው መልካም ባሕርያት

በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች ካላመኑ ለዎች የተሰየ ባሕርይ በሥራ ቦታ ማሳየት አለባቸው። ይህ በሚታይ ተግባር ብቻም ሳይሆን በውስጣዊ እመለካከታቸውም ስለሥራ ባላቸው እመለካከት የተሰየ መሆን አንዳለባቸው ያመለክታል። ያመኑ ካላመኑት የግድ የተሰየ ነገር ሊኖራቸው ያስፈልጋል ማለት ሳይሆን እማኞች ሊኖራቸው የሚገባ አመለካከትና የሚያሳዩት ባሕርይ መልካምና አንደ እግዚአብሔር ቃል መሆን አንደሚጠበቅበት ለማሳየት ነው። ክርስቲያኖች ማሳየት ከሚገባቸው መልካም አመለካከቶችና ባሕርያት መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው። አነርሱም፡-

ትጋት፡- ክርስቲያኖች በሥራቸው ከማንም ሰው በላይ ትጋትን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። እምኞች በተሰጣቸው የሥራ ዕድል ተጠቅመው ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለሰዎችና ለራሳቸው ጥቅም በትጋት መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ትጋት ጊዜን በሚገባ መጠቀም ያስችላል። ጊዜ ቆሞ አይጠብቅም። ጥበበኞች ግን እግዚአብሔር በሰጣቸው ጊዜ በትጋት በመሥራት ይጠቀሙበታል።

> *ክርስቲያኖች የግላቸው ያልሆነውን ሥራ ማለትም ለሌላ ሰው ወይም ድርጅት ተቀጥረው የሚሠሩ ከሆነ ከሌሎች ሠራተኞች በተለየ ሁኔታ ትጋት ማሳየት ይጠበቅባቸዋልን? በየወሩ ደመወዝ አሰከተከፈላቸው ድረስ ለምን በትጋት መሥራት ያስፈልጋቸዋል?*

ሐዋርያው ጳውሎስ ምዕመናን በትጋት ሥራዎቻቸውን መሥራት እንደሚገባቸው ይመክራቸዋል። «ሰለው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ ሁሉ በትጋት አድርጉት፣ ከጌታ የርስትን ብድራት እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና» (ቆላ.3:23-24) ይላል። ክርስቲያኖች በሚሠሩት ሥራ ሁሉ ትጋትን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። ለሰው ሳይሆን እግዚአብሔርን እያገለገሉ እንደሆኑ እንዲያስቡና እንዲሠሩ ተመክረዋል። ይህ ማለት በሥራቸው ክብርን የሚሰጡት ሰሚያመልኩት አምላካቸው እንደሆነ በመገንዘብ እንደ ቃሉ፣ በልብ ቅንነት አርሱ በሰጣቸው ችሎታ መልካም የሆነውን ነገር ያለመታከት መሥራት አስባቸው ማለት ነው።

ለእሠሪያቸው በትጋት ሲሠሩ እግዚአብሔርን ማክበራቸው ነው። እንዲህ ዓይነት መልካም ሥራ በመሥራታቸውም ካከበሩት ከእግዚአብሔር ዘንድ ብድራታቸውን ያገኛሉ።

ታማኝነት - ክርስቲያኖች ለሚሠሩት ሥራ ታማኞች መሆን ይገባቸዋል። ማንም ሰው የታዘዘውን ነገር በታማኝነት በሚሠራበት ጊዜ አዛዡ በጣም ደስ እንደሚሰው የታወቀ ነው። ሠራተኛ በታማኝነት ሥራውን በሚያከናወንበት ጊዜ አሠሪ በጣም ይደሰታል፣ በሠራተኛው ሥራ አርካታን ያገኛል እንዲሁም ለሠራተኛው ተገቢውን ብድራት ለመስጠት ያስባል። ሐዋርያው ጳውሎስ በቀርጤስ ቤተክርስቲያንን ይመራ ለነበረው ቲቶ በጻፈው መልዕክት ውስጥ እንደ ቤተክርስቲያን መሪ ቲቶ የቤተክርስቲያን አባላት ሆነው በተሰያየ ቦታ በወቅቱ ባሪያዎች ሆነው ለሚሠሩ ምዕመናን እንዲህ የሚል መልዕክት ጽፎ ነበር።

> ባሪያዎች ስለመድኃኒታችን ስለእግዚአብሔር የሚሆነውን ትምህርት ሁሉ ነገር ያለመሰግኑ ዘንድ ለገዛ ጌቶቻቸው እንዲገዙ በሁሉም ደስ እንዲያሰኙ ሳይቃወሙና ሳይሰርቁም በጎ ታማኝነትን ሁሉ እንዲያሳዩ ምከራቸው (ቲቶ2:9-10)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በተሰያየ ሥራ ላይ ተሠማርተው የሚኖሩ በወቅቱ ባሪያዎች የነበሩ ለዎች በጎብረተሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ሥፍራ ቢኖራቸውም ይህ ግን ለእግዚአብሔር አሳብ ከመታዘዝ ነጻ እንደማያደርጋቸው ይናገራል። የክርስቶስ ተከታይ የሆነ አማኝ በማንኛውም የኑሮ ደረጃ ላይ ቢገኝ፣ ምንም ዓይነት ሥራ ቢሠራ በሚገኝበት ሥፍራ ሁሉ የክርስቶስን ሕግ መፈጸምና ሥራውን በፈሪሃ እግዚአብሔር ማከናወን ይጠበቅበታል። ሠራተኞች ለአሠሪያቸው መታዘዝና ሥራቸውን ደግሞ በታማኝነት መፈጸም ይገባቸዋል። ይህ አሠሪን መታዘዝ የሚሰው አሳብ አርሱን/አርስዋን በመፍራት አለቃ የሚለውን ነገር መፈጸም ሳይሆን ለአሠሪ የሚገባውን ሥፍራ በመስጠት ከማክበር የመነጨ መታዘዝን ማሳየት ነው። ክርስቲያን የሆኑ ሠራተኞች ለአሠሪያቸው የሚታዘዙት በራሳቸው ፈቃድ በዚያ ሥፍራ ሆነው ለመሥራት በመወሰናቸውና ይህም የእግዚአብሔር አሳብ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ጉልበታቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ልምዳቸውንና ጊዜያቸውን ሳይቆጥቡ በታማኝነት ማገልገል ይገባቸዋል። በሚሠሩበት ሥፍራ ታማኝነትን ማጉደል አሠሪያቸውንና ራሳቸውንም ይጎዳል። ከሁሉም በላይ ደግሞ እግዚአብሔርን ያሳዝናል፣ እርሱ በሕይወታቸው እንዳይከብር ያደርጋል።

ክርስቲያኖች በሚሠሩበት ቦታ ተገቢ በሆነ ነገር ሁሉ አሠሪዎቻቸውን ደስ ማሰኘት እንደሚገባቸው ታዘዋል። አሠሪያቸው የሚያዛቸው ከክርስቲያናዊ ሥነምግባር ውጭ ካልሆነ በስተቀር ሥራውን በሚመለከት ለአሠሪያቸው መታዘዝና የታዘዙትን በታማኝነት መፈጸም ተገቢ ነው። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሆነ መታዘዝ ለአሠሪ መታዘዝ ከአሠሪ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔርም ዘንድ ብድራትን ያስገኛል። ለክርስቲያን ሠራተኞች የአሠሪያቸው የሆነውን ማንኛውንም ነገር ያለፈቃድ ለራሳቸው ጥቅም ማዋል ከሥነምግባር የጎደለ ሥራ ነው። የአሠሪያቸው የሆነን ነገር ያለፈቃድ መጠቀም ብቻም ሳይሆን የአሠሪያቸው ለሆነው ነገር ለራሳቸው ንብረት እንደሚጠነቀቁ ሁሉ መጠንቀቅና በአግባቡ መጠበቅ ይገባቸዋል። አሠሪያቸው እነርሱን በማመን ለሚሰጣቸው ለማንኛውም ነገር

ታማኞች ሆነው መገኘት ደረጃውን የጠበቀ ክርስቲያናዊ ሕይወት የመኖራቸው አንዱ ምልክት ነው።

ክርስቲያን ሠራተኞች የአሠሪያቸውን ንብረት አለመሰረቅ ወይም ያለ አግባብ ማባከን መተዋቸው ብቻ በቂ አይደለም። መጥፎ የሆነውን ነገር አለማድረግ መልካም ቢሆንም የክርስቶስ ተከታዮች ግን ከዚያ ያለፈ መልካም ነገር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በዚሁም መሠረት ክርስቲያን ሠራተኞች አሠሪያቸው አሁን ካለበት ደረጃ በላይ እንዲያድግ ከአነርሱ የሚጠበቀውን ማንኛውንም መልካም ነገር ሁሉ ማከናወን ይኖርባቸዋል። ሌሎች ከአነርሱ ጋር የሚሠሩ ሠራተኞች መጥፎ ነገር ቢያደርጉም «የእኔ መልካም ነገር ማድረግ ምን ለውጥ ሲያመጣ ይችላል?» ብለው ተስፋ ሳይቆርጡ በራሳቸው በኩል ማድረግ የሚችሉትን መልካም ነገር ሁሉ ማድረግ ቀለል በቀለ ለውጥን ያመጣል።

መጥፎ ነገር የአንድን ቡድን ሥርዓት ወደ መጥፎ ሁኔታ መለወጥ እንደሚችል ሁሉ መልካም የሆነ ነገር በሥርዓቱ ውስጥ ሲከናወንም ሥርዓቱን ወደ መልካም ሁኔታ መለወጥ ይችላል። «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ... መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» (ማቴ.5፡14-16) ብሎ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለተከታዮቹ የተናገረውን ቃል ማስታወስ ጠቃሚ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም የክርስቶስ ተከታዮችን «በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለ ነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች አንድትሆኑ ሳታንጎራጉሩ ከፋም ሳታስቡ ሁሉን አድርጉ በእነርሱም መካከል የሕይወትን ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ» (ፊልጵ2፡14-16) በማለት መክሮአቸዋል።

ብርሃን በብዛት ሳይሆን በማንነቱ ጨለማን የማስወገድ ኃይል አለው። ክርስቲያኖች በሚሠሩበት ሥፍራ ብዛት ባይኖራቸውም በአካባቢያቸው ላሉት ሰዎች ብርሃን መሆን ይችላሉ። እንደ ክርስቲያን በሥራ ቦታችን እንዴት በመልካም ሥራችን ሰዬሎች ሰዎች ብርሃን መሆን እንችላለን? በግላችን ብርሃን ሆነን ለእግዚአብሔር ክብር ማምጣት የምንችልባቸው መንገዶች ምንድናቸው?

ክርስቲያኖች በየትኛውም ሥፍራ በሚሆኑበት ወቅት ብርሃን መሆን ይጠበቅባቸዋል። ፍጥረተ-ዓለም ሲፈጠር በዓለም ትልቅ ልዩነት *ያመጣው* የብርሃን መፈጠር ነበር (ዘፍ1:3)። ይህ በብርሃን መፈጠር ትርጉም ያገኘው ዓለም ዛሬም የሚኖረው በብርሃን እማኝነት ነው። የዓለም አዳኝ የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ የዓለም ብርሃን እንደሆነ ተናገሯል (ዮሐ.8፡12)። ክርስቲያኖችም እርሱን በመከተላቸው የእርሱ ባሕርይ በሕይወታቸው ውስጥ ይንጸባረቃል። ይህን ባሕርይ ደግሞ በዓለም በሚሆኑበት በማንኛውም ሥፍራ ማሳየትና ብልሹ ሥርዓት ባለበት ዓውድ ውስጥ መልካም ሥራዎችን በመሥራት መልካም ለውጥን የሚያመጣ አቅጣጫን ማሳየት ይገባቸዋል። የክርስቶስ ተከታዮች ሙሰናና ብልሹ አሠራር ባለበት ሥርዓት ውስጥ ሆነው መልካም ነገርን እያደረጉ ለውጥ ማምጣት ካልቻሉ ዓለም ምን ተስፋ ሊኖራት ይችላል?

ከተነሳንበት ርዕስ አንጻር ክርስቲያኖች በሥራ ቦታዎቻቸው ያለው ሥርዓት ታማኝነትን የማያበረታታ ቢሆንም ተስፋ ሳይቆርጡ መልካም ሥራን ሁሉ እየሠሩ በሥርዓቱ ውስጥ እንደ ምልክት መታየት ቢችሉ እንደ ተራራ የማይገፋ የሚመስለው መልካም ያልሆነው የሰዎች አመለካከትና ድርጊት ይለወጣል። ክርስቲያኖች በለምዶ ዘንድ እንደ መልካም እጋጣሚ የሚታዩትን ነገሮች ባለመፈጸማቸውና ራሳቸውን በክርስቲያናዊ ሥነምግባር ማስገዛታቸው ከውጭ ሆነው ለሚመለከቱ ለዎች የተለያየ ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል የታወቀ ነው። ቢሆንም ክርስቲያኖች ከሥነምግባር የጎደለ ድርጊት ጋር ባለመተባበራቸው ሌሎች እንደሚፈልጉት እንዳያደርጉ እንቅፋት በመሆናቸው ደስ ሲላቸው ይገባል። እንዲሁም የሚበጃቸውን የማያውቁ፣ ከሞት በኋላ መልካም ብድራት ለማግኘት ብለው በተሰጣቸው ዳግመኛ ዕድል በማይኖራቸው በዚህች ዓለም ምስኪን ኑሮ የሚኖሩ ሞኞች፣ ጠባብ አእምሮ ያላቸው፣ አጉል ጽድቅ የሚፈልጉና የመሳለሉት አያሉ ማጥላላታቸው እንደሚኖር መገንዘብ መልካም ነው።

በተቃራኒው ጥቂቶች ደግሞ ክርስቲያኖቹ ለራሳቸው ጥቅም ሳይሸነፉ ራሳቸውን በመግዛት የተሰማሩበትን ሥራ በታማኝነት ሲያከናውኑ በማየታቸው ያደንቁአቸዋል፣ እነርሱንም ለመከተል ፍላጎት ይኖራቸዋል። አንድ ነገር እርግጠኛ መሆን ይቻላል፣ እርሱም ክርስቲያኖች መልካም ሥነምግባራቸውን ጠብቀው በታማኝነት ሥራዎቻቸውን ሲሠሩ በሚሠሩበት ዓውድ ውስጥ በጨለማ ውስጥ እንዳለች ጭል ጭል እንደምትል ብርሃን መሆናቸው ነው። እነዚህ ጭል ጭል የሚሉ ብርሃናት አንድ ላይ ሲመጡ ደግሞ ምድራችንን ወደ መልካም ሁኔታ መለወጥ የሚችል ኃይለኛ ብርሃን ይሆናሉ።

ለለሆነም ክርስቲያኖች በሚሠሩበት በማንኛውም ሥራ ቦታ ክርስቲያናዊ ሥነምግባራትን በመጠበቅ በሚሠሩት ሥራ ስኬታማ ከመሆንም አልፈው ለእግዚአብሔር ትልቅ ክብር የሚያመጣ ለውጥን ማምጣት ይችላሉ። እንዲህ እንዲሆን «ክርስትና በልብ ነው» የሚለውን ፈሊጥ በመተው ክርስቲያን መሆናቸውን በእንደበትና በተግባር መግለጽ ይገባቸዋል። ካልሆነ መብራት አብርቶ ከመቅረዝ ላይ ሳይሆን በዕንቅብ ሥር ማለቀመጥ ይሆናል። ብርሃኑን ለማየት ለሚፈልጉ ሰዎች መብራት አይችልም። ክርስቶስን ባሳመኑ ለዎች መካከል በክርስቲያናዊ ሥነምግባር የማይመላለሱ ክርስቲያኖች በስም እንጂ በተግባር ለሌሎች ሊበራ የሚችል ብርሃን የላቸውም። ጨለማው እነርሱንም ውጦአቸዋል። ለሕዝቡ አቅጣጫን የምያሳይ ብርሃን በአካባቢው የለም ማለት ነው። በክርስቲያናዊ ሥነምግባር የሚመላለሱ ክርስቲያኖች ግን በሚሠሩበት አካባቢ ምንም ያህል ቢጠሉም በተራራ ላይ እንዳለች ከተማ ሲለወሩ አይችሉም። ለሕዝብ ሁሉ ምልክት ይሆናሉ፣ ሲመጣ ባለው ዓለም ብቻ ላይሆን በዚህም ሕይወት ከለማዩ አባታቸው ብድራታቸውን ያገኛሉ።

አንደ ክርስቲያን ማድረግ የሌለብን እንደሆነ አያወቅን ነገር ግን ምንም አይደለም ብለን ከክርስቲያናዊ ሥነምግባር የጎደለ በሥራ ቦታ የምናደርጋቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው? እነዚህንስ ነገሮች እንዴት ማስወገድ አንችላለን?

ክርስቲያኖች በሚሠሩበት የሥራ ቦታ መልካም ያልሆነ ድርጊታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ማጽደቅ የለባቸውም። በአብዛኛው ያላመኑ ሰዎች ምንም ላይለማቸው የሚያደርጉአቸው ነገሮች አሉ። ክርስቲያኖች አነዚያን ነገሮች ማድረግ አይገባቸውም። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ለክርስቲያን ተገቢ አይደለም፦

- ✓ ምንም አይደለም እየተባለ ትንሽ ሐሰት የሆነ ነገር መናገር ወይም ለሰዎች ማውራት፣
- ✓ ለአሠሪያቸው፣ ለአብሮ ሠራተኞች ወይም ለተገልጋዮች የገቡትን ቃል አለመጠበቅ፣
- ✓ በሥራ ቦታ አሠሪን፣ ሌሎች ሠራተኞችን ወይም ሌሎች ሰዎችን ማማት፣
- ✓ ከሥራ ለመቅረት አስበው ሳይታመሙ ታመምን ብለው ቤት መዋል፣ የሐኪም ማስረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ ደግሞ ከዘመድ ወይም ከጓደኛ ወይም በሌላም መልክ የሐኪም ፈቃድ ለማግኘት መሞከር፣
- ✓ የመሥሪያ ቤቱን ሰልክና ንብረት ያለአግባብ ለግል ጥቅም ማዋል፣ አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያኖችንም ጨምሮ የመሥሪያ ቤታቸውን ሰልክ ያለአግባብ ለራሳቸው ሲጠቀሙበት ይታያሉ። አንዳንዶች አንደ ሰልክ ቤት ሠራተኛ ቀኑን ሁሉ ስልክ እየደወሉ ይውላሉ።
- ✓ መሥራት ከሚችሉት በታች መሥራትና ሥራን መሰገምና ተገቢ ያልሆነ ውጤት ማምጣት፣

ከላይ የተጠቀሱትንና ተመሰሳይ ነገሮችን ማድረግ ለእግዚአብሔር፣ ለአሠሪ፣ ለተሰጣቸው ኃላፊነትና ንብረት እንዲሁም ለጊዜ ታማኝ አለመሆንን ያመለክታል። ክርስቲያኖች ለአሠሪያቸው ታማኝነታቸውን ከሚገልጡባቸው መንገዶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም፦

- የአሠሪን ማንኛውንም ንብረት ያለፈቃድ አለመጠቀም፣
- በተገቢው ጊዜ ተገቢ የሆነው ውጤት ማምጣት፣
- ችሎታን፣ ልምድንና አውቀትን ያለመሰገም ተጠቅሞ መሥራት፣
- ተገቢ የሆነውን የአሠሪን ትዕዛዝ ለማስተናገድ ዝግጁ በመሆን፣
- የሥራን ጊዜ በሚገባ ማክበር፣
- አሠሪው በምስጢር እንዲጠበቅ የሚፈልጋቸውን መረጃዎች በምስጢር መጠበቅ፣
- በኃላፊነት የተሰጣቸውን ማንኛውንም ነገር ለአሠሪው ጥቅም መጠቀም፣
- አሠሪውን ሲጎዳ የሚችል ማንኛውንም መረጃ ቶሎ መናገርና የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ናቸው።

እንግዲህ ክርስቲያኖች በሥራቸው በክርስቶስ ሳማኖት ለምች ብርሃን መሆን ከሚችሉባቸው መንገዶች አንዱ በታማኝነት የተሰጣቸውን ሥራ መፈጸማቸው ነው። በፈሪሃ አግዚአብሔር የሚመሳሰሉ የክርስቶስ ተከታዮች ታማኞች በመሆን ትውልድን ወደ ታማኝነት ጎዳና ማራመድ ይችላሉ።

ፍትሕ፦ ክርስቲያኖች በተለይ አሠሪ ወይም ተጠሪ ሆነው ሌሎች ሠራተኞችን የሚመሩ ሲሆን በአመራራቸው ውስጥ ፍትሕ ጎልቶ መታየት

ይኖርበታል። ሠራተኞች ፍትሐዊ የሆነ አመራርን ይፈልጋሉ። ይህን ዓይነት አመራር ለመስጠት ብቃት ያለው ደግሞ ፍትሕ ከተሞላበት ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት ያለው ሰው ነው። በዚህ ዓለም በተለይ ደግሞ በዓውዳችን በሥራ ቦታ ፍትሕ አይታይም። አሠሪዎች ወይም የሥራ መሪዎች መሥሪያ ቤቱ በሚተዳደረው መመሪያ ሳይሆን በሚፈልጉበት አቅጣጫ በመሄድ ሠራተኞችን ይበድላሉ፣ ተገቢ የሆነ ጥቅማ ጥቅሞችን ይከለክላሉ፣ ዝቅተኛ ክፊያ ይከፍሉአቸዋል፣ የደመወዝ ጭማሪ ይከለክላሉ፣ አንዱን ሠራተኛ ክሌላው በማበላለጥ ለአንዱ የማይገባውን ጥቅም ሲሰጡ፣ ሌላውን ደግሞ ያለአግባብ ሲበድሉና የመሳሰሉትን ኢፍትሐዊ ድርጊቶችን ሲፈጽሙ ይለማል/ይታያል።

አንዳንድ አሠሪዎች ለሠራተኛው የሚገባውን ጥቅማ ጥቅም ለመስጠት ከራሳቸው ንብረት እንደሚሰጡ ያህል በማሰብ ሠራተኛው ለመብቱ ሲጠይቅ ይከፋቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ ራሳቸው በትጋት ሳይሠሩ ሌላውን ሠራተኛ በማሠራት በሥራው ውጤት ግን ራሳቸውን ለማለተዋወቅ ይፈልጋሉ። አንዱ በሠራው ሌላው ይመሰገናል፣ ጥቅምም ያገኛል። ለአንድ የሥራ ቦታ/ደረጃ ወደዚያ ደረጃ ሲያድግ የሚችል ሠራተኛ መሥሪያ ቤት ውስጥ እያለ ዘመድ ወይም ጓደኛን ለመቅጠር ማስታወቂያ ያወጣል። ከዚያም መሥፈርቱን እንዲያመጣ በተፈለገው ዘመድ ሁኔታ በመቅረጽ ዘመዱን ይቀጥራል። እነዚህ ነገሮች ፍትሕ የጎደላቸው ሥራዎች ናቸው (ኤፌ.6፡9)። ክርስቲያን አሠሪ ወይም የሥራ መሪ እንዲህ ዓይነት ነገሮችን በፍጹም ማድረግ የለበትም።

> *ክርስቲያን የሥራ መሪ በሚመራበት ጊዜ የትኛውን ዓይነት የአመራር ዘይቤ መብት-መርሕ፣ ሥራ-መርሕ ወይስ ሰው-መርሕ ወይስ ሁሉንም መከተል አለበት? የትኛው መርሕ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው? ለሠራተኛውና ለሥራው ስኬት ይጠቅማል?*

ክርስቲያን አሠሪ ወይም የሥራ መሪ ሠራተኞች መብታቸውን በማክበር መምራት ይጠበቅበታል። ከሥራ ይልቅ ለሠራተኞች ለብዓዊ መብቶች ቅድሚያ መስጠት ይኖርበታል። ሥራ የሚሠራው ለሰው በመሆኑና ውጤታማ ሥራ የሚሠራው ደግሞ አመራሩ ለሠራተኞች ዋጋ እንደሚሰጣቸው ሲረዱ በመሆኑ ነው። ሠራተኞችን በክርስቲያናዊ ትሕትናና በጎነት መያዝ መልካም ነው። በክርስቲያን የሥራ መሪና ክርስቲያን ባልሆነው የሥራ መሪ መካከል ለሠራተኛው ፍትሕን በማድረግ ልዩነት ከሌለ የክርስቶስ ተከታይ መሆን ወዴት አለ? ያሰኛል። ለክርስቲያን አሠሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ ምክርና ተግሳጽ አለው (ያዕ5:1-6፣ ቆላ3:24)።

ክርስቲያን የሥራ መሪዎች የሠራተኞችን መብት ማክበርና ማለክበር እንዳለባቸው ቢታወቅም እንኳን በዓለማዊ መሥሪያ ቤት የሥራ መሪ ሆነው በቤተክርስቲያንና በክርስቲያናዊ ድርጅት ውስጥ በተለያየ ደረጃ የሥራ መሪ ሆነው የሚመሩ ክርስቲያኖች የሠራተኞችን መብት እንደሚገባ አያከብሩም። ሠራተኛው ለመብቱ ጥያቄ ሲያቀርብ ክርስቲያን አሠሪዎች «ብርቱ ክርስቲያን ለመብቱ አይከራከርም፣ ለእግዚአብሔር ብቻ ይናገራል እንጂ» እያሉ ዝም ለማሰኘት ጥረት ያደርጋሉ። ሠራተኛው ደግሞ በመንፈሳዊ መንገድ በመሄድ «እኛ ክርስቲያኖች አይደለንም ወይ? ይህ ነገር

ሰምን እንዲህ አልተደረገም» ብሎ ሲጠይቅ የመሥሪያ ቤቱን ደንቦች መጥቀስ ይጀምራል። ክርስቲያን አሠሪ በተሰይ ክርስቲያኖችን ሲመራ ክርስቲያኖች የመብት ጉዳይ ሲያነሱ በመንፈሳዊ አቀራረብ በመቅረብ ዝም ያሰኛቸዋል። እነርሱ በመንፈሳዊ አቀራረብ ሲቀርቡት ደግሞ «ዓለማዊ» ይሆንባቸዋል። ክርስቲያኖች በክርስቲያኖች ላይ በደል ለመፈጸም መንፈሳዊ አቀራረብ ወይም ቋንቋን ሲጠቀሙ ከማየት በላይ የሚያሳዝን ምን አለ? እንዲህ እየተደረገ ክርስቲያን እንዴት የዓለም ብርሃንና ጨው መሆን ይችላሉ? ስሌላው መልካምነታቸው ከመውጣቱ በፊት ለእርስ በርሳቸው መልካምነታቸው መታየት እይኖርበትምን?

> *ክርስቲያን የሥራ መሪ/አሠሪን ከሌሎች ካላመኑ የሥራ መሪዎች/አሠሪዎች ልዩ የሚያደርጉት ዋና ዋና መለያ ምልክቶች ምንድናቸው? እነዚህን ባሕርያት እንዴት ማሳደግ ይቻላል?*

እንግዲህ ክርስቲያን አሠሪዎች ለሠራተኞች የሚገባውን ነገር ሁሉ በማድረግ በሁሰንተናዊ ሕይወታቸው ማደግ እንዲችሉ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። በእነርሱና በሠራተኞች መካከል ባለው ግንኙነትና አሠራር ሁሉ ፍትሕ መታየት አለበት። እግዚአብሔር የፍትሕ አምላክ በመሆኑ እርሱን የሚከተሉ ሰዎችም ከሌሎች ሰዎች ጋር ባላቸው ማንኛውም ግንኘ ነት ፍትሕን በተግባር ማሳየት መለያቸው ሲሆን ይገባል።

ሥራን እንደ አገልግሎት መቁጠር:- ሥራን መንፈሳዊና ዓለማዊ እያሉ መከፋፈል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም። ዶ/ር ክሳውድና ዶ/ር ታውንሴንድ የተባሉ ክርስቲያን ጸሐፊዎች ሥራ መንፈሳዊ እንደሆነና ሰባሕርይ ቀረጻም አስፈላጊ እንደሆነ እንዲህ በማለት ተናግረዋል።

> ሥራ መንፈሳዊ ነው። በሥራችን አግዚአብሔርን ወደ መምሰል እናድጋለን፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱ ሠራተኛ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ፈጣሪ፣ አሳዳጊ፣ ባለእደራና ፈዋሽ ነው። ክርስቲያን መሆን ማለት በሰብዓዊ ማህበረሰብ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ሠራተኛ መሆን ነው። ... ሥራ ለዘላለም እንድንሠራው ለሚጠብቀን ሥራ ባሕርይያችንን እየቀረጸ የሚያዘጋጀን ሥፍራ ነው።[13]

በዚህ አሳብ መሠረት ሥራ እግዚአብሔር በስጠን ስጦታ ሠራተኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን ምሳሌነት በመከተል መሥራት፣ መምራት፣ መፍጠር፣ ማሳደግ፣ ባለአደራነትን መፈጸምና ፈውስ የሚያስፈልገውን መፈወስ ነው። እነዚህንም ነገሮች በመሥራት ሕይወታችን እያደገና ባሕርያችንም እግዚአብሔርን በመምሰል ያድጋል። በዚህ ዓለም ሥራ መሥራት ባሕርያችንን በመቅረጽ በሚመጣው ዓለም ለዘላለም ለሚሠራው ሥራ ያዘጋጀናል።

ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነ ሥራ በሚሠራበት ጊዜ ሥራውን እንደ አገልግሎት ሲያስብ ለሥራው የሚኖረው አመለካከትና

[13] Cloud, H. & Townsend, J. (1992). *Boundaries*. Zondervan Publishing House, PP.194-195.

የሚያሳየው ትጋት የተለየ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች ሥራ ሲሠሩ ለአሠሪያቸው ብቻ እንደሚሠሩ ሳይሆን ለክርስቶስ እንደሚሠሩ በማሰብ በትጋት መሥራት እንዳለባቸው ተመልክተናል (ኤፌ.6:5-8፣ ቆላ.3:23-24፣ 1ጢሞ6:1-2)።

በመሠረቱ አሳብ ደረጃ የክርስቶስ ወንጌል የሰዎችን ሕይወት ከሰወጠ ሰዎች ለሰሥራ ያላቸውም አመለካከት ይሰወጣል። በሥራ ውስጥ ድካም እንዳለ የታወቀ ነው። ለመልካም ነገር መድከም ግን ውጤት አለው። ክርስቲያኖች ሆነው ለሰሥራ ያላቸው አመለካከትና በሥራ ቦታ የሚያሳዩት ባሕርያት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆነ የሰዎቹን በወንጌል መሰወጥና የአእምሮአቸውን መታደስ መጠርጠር ያስፈልጋል። ሰዎች ለለአንድ ነገር የነበራቸው አመለካከትና ባሕርይ ቶሎ ብሎ እንደማይለቃቸው ቢታወቅም ቀስ በቀስ የወንጌል በሕይወታቸው ፍሬ ማፍራት ወደ እግዚአብሔር አሳብ እንዲያደርሳቸው ይጠበቃል። ይህ ፍሬ በሥራም ላይ መታየት እንዳለበት መታወቅ አለበት።

ክርስቲያኖች ለሰሥራ ያላቸው አመለካከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳይሆን ያደረገው አንዱ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰጠው ሚዛን ያልጠበቀ መንፈሳዊ ትምህርት ነው። ቤተክርሰቲያን በዓውዳችን ክርሰቲያኖች ለሰሥራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ እያበረከተች ያለው አስተዋጽእ ከቁም ነገር ገብቶ የሚቆጠር አይመስልም። ቤተክርስቲያን በምትሰጣቸው መንፈሳዊ ትምህርቶች ክርሰቲያኖች ለሰሥራ ያላቸው ግንዛቤ እንዲዛባ ማድረግዋን ከሚታየው ተጨባጭ ነገር በመነሳት መናገር ይቻላል። ክቤተክርስቲያን ምሰባክ የሚሰማው ሥራ ዓለማዊና ምድራዊ እንደሆነ በተቃራኒው ደግሞ መንፈሳዊ እገልግሎት መስጠት ደግሞ የተቀደሰ ሥራና መንፈሳዊ እንደሆነ ነው። ከሥራዎች ሁሉ የሚበልጠው መንፈሳዊ ሥራ መሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ይነገራል። በእርግጥ ይህ አሳብ በአንድ በኩል እውነትነት ቢኖረውም ሰዎች ግን ለኑሮአቸው በርትተው እንዳይሠሩ እንቅፋት ሲሆን እይገባም።

በቤተክርስቲያን በኩል የሚታየው ሌላው ችግር ደግሞ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰጠው መንፈሳዊ ትምህርት ለዎች በዚህ ዓለም በአቋራጭ መንግሥተ ሰማያትን በምድር እንዲኖሩ የሚያደፋፍር ነው። የዘመኑ ክርስቲያኖች በቤተክርስቲያን ውስጥ በአምልኮ ላይ ላሉ መንግሥተ ሰማያት የገቡ ይመስላቸዋል። በስሜታቸው ነፋስ ላይ ሲለንፉ ውሰው የዕለቱ የጉባኤ አምልክ ተጠናቅቆ ከቤተክርስቲያን ሕንጻ ሲወጡ ደግሞ ወደ ምድር ይመለሱና ተመልስው በቀድሞው ሕይወታቸው ውሰጥ ይገባሉ። መንፈሳዊ ትምህርቱ እንደ ሕመም ማስታገሻ መድኃኒት ሆኖላቸዋል። ቤተክርስቲያን መሄድ ለጊዜው ከዚህ ዓለም ችግር «ነጻ» ሆነው በስሜታቸው እፎይታን የሚሹበት መንገድ ሆኗል።

ከዚህም በተጨማሪ በቤተክርስቲያን የሚሰጠው መንፈሳዊ ትምህርት ክርስቲያኖች ከሚኖሩበት ተጨባጭ ዓለምና ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ባለመሆኑ ምዕመናን ቤተክርሰቲያን ሲሄዱ የዕለት ኑሮአቸውን በምን ዓይነት ሁኔታ በመኖር ወደ እግዚአብሔር አሳብ ሙላት መድረስ እንደሚችሉ በቂ እውቀት እያገኙም። ምዕመናን ያሉበት ሁኔታ በድህነትና በጉስቁልና ሆነው ሳሰ የሚሰበከው ግን ከድህነትና ጉስቁልና እንዴት መውጣት እንደሚቻል ሳይሆን ሰለበረከትና የድል ሕይወት ነው። ምዕመናን ቤተክርስቲያን ውስጥ

ሊሆኑ ስለድህነታቸው እንዲያስቡም አይፈለግም፣ እርሱን መርሳት እንዳለባቸው ይነገራቸዋል። የሚሰበከው ስለምድር ሳይሆን ስለሰማይ ነው። እንዴት ከምድር ተነስቶ ለሰማይ መድረስ እንደሚቻል ግን ተጨባጭ የሆነ ምክርና መመሪያ አይሰጥም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ምዕመናን በእርሱ ላይ እምነት ቢኖራቸው እግዚአብሔር ሁሉን ነገር መልካም እንደሚያደርግ ተደጋግሞ ይነገራል። በዚህ ሂደት ማለትም ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ሲታመኑና እግዚአብሔር ለመባረክ ሲያስብ በሚለጠው ትምህርት ውስጥ ለብዓዊ ድርሻ ምን እንደሆነ እይጠቀስም። ይህን መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰማው ምዕመን ለጊዜው እውነት ነው ብሎ ተቀብሎ ወጣ ብሎ ከተጨባጩ ዓለም ጋር ሲገናኝ ከፉውን ዓለም እንዴት ማሸነፍ እንደሚችል ምንም ዋስትና የለውም። ኑሮውን ለማሻሻል እንድ እውነት የተማረ መስሎት ነበር፣ ነገር ግን የሰማው ትምህርት ከሕይወት ጋር ተዋሕዶ የሚጠቅመው ሳይሆን ሰጊዜው ስሜትን የሚያግል ሆኖ ያገኘዋል። መንፈሳዊነቱ ሁለንተናዊ ሕይወቱን ሊሰውጥ አይታይም።

ምዕመናን በቤተክርስቲያን የሰሙትን ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ ሊያስቡ ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ምላሾችን ይሰጣሉ። የመጀመሪያው የሰሙት ትምህርት በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ተግባራዊ ሊደረግ የማይችል እንደሆነ በማሰብ መንፈሳዊውንና ዓለማዊውን የሕይወት ገጽታ በመለየት ሁለቱን በማለያየት ለመኖር ጥረት ማድረግ ነው። ሁለተኛ ው ደግሞ የሰሙት ትምህርት ቅዱስና እውነተኛ ትምህርት ሆኖ እያለ በሕይወት ተግባራዊ እንዳይሆን ሰሚው ኃጢአተኛ በመሆኑ ወይም እምነት ስለሌለው እንደሆነ በማሰብ ራስን እየከነኑ መኖር ነው።

> *ክርስቲያኖች በዓለም የሚሠሩትን ሥራዎቻቸውን እንደ አገልግሎት በመቁጠር ለእግዚአብሔር ክብር በሚሆን መልኩ እንዲሠሩ ቤተክርስቲያን እንደ ተቋም ምን ማድረግ ይጠበቅባታል?*

ቤተክርስቲያን ምዕመናንን ስለሥራ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ ትምህርትና ምክር ልትሰጣቸው ይገባታል። ሆኖም ግን ስለሥራ በምታስተምርበትና በምታነሳበት ጊዜ ደግሞ ከሁለት ጽንፈኛ አመለካከቶች መጠበቅ ይኖርባታል። የመጀመሪያው ሰሥራ ከፍተኛ ሥፍራ በመስጠት እግዚአብሔር በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የሚኖረውን የአምሳክነት ሥፍራ አንዳይወስድ ነው። ክርስቲያኖች እንደ ማንኛውም ዓለማዊ ሰው የሕይወትን ደስታና እርካታ ማግኘት የሚችሉት በሥራ ብቻ እንደሆነ እንዲያስቡ የሚጋብዝ ትምህርት መስጠት የሰበትም። ክርስቲያኖች ለሥራ ክብርን የሚሰጡት መንፈሳዊነታቸውን በመጠበቅ ሲሆን ይገባል። ሥራውንም መሥራት የሚገባቸው ክርስቲያን ሆነው ነው። በሥራ ሀብትን ማግኘት፣ በትምህርት መጥቆ መሄድ የሚበረታታ ጉዳይ ነው። ቤተክርስቲያንም ምዕመናን በማንኛውም መስክ ክርስቲያኖች ቀድመው እንዲገኙ ማስተማር፣ ማደፋፈርና መደገፍ ይገባታል። ግን ስኬት መልካም ጣዕም እንዲሁም ዘላቂነት ያለው እርካታና ደስታ የሚኖረው ከክርስቶስ ጋር እንደሆነ ደግሞ እበክሮ ማሳየትና ክርስቲያኖች ስኬት ሲያገኙ እንዴት ክርስቶስን አክብረው መኖር እንደሚችሉ ማሳየት ተገቢ ነው።

ሁለተኛው ጽንፈኛ አመለካከት ደግሞ የብልጽግና ወንጌል ነው። ክርስቲያኖች ሥራ ከሠሩ በሥራቸው ስኬትን ሊያገኙ ይችላሉ። በክርስቶስ ማመን ግን በራሱ ሰዎችን ባለጠጋ አያደርጋቸውም። ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ላይ እምነት ቢኖራቸው ምድራዊ በረከትንም ማግኘት ይችላሉ፣ ክርስቲያን ድሃ መሆን የሰበትምና የመሳሰሉት አሳቦች መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳተ ሁኔታ ከመተርጎም የመነጩ አሳብ ነው። በዓውዳችን ምስባኮችም በአብዛኛው የሚነገረው መንፈሳዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም ምድራዊ በረከቶችን ማግኘት ነው። «እግዚአብሔር መኪና አንዲሰጠኝ ሦስት ዓመት ጸሰይኩና ጌታ ጥሩ መኪና ሰጠኝ» «ሰእገልግሎት ሙሉ ጊዜዬን ከመስጠቴ በፊት ቤት አልነበረኝም፣ ሰእገልግሎት ከወጣው በኋላ ግን እግዚአብሔር ግማሽ ሚልዮን የሚያወጣ ቤት ሰጠኝ» የሚሉና የመሳሰሉ አባባሎች ምዕመናን እግዚአብሔርን ቢጠይቁ የሚፈልጉትን ነገር እንደሚቀበሉ እንዲሁም ሠርቶ ከማግኘት ይልቅ በትጋት መጸለይ የተሻለ ውጤት እንዳለው ያመለክታል። እግዚአብሔር የምንፈልገውን ነገር ሳይሆን የሚያስፈልገንን ነገር ይሰጠናል። ያለ ሥራ ቁጭ ብሎ ከመጸለይ ይልቅ እየጸለዩ መሥራት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

ቤተክርስቲያን ምዕመናን ስለሥራና ስለሀብት ሊኖራቸው የሚገባቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ዘወትር በትጋት ማስተማር ይገባታል። ወደ ሥራ ዓለም የሚገቡ ወጣቶች እንዴት እግዚአብሔርን የሚያስደስትና ከችሎታቸው ጋር የሚዛመድ ሥራ መያዝ እንደሚችሉ ምክርና ትምህርት በመስጠት አቅጣጫ ማሳየት ይጠበቅባታል። የቤተክርስቲያን መሪዎች ሚዛኑን የጠበቀ መልካም የሥራ ሥነምግባር ያላቸው ምዕመናን ሊሆኑ ይገባቸዋል። በመንፈሳዊና የሥራ ሥነምግባራቸው የተመሰከረላቸው ምዕመናን ሰሌሎች ማስተማር የሚችሉበትንም ሁኔታዎች ማመቻቸት ተገቢ ነው።

ክርስቲያኖች ስለሥራ ያላቸው አስተሳሰብና የሚያደርጉትን ነገር እንደ እግዚአብሔር ቃል መሆኑን ለመፈተሽ ራሳቸውን እንዲፈትሹ የሚረዱ አሳቦች እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል። እነርሱም፡-

- ✓ ለሥራ ያነሳሳቸውና ሥራ የሚሠሩት በምን ምክንያት ነው? ገንዘብ ለማግኘት፣ ኃላፊነት ስለሆነ፣ በፍርሃት መንፈስ ተይዘው ወይስ ለእግዚአብሔር ክብርን ለማምጣት ወይስ ሁሉም?
- ✓ ሥራ ለምሥራት ኃላፊነት ሲሰጣቸው ከሥራው ቶሎ ለመገላገል እቋራጭ መንገዶችን ይፈልጋሉ ወይ? እንድን ሥራ በእቋራጭ መንገድ ለመሥራት ሲታሰብ ውጤታማ ሥራ ሳይሠራ ይችላል። ሥራው ቶሎ ካለቀ ደግሞ የተረፈው ጊዜ ምን ላይ ይውላል? ጊዜን በጥሩ ሁኔታ ለመጠቀም ሥራዎችን ሁሉ ቶሎ ቶሎ ብሎ መሥራት የሚደገፍ ነው። ሆኖም ቶሎ ቶሎ ሠርቶ ለመገላገል ማሰብ ትክክለኛ ዓላማ እይደለም።
- ✓ በሥራ ላይ የሚከሰቱ ስህተቶችን እንዴት ያስተናግዳሉ? ማንኛውም ሰው በሥራ ላይ ስህተት ሊፈጽም ይችላል። ምዕመናን በሥራ ላይ ለስህተት ሊሠሩ በተለይ ስህተታቸው ሌሎች ሰዎችን የሚጎዳ ሆነው ሲያገኙት ምን ዓይነት እርምጃ ይወስዳሉ? ስህተቱ በሕይወታቸው ወይም በሥራቸው ዋስትና ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በመፍራት ይደብቃሉ? ወይም ሰዎች ምን ይሉኛል፣ ስህተቴን አምኜ እንዴት እዋረዳለሁ? በማለት ለህተታቸውን ለመሸፈን ይሞክራሉ?

- ✓ ከአሠሪያቸው ወይም ተጠሪያቸው ጋር ግጭት ውስጥ ሲገቡ ምን ያደርጋሉ? ስለአሠሪው ወይም ተጠሪው ክፋትና ስህተት ስሌሎች ሰዎች ያወራሉ ወይስ ቀጥታ ወደ የሚመለከተው በመሄድ ያነጋገሩታል?
- ✓ ሳይታመሙ ነገር ግን ሥራን ላለመሥራት በሕመም በማሳታከክ ይቀራሉን?
- ✓ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሳይስጡ ሥራውን ይተዋሉን?

በአጠቃላይ አያንዳንዱ ክርስቲያን እንደሚኖርበት ዓውድ ስለሥራ የሚኖረው አመለካከት የተለያየ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ስንመለከተው ሥራ የሰው ልጅ ስራሱ የፈጠረው ክስተት ሳይሆን ከእግዚአብሔር አምላክ ዘንድ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። እግዚአብሔር ሰሰው ልጅ የሚሰጠው ትዕዛዝ ደግሞ ተግባራዊ ሲሆን ሰውን በሁለንተናዊ መልኩ የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ነገር የለውም። አለመሥራት በእግዚአብሔር ዘንድ የማይፈለግ ባሕርይ ሲሆን ሰለው ልጅ መርገምን እንጂ በረከትን አያመጣም። የስንፍና ፍሬው ድህነትና ጉስቁልና ነው።

በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ዳግም የተወለዱ ምዕመናን ስለሥራ ያላቸው አመለካከትና በሥራ ላይ የሚያሳዩት ባሕርይ የተለወጠ ሊሆን ግድ ነው። ምክንያቱም ዳግም ልደት በሁለንተናዊ ሕይወታችን ላይ መልካም ለውጥ ሊያመጣ ይገባል። ይህ ለውጥ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተጠቀሱትን ትዕዛዛትን ተግባራዊ በማድረግ ይገለጣል። ለክርስቲያን መሥራት መብት ሳይሆን ግዴታ ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ «ሊሠራ የማይወድ አይብላ» (2ተስ3:10) በማለት ስለሚያዝ ነው። ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነውን ማንኛውንም ሥራ መሥራት ይችላል። በማንኛውም በተሠማራበት ሥራ ላይ ክርስቲያን ታታሪ፣ ታማኝ፣ ፍትሕን የሚያደርግና ሥራውን እንደ አገልግሎት በመቁጠር ለእግዚአብሔር ክብር የሚሠራ ሊሆን ይገባል።

ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጠውን ጊዜ በመልካም ሁኔታ በመጠቀም ሥራውን በትጋት መሥራት አለበት ሊባል ግን ሰራሱ ሕይወት፣ ለቤተሰቡና ለመንፈሳዊ አገልግሎት ጊዜ መስጠት የለበትም ማለት አይደለም። በሥራ፣ በግል ሕይወትና በመንፈሳዊ አገልግሎት መካከል ሚዛን የጠበቀ አሠራር መኖር አለበት። ይህ እንዴት መሆን እንደሚችል በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ በስፋት እንመለከታለን።

ምዕራፍ 10.

ሥራን፣ ክርስቲያናዊ ሕይወትንና መንፈሳዊ አገልግሎትን በሚዛን መጠበቅ

ሥራ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጅ የተሰጠ መልካም ኃላፊነት እንደሆነ ተመልክተናል። ሥራ መልካም ቢሆንም ገደብ ሊኖረው ይገባል። ለሰዎች ፍሬያማ የሆነ ሁለንተናዊ ሕይወት እንዲኖራቸው ከፈለጉ ለሥራና ለአረፍት ጊዜ መመደብ ይጠበቅባቸዋል። እንደ ክርስቲያን በቀን ወይም በሳምንት ለንት ሰዓት መሥራት አለብን? ለዚህ ጥያቄ እያንዳንዱ ሰው የሚለጠው ምላሽ የተለያየ እንደሚሆን የታወቀ ነው። አንዳንዶች ሥራን ከመጠን በላይ በመውደድ እንደ ጣዖት በማምለክ ዘወትር በሥራ ሊጠመዱ ሌሎች ደግሞ ሊያመልኩት ሌሎች ደግሞ ሥራን ከመጠን በላይ ከመጥላታቸው የተነሣ ከሥራ መቅረት ወይም ሥራ መሥራትን ማስወገድ የሚችሉበትን ማንኛውንም አማራጭ መንገድ ለመጠቀም ይሞክራሉ። በዓውዳችን ክርስቲያኖች ለስሥራ ያላቸው አመለካከት ሌሎች ሰዎች ለስሥራ ካላቸው አመለካከት እምብዛም የተለየ እንዳልሆነ ማስብ ይቻላል። ሁለቱም ዓይነት ሰዎች ባመኑትና ባላመኑት ውስጥ እንደሚገኙ የታወቀ ነው። ከዚህ በላይ ለስሥራ የተጠቀሱት ሁለቱ አመለካከቶች ጽንፈኛ ናቸው። በሁለቱም መካከል ሚዛን ሊኖር ይገባል።

ሥራና አረፍት

መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ ሥራን በትጋት መሥራት እንዳለበት ቢያስተምርም በሥራ መካከል አረፍት አስፈላጊ እንደሆነም በግልጽ ይናገራል። ለለሆነም ሥራና አረፍት ተያይዘው የሚሄዱ ነገሮች ናቸው። ከሥራ በኋላ አረፍት ሊኖር እንደሚገባ እግዚአብሔር በራሱ ምሳሌ አሳይቶናል። እግዚአብሔር ኃይሉ ባይደክምም፣ የሚፈልገውን ነገር ለማድረግ የሚችል ቢሆንም ግን ሥራዎቹን የሚሠራው በዕቅድ ነው። በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ደረጃ በደረጃ ማስትም በአንድ ጊዜ አንድ ነገርን እየፈጠራቸው ፍጥረታትን ወደ ሙላት አንዳመጣቸው እንመለከታለን። በወቅቱ መሥራት የሚገባውን ሥራ ከጨረሰ በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር እንዳረፈ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እግዚአብሔር ሰምን ከሥራው አረፈ? እግዚአብሔር ከሥራው ያረፈው ለለደከመው አይደለም። ነገር ግን በጊዜው መሥራት ኖሚገባውን ሥራ በማጠናቀቁና እርሱ ከሥራው እረፍት በማድረግ የሰው ልጅም የእርሱን ምሳሌ በመከተል ለተወሰነ ጊዜ ሥራን ሠርቶ ከዚያ ደግሞ ለጥቂት ጊዜ ማረፍ እንደሚገባው ለማሳየት ነው።

እግዚአብሔር ከሥራው ያረፈበትን ቀን ሰንበት ብሎ ለየመው። «እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በለባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በለባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። እግዚአብሔርም ለባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፎአልና» (ዘፍ.2:2-3)። እግዚአብሔር ከሥራው ሲያርፍ ምን አደረገ? የአረፍት ጊዜውን በምን ላይ አዋለ? እግዚአብሔር ያረፈው በሠራው ሥራ የድካም መንፈስ ይዞት ወይም ለውነቱ ዝሎ ሳይሆን የሠራውን ሥራ አይቶ ለመደሰት ነው። ለለዚህ እግዚአብሔር በዚህ የለንበት ቀን ለለሠራው ሥራ እያለበ ይደነቅ ነበር ማለት ይቻላል።

አረፍት ለምች ለራሳቸው የፈጠሩት ጊዜ ሳይሆን እግዚአብሔር ለስምች ያዘዘው አሳብ ነው። ሠርቶ ማረፍን ያስተማረው እግዚአብሔር ራሱ ነው። እግዚአብሔር ፍጥረተ-ዓለምን ፈጥሮ በየቦታቸው አድርጎ ሂደቱ እንዲቀጥል ካደረገ በኋላ ከሥራው ዐረፈ። ይህ የለንበት ቀን የተባረከና የተቀደስ ቀን ነው። በሳምንት ውስጥ ለድስት የሥራ ቀናትና አንድ የእረፍት ቀን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለስው ልጅ ተስጥቶአል። እግዚአብሔር ለሕዝቤ አለራኤል በስጠው ሕግ ውስጥም ሕዝቡ የስንበትን ቀን እንዲያክብር ትዕዛዝ ለጥቶአቸዋል (ዘጸ 20፡11)። በዚህ ዕለት ማንኛውም የቤተስብ አባል ሥራ መሥራት የለበትም። እግዚአብሔር ለምች ለድስት ቀን ሠርተው አንድ ቀን ግን እንዲያርፉ ያዘዘው ለምንድነው?

> ለምች ለጉሮአቸው የሚያስፈልገውን ነገር ለማግኘት ለድስት ቀን ሲደክሙ ከርመው በሰንበት ቀን ደግሞ ስለአምላካቸው ሥራ እንዲያስቡና እርሱን እንዲያመስግኑና እንዲያመልኩ፣ የሚያስፈልገውን ሥራ ለመሥራት ለድስት ቀን በቂ ስለሆነና ለሚቀጥለው የሥራ ቀናት ደግሞ በአዲስ መንፈስና ኃይል ለመዘጋጀት ጊዜ መውለድ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ከርስቲያኖች በሥራ መትጋት እንደሚገባቸው ተጠቅሷል። እረፍት የሚገባው ጊዜውን በሚገባ ተጠቅሞ ተገቢ የሆነ ሥራ ለሠራ ለው ብቻ ነው። አንድ ለው ሳይሠራ ለለእረፍት እንዴት ማንሣት ይችላል? ለለዚህ እረፍት ሊታለብ በቅድሚያ መምጣት ያለበት ሥራ ነው። ሠርቶ ማረፍ አምላካዊ ትዕዛዝ ነው። ሳይሠሩ መዝናናት መፈለግ ግን የስንፍና አንዱ ምልክት ነው።

በትጋት ለሚሠሩ ለምች ግን እረፍት ያስፈልጋቸዋል። ለምች ሲፈጠሩ እረፍቶ ማድረግ እንደሚገባቸው ሆነው ተፈጥረዋል። ለለዚህ ያለእረፍት ጤናማ የሆነ ሕይወት መምራት አይቻልም። ያለእረፍት ለሥራ ብቻ ተጠምዶ መኖር ማለብ ለብዓዊ ላለመሆን ጥረት ማድረግ ሲሆን ውጤቱ ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም። ለሥራ የሚለጠው ሥፍራ በሚዛን ካልሆነ ለለው ልጅ ሕይወት የሚለጠውን እርካታና ደስታ መለጠት አይችልም። ሥራ እንደ ሱስ ሆኖ ሕይወትን ሊያጠፋ የሚችል ባሕርይ አለው። አንዳንዶች ሥራን እንደ ጣዖት አድርገው ለራሳቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ለእግዚአብሔር መለጠት የሚገባቸውን ጊዜ ባለመለጠታቸው ሕይወታቸው ይናጋል። ክርስቲያኖች ሥራን አያመልኩትም። ለክርስቲያን ሥራ በእርሱና በአምላኩ መካከል መግባት የለበትም። ከዚያም ለልፎ ሥራ ቤተሰብንና ትዳርን ለማፍረስ ምክንያት ሊሆን አይገባም። ሥራ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚያዛባ እንዲሁም ትዳርንና ቤተሰብን ለማፍረስ ምክንያት የሚሆን ከሆነ ምኑ ተወደደ?

ለሥራ ምን ያህል ትኩረትና ጊዜ መለጠት አለበት? በአንድ በኩል ለሥራ ትጋትን ማሳየት ሲጠበቅ በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ አገልግሎትና ቤተሰብ መረሳት የለባቸውም የሚለውን አሳብ በሚዛን መጠበቅ የክርስቲያን የሁልጊዜ ፈተና ወይም ውለጣዊ ትግል ነው። ብአብዛኛው ወደ አንዱ አቅጣጫ ማዘንበል ይታያል። በሥራ፣ በቤተሰብና መንፈሳዊ አገልግሎት መካከል ያለውን ሚዛን መጠበቃቸውን ለመፈተሽ ክርስቲያኖች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራሳቸውን መጠየቅ ይችላሉ፦

- ✓ የምሠራው ሥራ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳላነብ፣ እንዳልጸልይ፣ ቤተክርስቲያን ሂጀ እንዳላመልክ ወይም መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳልሰጥ እያደረገኝ ነው ወይ?
- ✓ አብዛኛውን ጊዜ የማስበው ለለምንድነው? ብዙ ጊዜ ከአለምሮዬ የማይጠፋው አሳብ ምንድነው? ሥራ፣ ቤተሰብ፣ መንፈሳዊ አገልግሎት ወይስ ሌላ?
- ✓ ለሥራ ወይም ለመንፈሳዊ አገልግሎት የምለጠው ጊዜ ክትዳር ጓደኛ ዬና ከቤተሰቤ ጋር ባለኝ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አላድርል ወይ?
- ✓ ሥራ በማልሠራበት ጊዜ ምን ዓይነት ለሜት ይለማኛል? ከሥራ እረፍትን ላደርግ በውስጤ የመረበሽና የመጨነቅ ለሜት ይለማኛል ወይ? እና የመላለሱትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ለሥራና ለሌሎች ኃላፊነቶች ተገቢው ሥፍራ መለጠቱን መፈተሽ ይቻላል።

ከላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች «አዎን» የሚል ምላሽ ከተለጠ ሥራ ሕይወትን እያፈረሰ እንጂ እየገነባ እንዳልሆነ መመልከት ቀላል ነው።

ሥራና መንፈሳዊ አገልግሎት

ሥራንና መንፈሳዊ አገልግሎትን በተመለከተም ሚዛን መጠበቅ አለበት። ሆኖም ይህን በተመለከተ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ አመለካከቶች ተንጸባርቀዋል። በመካከለኛው የቤተክርስቲያን ታሪክ ቶማስ አኩኒስ የተባለ የሥነመለኮት ምሁር ለተለያዩ ሥራዎች ደረጃ ለጥቶአቸው ነበር። በዚህ መሠረት እርሻ የቀዳሚነት ሥፍራ ሲይዝ የዕደ ጥበብ ሥራዎችና ንግድ በሁለተኛና በሦለተኛ ደረጃ ላይ ተመድበው ነበር። እነዚህ ሁሉ ሥራዎች ግን ዓለማዊ ሥራዎች ይባሉ ለለነበር መንፈሳዊ ሥራ ማለትም የቤተክርስቲያን ሥራ ከእነዚህ ሥራዎች የላቀ እንደሆነ ይታመን ነበር። በቤተክርስቲያን በተለይም በገዳም ውስጥ መእለይና ለለእግዚአብሔር ማለላለል ወደር የለሽ ሥራ በመሆኑ ከሁሉም ሥራዎች ልቆ ይታይ ነበር። ሥራ መንፈሳዊና ዓለማዊ በመባል ለሁለት ይከፈል እንጂ በማንኛውም ዓለማዊ ሥራ ላይ የተሠማራም ክርስቲያን ያን ሥራ ያገኘው በእግዚአብሔር ጥሪ እንደሆነ ለለሚታሰብ እያንዳንዱ ክርስቲያን ሥራውን በትጋት እንዲሠራና የሚሠራውንም ሥራ ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ ለልጆቹ ማስተማር እንደሚገባ ይበረታታ ነበር።

በዚያን ዘመን ለምች ሥራን የሚሠሩት ለዕለት ኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለማግኘት እንዲሁም ያለሥራ መቀመጥን ለማስወገድ ነበር። ክርስቲያን ያለሥራ ቢቀመጥ ወደ ኃጢአት የሚያመራውን ነገር ያስባል እንዲሁም ያደርጋል ተብሎ ለለሚታመን ክርስቲያኖች ሥራን እንዲሠሩ ይደረጋል። ይህም የሚያሳየው ሥራ ለኑሮ የሚሆን ነገር ለማግኘትና ከኃጢአት እንዲከላከል በማሰብ እንጂ ሥራ በራሱ እርካታን ወይም ደስታን እንደሚሰጥ በማለብ አይሠራም ነበር።

ክርስቲያኖች በማንኛውም ሥራ ላይ ተሠማርተው በሚሠሩበት ወቅት ሥራቸውን እንደ አገልግሎት መውለድ ይችላሉ። እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነ ማንኛውም ሥራ እንደ አገልግሎት ይቆጠራል። ይህም የሚሆነው ሠራተኛው ሥራውን ለእግዚአብሔር ክብርን እየለጠና

ለሰዎች ጥቅም እንዲሆን አውቆ ሲሠራው ነው። በእንድ በኩል ሥራን እገልግሎት ወይም ሰጥቅም ማግኛ የሚሠራ ሥራ የሚያደርገው ሥራውን የሚሠራው ሠራተኛው እንደሆነ መናገር ይቻላል። የሚሠራውን ሥራ እንደ ገቢ ማግኛ ብቻ አድርጎ የሚያስብ ሰው ሥራው ለእርሱ ጥቅም የሚያመጣ ብቻ ስለሆነ ሥራ ነው እንጂ አገልግሎት አይደለም። ምክንያቱም በሥራው ውስጥ ጎልቶ የሚታየው የሠራተኛው ጥቅም ነው። ሥራውን እንደ እገልግሎት የሚያስበው ሠራተኛ ደግሞ ሥራውን የተቀበለው ከእግዚአብሔር እንደሆነ በማመን በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር ክብርን ለመስጠት በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሚሠራላቸውን ሰዎች ለመጥቀም በመጨረሻም ከሁለቱ ውጤት የተነሣ ለራሱም ይጠቀማል። በዚህ አሳብ መሠረት ሥራን እገልግሎት ወይም «ተራ» ሥራ የሚያደርገው የሠራተኛው የውስጥ አሳብና ዓላማ እንደሆነ መመልከት ይቻላል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ተከታዮች የሚያደርጉትን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲያደርጉት ይመክራቸው ነበር። «በቃል ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት» (ቆሊ.3:17 ይላል። ክርስቲያኖች ሥራቸውን እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ያስቀመጠውን መመሪያ በመከተል፣ የአሠሪያቸውን ብቻ ሳይሆን የክርስቶስን ሥልጣን በመፍራት፣ የሚሠሩት ከእርሱ ባገኙት አውቀትና ችሎታ እንደሆነ በመረዳትና በማሳወቅ ከሁሉም በላይ እምላካቸውን ለማክበር በሚሠሩበት ጊዜ ሥራቸው «ተራ» ሥራ መሆኑ ይቀርና እገልግሎት ይሆናል። ክርስቲያኖች «ይህን ሥራ የሰጠኝ እግዚአብሔር ስለሆነ ለእርሱ ክብርን ለማምጣት መሥራት አለብኝ» ብሎ የመጀመሪያ ተጠያቂነታቸውን ለእግዚአብሔር ሲያደርጉ ሥራቸው እገልግሎት ይሆናል። በኢየሱስ ስም የተደረገ መልካም ሥራ እገልግሎት ነው። ሥራን በኢየሱስ ስም ማድረግ ማለት በጸሎት መጀመር ብቻ እንዳልሆነ ሊታሰብበት ይገባል። ሥራውን ለጌታ ኢየሱስ ክብርን ለማምጣት በተነሳሳ ልብ ማድረግ ነው።

ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው መንፈሳዊ ሥራ ማለትም በቤተክርስቲያን ውስጥ ሆነው ሙሉ ጊዜን ሰጥቶ (መንፈሳዊ፣ መጋቢ፣ የወንጌል አስተማሪ የመሳሰሉት በመሆን) ማገልገል እንደሆነ ያስባሉ። መንፈሳዊ ሥራዎች እንጂ በዓለም የሚሠሩ ሌሎች ሥራዎች እገልግሎት እንደሆኑ አያስቡም። በቤተክርስቲያን ወንጌል ሲሰበክም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረጉ ያሉ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ሥራዎችን የሚሠሩ እንደሆነ ነው። አንድ ሰው በእንድ ሥፍራ ወንጌልን ሲያስተምር ቀድሞ ይሠራ በነበረበት ድርጅት ውስጥ ሲሠራ እንድ ቀን «ጌታ ሆይ! እንደ በሬ በልቼና ጠጥቼ የምኖረው እስከ መቼ ነው?» ብሎ እግዚአብሔርን እንደጠየቀ ይናገር ነበር። አሁን እግዚአብሔር ከዚያ አውጥቶ መንፈሳዊ አገልጋይ እንዲሆን እንዳደረገው ይመሰክራል። ሰዎች የራሳቸውን አሳብ ለመግለጽ የሚጠቀሙበት አገላለጽ ፍጹም አስመሆኑ ቢታወቅም ይህ አባባል መንፈሳዊ አገልግሎትን በከፍታ ሥፍራ ላይ አስቀምጦ መንፈሳዊ የማይባለውን ሥራ መሥራትን ደግሞ እንደ በሬ ስመብላትና ለመጠጣት ብቻ እንደ መኖር የሚያስቆጥር ነው። ይህና እነዚህን የሚመስሉ አባባሎች የሚሰማ ክርስቲያን የሚሠራውን ሥራ እግዚአብሔር የሰጠው አገልግሎት እንደሆነ እንዲያስብ የሚያበረታቱ አይደሉም።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ማለት በቤተክርስቲያን ውስጥ የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይ መሆን ብቻ እንደሆነ የሚታሰብ ከሆነ

ክርስቲያኖች ሌሎች ሥራዎችን መሥራት የሰባቸውም ማለት ነው። በእርግጥ አያንዳንዱ ክርስቲያን በግሉ ሊጠየቅ ክርስቲያን ማንኛውንም ለእግዚአብሔር ክብርን የሚሰጥ ሥራ መሥራት ይችላል የሚል ምላሽ ይሰጣል። ነገር ግን የወንጌል ስብከትና ትምህርት ቅኝቱ ግን አሁንም ያዘነበለው ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር ባስቀመጣቸው ሥፍራ ለእርሱ ክብር እንዲኖሩ ሳይሆን ሰባኪዎቹ መንፈሳዊ ነው ወደሚሉት ሥራ እንዲያዘነብሉ ነው። ይህን ለማረጋገጥ በየሥፍራው የሚሰጡትን መንፈሳዊ ትምህርቶችና ስብክቶችን መገምገም ይቻላል።

ምን ዓይነት አገልግሎት ለቤተክርስቲያን መስጠት ይቻላል?

የሙሉ ጊዜ እገልጋይ ያልሆነ ክርስቲያን ወይም ወንጌልን ለማስተማር በቂ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሌለው ወይም እንዲህ ጎላ ብሎ የወጡ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች የለኝም የሚል ክርስቲያን ምን ዓይነት መንፈሳዊ አገልግሎት በቤተክርስቲያን ውስጥ መስጠት ይችላል? መልካም ሥራ የሚባለው የሙሉጊዜ የወንጌል አገልጋይ መሆን እንደሆነ መታሰብ የለበትም። ሥራን መንፈሳዊና ሥጋዊ ብሎው የከፈሉት ክርስቲያኖቹ ናቸው እንጂ ቃሉ እንዲህ ዓይነት አሳብ አይሰጠንም።

ችሎታን በተፈጥሮም ወይም በትምህርት ተገኘ ቢባል ምንጩ እግዚአብሔር ነው። በዚህ ችሎታ የሚሠሩ እንደ ቃሉ የሆኑ ሥራዎች ሁሉ እስደሳቢ ናቸው። አያንዳንዱ ሥራ የሚያስፈልግበት ቦታ አለው። እንዱ ሌላውን የሚያግዝ ነገር አለው። በስተማ ውስጥ ኤሌክትሪክ የሚሠራ ሠራተኛ ባይኖር የኤሌክትሪክ ብልሽት ቢያጋጥም ማን ሊያስተካክል ይችላል? ኤሌክትሪክ ባይኖር መንፈሳዊ ሥራዎች ሊቋረጡ ይችላሉ። የኤሌክትሪክ ሙያ ያለው ሰው ቢመጣና ብልሽቱን ቢያስተካክል ለእግዚአብሔር ሥራ እገዛ አደረገ ማለት ነው። እንደ ክርስቲያን እንዱ ሥራ ከሌለው እንደሚበልጥ ከማሰብ ይልቅ ሥራዎች ሁሉ በፈሪሃ እግዚአብሔር ከተሠሩ የሚደጋገፉና ለእግዚአብሔር ክብር የሚሰጡ መሆናቸውን ማሰብ የተሻለ ነው። ማንኛውም ተገቢ ሥራ በታማኝነትና በትጋት ለእግዚአብሔር ክብርን ለመስጠት ቢሠራ መልካም ነው።

እንዳንድ ጊዜ ጥቃቅን የሆኑ አሳቦች ወደ ክርስቲያኖች አእምሮ ውስጥ ገብተው አመለካከታቸውን ያበላሻሉ። ጥቃቅን ቢሆኑም ውስጥ ለውስጥ እየቦረቦሩ አቅጣጫን ያስስውጣሉ። አንደ ክርስቲያን በሥራና ለሥራ ሥነምግባር ላይ ማመቻመች ማለትም አንደ እግዚአብሔር ቃል እስማድረግ ቀስ በቀስ እያደገ ይሄድና ሕይወትን ይወርሳል። ሰይጣንም በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ መግባት የሚችሰው ጥቂት ትክክለኛ ያልሆነ አሳብ አስቀድሞ በማስገባት ነው። አንድ ጊዜ ከተከክለኛው አስተሳሰብ ካስወጣ ትክክለኛ ወዳልሆነ ድርጊት ይመራል። ክርስቲያናዊ ያልሆነ ድርጊት ሊፈጸም ደግሞ የበደለኛነትን ስሜት ያስከትላል።

እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ የወንጌል አገልጋዮች እንዲሆኑ አልጠራም። ሁሉም የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይ እንዲሆን አልተጠራም። ነገር ግን አያንዳንዱ በክርስቶስ ያመነ ሁሉ በዓለም ውስጥ የክርስቶስ ምስክር እንዲሆን ተጠርቷል። ለወንጌል አገልግሎት የተጠሩ አገልጋዮች በትጋት የወንጌልን ሥራ እንዲሠሩ እንዲሁም ለወንጌል አገልግሎት የሚያስፈልገው ሀብት እንዲገኝ ምዕመናን ተግተው ሠርተው

ለወንጌል አገልግሎት መስጠት ይችላሉ። ይህ የማይሆን ከሆነ የታላቁ ተልዕኮ እንደሚገባ ከግብ አይደርስም። የክርስቶስ ተከታዮች በሁለት መልኩ ለታላቁ ተልዕኮ ስኬት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። የመጀመሪያ ከላይ እንደ ተጠቀሰው ሠርተው ከሚያገኙት ገቢ በገንዘብና በቁሳ ቁስ በመደገፍ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ሥራቸውን በትጋት በመሥራት ለሌሎች ሰዎች ምሳሌ ሆነው በተግባር ምስክርነት በመስጠት ነው (1ጢሞ6:1፤ ቲቶ2:9፤10)።

ክርስቲያኖች አንድ ማወቅ የሚገባቸው አሳብ አለ። ይኼውም እያንዳንዱ ክርስቲያን ከዚህ ከጨለማው ዓለም ሥርዓትና የሕይወት ዘይቤ የተጠራው የእግዚአብሔርን በጎነት እንድነግር ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ ስምዕመናን እንዲህ የሚል መልዕክት ጽፎላቸዋል።

> እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ሰርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» (1ጴጥ2:9) ይላል።

እግዚአብሔር ለምኞን ከዚህ ከጨለማው ሥርዓት በልጁ ደም ገዝቶ ነጻ ያወጣቸው የእርሱን በጎነት እንዲነግሩ ነው። ምዕመናን የእግዚአብሔርን በጎነት የሚናገሩት ለምዕመናን ላይሆን እነርሱ ከመጡበት በጨለማው ዓለም ውስጥ ለሚገኙ ለምኞ ናቸው። እግዚአብሔር በሕይወታቸው ያደረገውን ለውጥ በአንደበትና በድርጊት ይናገራሉ። ይህ ሥራ የእያንዳንዱ ከጨለማ ወጥቶ ወደ ብርሃን የመጣ አማኝ ኃላፊነት ነው። ይህን ኃላፊነት ለመወጣት ደግሞ የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይ መሆን አያስፈልግም። ምዕመናን ተበታትነው ባሉበት በማንኛውም ሥፍራ ለክርስቶስ ኢየሱስ ምስክሮች መሆን ይችላሉ። ስለዚህ ወደ ቤተክርስቲያን በመምጣት እርስ በርስ ለመሚሚቅ መቻላቸውን እንደ ትልቅ መንፈሳዊነትና አገልግሎት መቁጠራቸውን መተው ይገባቸዋል። ብርሃናቸው ደምቀው የሚታየው እንዲሁም ለምኞን ከጨለማው ዓለም ወደ ወንጌል ብርሃን ማምጣት የሚችሉት ባለመኑ ለምኞ መካከል ሲሆኑ ነው። ካለመኑ ለምኞ ጋር ስመሆን አንዱ ምቹ ሥፍራ ደግሞ የሥራ ቦታ ነው።

እግዚአብሔር ለወንጌል አገልግሎት በልዩ ጥሪ ስጠራቸው ለምኞ ውጭ ሌሎች ምዕመናን እንደ እግዚአብሔር ቃል በሆነ ሥራዎቻቸው እግዚአብሔርን ማክበር ይገባቸዋል። ሥራዎቻቸው መንፈሳዊ እንዳልሆኑ አስበው መስነፍ አይገባቸውም። መንፈሳዊ አገልግሎት የሚባለው የግድ ወንጌልን መስበክ፣ መንፈሳዊ ፕሮግራም መምራት፣ የመዘምራን አባል ሆኖ መዘመር፣ ዲያቆን ሆኖ የአስተዳደር ሥራ መሥራት፣ ብቻ አይደለም።

ሥራ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መንፈሳዊ የሆነና መንፈሳዊ ያልሆነ ተብሎ ሳይሆን ከተገለጠው ከእግዚአብሔር አሳብና ፈቃድ ጋር የማይቃረን ሥራ ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለለው ልጆች ጥቅምና መታነጽ ከተሠራ መልካም ነው። በተለያየ ሙያ በተለያየ ዓለማዊ ወይም ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ክርስቲያኖች በሙያቸው ቤተክርስቲያንን ቢያገለግሉ እግዚአብሔር በስጣቸው ችሎታና በተማሩት አውቀት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን አገልግለዋል ማለት ነው። ለምሳሌ መሐንዲሶች ለምዕመናን የአምልኮ ቤት ዲዛይን ቢሠሩ፣ ግንበኞች ቤቱን ቢገነቡ፣ የኤሌክትሪክ ባለሙያዎች ኤሌክትሪክ መስመር ቢዘረጉ፣ የቧንቧ ሠራተኞች በቤቱ ውስጥ ቧንቧውን ቢዘረጉ፣ አናጢው ቆርቆሮውን ቢመታ፣

እንዲሁም ሌሎችም ቤቱ አስኪያልቅ ድረስ የሚያስፈልገውን ነገር ቢያደርጉ ይህ አገልግሎት አይደለምን? የግድ እነዚህ ለምኞ መንፈሳዊ አገልግሎት ስመስጠት መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር ወይም የሆነ መንፈሳዊ ኮሚቴ ውስጥ መግባት አለባቸውን? የለባቸውም።

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሲፈጥር የሠራቸው ሥራዎች መንፈሳዊ የሆኑ ወይስ መንፈሳዊ ያልሆኑ ናቸው? እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሊፈጥር የወንጌል ስብከት አሳደረገም። ለነገሩ የለው ልጅ ስብልተፈጠረ ለማን ይለብክ ነበር! ሥራዎቹን ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ ግን የሠራቸው ሥራዎች ሁሉ እጅግ መልካም እንደሆኑ ተናግሯል (ዘፍ.1:31)። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ የለው ልጅ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ብቻ እንዲጎለብት የሚጠቅሙ ድርጊቶች ብቻ አልነበሩም። የእርሱ ሥራዎች ሁለንተናዊ ጥቅም አላቸው። እግዚአብሔር ሥራዎችን ሲሠራ ሥራዎቹ ሁሉ በእምነት (መዝ.33:4)ና በጥበብ (መዝ.104:24) ይሠራሉ።

በዚህ ዓለም ላይ የለው ልጅ የሚሠራው ሥራዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት መልካም አይደሉም። አንዳንድ ሥራዎች መልካም ሲሆኑ ሌሎቹ ግን ከፋዎች ናቸው። የክርስቲያኖች ሥራ ግን መልካም ሥራ ሲሆን እንደሚገባ ታዘዋል። ክርስቲያኖች ክፉ ሥራዎችን ለሚሠሩ ለምኞ መልካምን ሥራ ሠርተው ማሳየት እንደሚገባቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ አስተምሯል። ክርስቲያኖች ክርስቶስን ባለመኑ ለምኞ መካከል ሲኖሩ በሚሠሩት ሥራ ትጋትን፣ ታማኝነትንና ፍትሕን በማሳየትና ክርስቶስን የሚመስል ባሕርያት በማሳየት ለምኞ እግዚአብሔርን በእነርሱ ሕይወት ውስጥ እንዲመለከቱ በማድረግ ነው። ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ከክርስቲያኖች ጋር የሚደረጉትን ሥራዎችንማ የት ያዩታል?

> *ክርስቲያኖች የሚሠሩትን ማንኛውንም እንደ ቃሉ የሆነ ሥራ እንደ አገልግሎት መቁጠር የሚችሉ ከሆኑ መንፈሳዊ አገልግሎት በቤተክርሰቲያን መስጠት ያስፈልጋቸዋል? በሁለቱም ሥፍራ ከሚወጠሩ አንዱን ብቻ በተገቢ ሁኔታ ቢሠሩ ምን ችግር አለው?*

ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካል ብልቶች በመሆናቸው ለአካሉ ማስትም ለቤተክርስቲያን መታነጽ እያንዳንዳቸው ስጦታ አላቸው። ይህ ስጦታቸው ምን እንደሆነ ሳይተው በማወቅ በሙያቸው ወይም እግዚአብሔር በውስጣቸው ባስቀመጠው ማንኛውም ስጦታ ማገልገል ይችላሉ። ከላይ ለመጥቀስ የተሞከረው ሁሉም ክርስቲያን «መንፈሳዊ» የሚባሉትን ሥራዎች ለመሥራት ከማስብ የተነሣ እግዚአብሔር እንዲሠራ የሚፈልገውን ሥራ ላይሠራ መቅረት እንደሌለበት ነው። በዓለም ውስጥ በሚሠሩት ሙያና ስጦታ ወይም በተለየ ልዩ ስጦታ ቤተክርስቲያንን በሚያገለግሉበት ጊዜ ክርስቲያኖች ሚዛን መጠበቅ ይገባቸዋል።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅደም ተከተልን የሕይወት መርሕ ማድረግ

ለአንድ መንፈሳዊ አገልጋይ የተጠቀሱ መርሆዎች ለምዕመናንም ተግባራዊ ይሆናሉ። ከሁሉም በላይ ቅድሚያ የሚለጠው በግል ከእግዚአብሔር ጋር ተራክቦ ለማድረግ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው

ደግሞ ለቤተሰብ አሰፈላጊውን ትኩረት መስጠት ነው። ከቤተሰብ ቀጥሎ የሚመጣው ጉዳይ ሥራ ነው። በቤተክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎት የሚመጣው ከዚህ በኋላ ነው። አንድ የክርስቶስ ተከታይ የሚሠራው ሥራና በቤተክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎት የቤተሰብን ሕይወት የሚያንጽ አንጂ በቅርብ ወይም በረጅም ጊዜ የሚጎዳ ሊሆን አይገባም። ስለሆነም ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚሰጠው ጊዜ ሥራንና የቤተሰብ ሕይወትን ከዚያም በግል ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን የጥሞና ጊዜ አስከማይጎዳ ድረስ ነው።

አንድ መንፈሳዊ አገልጋይ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ የዕሰት ሥራውን ይሠራል። አንድ ምዕመን ግን መንፈሳዊ አገልግሎት በቤተክርስቲያን በሚሰጥበት ጊዜ በየዕሰቱ ከሚሠራው ሥራ በተጨማሪ ሌላ ሥራ ይሠራል። ይህ ደግሞ በሕይወቱ ላይ ጫናን እንደሚያመጣ የታወቀ ነው። ቀን ሥራ እየሠሩ ውሰው ማታ ወይም ሳምንቱን ሁሉ ሥራ ሊሠሩ ከርመው በሰንበት ቀን በመንፈሳዊ አገልግሎት ይጠመዳሉ። ይህ በግል ሕይወታቸው ከእግዚአብሔር እንዲሁም ከቤተሰባቸው ጋር የሚኖራቸውን ጊዜ እጅግ ይሻማል። ከዚህም የተነሣ መንፈላዊ ሕይወታቸውና የቤተሰባቸው ሕይወታቸው ይናጋል። በቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎትን መሰጠት በራሱ የግል መንፈላዊ ሕይወትን አያሳድግም እንዲሁም ቤተሰብን እግዚአብሔርን የሚያስከብር ቤተሰብ አያደርግም። ሁለቱም ጊዜ በመሰጠት መሥራትን የሚጠይቁ ጉዳዮች ናቸው።

አንግዲህ ክርስቲያን ሥራን በትጋት መሥራት ይኖርበታል። የሚሠራው ሥራ በዘላቂነት ፍሬያማ እንዲሆንና የሠራተኛውን ሁለንተናዊ ሕይወት በሚጠቅም ሁኔታ እንዲሆን እረፍት ያስፈልጋል። ክርስቲያን አንደ ማንኛውም ሠራተኛ ቢሠራም በቤተክርስቲያንም ድርሻ አለው። ይህንንም ድርሻውን ደግሞ ሥራውን፣ ቤተሰቡንና ሕይወቱንም በማያዳሽቅ ሁኔታ በሙያው በማገልገል ወይም ሠርቶ ከሚያገኘው ገቢ ሰታሳቁ ተልዕኮ መሳካት ድጋፍ በመሰጠት መወጣት ይችላል። ከሁሉም በላይ ግን በሚሠራበት ሥፍራ ባሳመኑ ሰዎች መካከል በቃልና በተግባር የሚመሰክርለት በመሆን ያገሰግላል። በክርስቶስ ባሳመኑ ሰዎች መካከል ብርሃን የመሆንን ተልዕኮ ትቶ በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ «መንፈላዊ» አገልግሎቶችን በመስጠት መባከን በእግዚአብሔር ፊት ሚዛን የሚደፋ አይሆንም።

Bibliography

Adams, J. (1972). *Christian Living in the Home*. NJ: Phillipsburg, Presbyterian and Reformed Publishing Company.

Adams, J. (1975). *Shepherding God's Flock*. Grand Rapids, MI: Zondervan Publishing House

Cloud, H. & Townsend, J. (1992). *Boundaries*. Zondervan Publishing House.

Fernando, A. (1985). *Leadership Life Style*. Wheaton, IL: Tyndale House Publishers, Inc

Miles, R.L. (1999). *The Pastor as Moral Guide*. MN, Fortress Press.

Murray, A. (1983). *How to Work for God*. Whitetaker House.

Parker, T.HL (1965). *Calvin's Commentaries*. Grand Rapids, MI: Wm.B. Eerdmans Publishing Company.

Shawchuck, N. and Heuser, R. (1993). *Leading the Congregation: Caring for Yourself While Serving Others*. Nashville, Abingdon Press.

Stott, J. (1989). *The Message of Ephesians*. Inter varsity Press.

Stott, J. (1996). *The Message of I Timothy and Titus*. Inter varsity Press

Sugden, H.F. and Wiersbe, W. W. (1980). *Confident Pastoral Leadership*. Cbicago, Moody Press.

ክበደ በከሬ (1997). *ልጆቻችንን እንዴት እናሳድጋቸው?* አአ

ክበደ በከሬ (1997). የስኬታማ አገልግሎት መርሆዎች። አአ